በፍቅር፤ በሰላም፤ በአንድነት
ተከባብሮ ለመኖር
መደማመጥ!
መቻቻል!

ኢትዮጵያዊ
የማህበራዊ ጉዳይ መጽሔት
በአማርኛ

$2.75

# ላንዳፍታ



## በስደት ላይ ያሉት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ አሜሪካን ገቡ። (14)

ታህሣሥ/ጥር
፲፱፻፺
ዓመት
ቁጥር ፪

# LANDAFTA

An Ethiopian Cultural Magazine in Amharic
(Amharic is the Official Language of Ethiopia)
Dec'97/Jan'98
Vol. 6 No.2

# የኢትዮጵያ መንደር





## ETHIO VILLAGE

### CAFE & RESTAURANT

**3462 N. Clark St.**
**Chicago, IL 60657**
**(312) 929-8300**

CATERING AND CARRY OUT AVAILABLE



## በቺካጎ ታላቁ የኢትዮጵያ ምግብ ቤት

ቀይወጥና ዝግኑ ዶሮ ወጥ አልጫው፤
አትክልት ከሥጋ ጋር ምንቸት አብሽ ክትፎው።
የአበሻ ዳቦና ቆንጆ የማር ጠጅ
ሽታው ግቡ ይላል ገና እያሉ ደጅ።
ቆርጠው በሩን ከፍተው ገባ ሲሉ ገና፤
አገርዎ የገቡ ያስመስላልና።
ዱለት የበግ ወጡ አልጫ ፍትፍቱ፤
ዕሮብና ዓርብ ዕለት የጾም በያይነቱ።
በአስራሁለት ዓመት ልምድ የሙያ ክምችት
ፍጹም ኢትዮጵያዊ ለሆነ ዝግጅት፤
ኢትዮ ቪሌጅ ይምጡ ሲያሻዎት መደሰት፤
አገር ሲናፍቆት።

አፀደ ይመር

# ላሊበላ የኢትዮጵያ ምግብ ቤት

# LALIBELA ETHIOPIAN CUISINE

ላ
ሊ
በ
ላ



በቅርቡ በአዲስ አስተዳደር ሥራውን
የጀመረውና ጣዕም ያላቸውን የአገር
ምግቦችን የሚያቀርበውን
ላሊበላ ምግብ ቤትን
ብቅ ይበሉና ይጎብኙ!
ጣፋጭ ምግቦቻችንንም ይቅመሱ!
በመስተንግዷችን ይደሰታሉ!
በምግባችን ጣዕም ይረካሉ!!




ከእሁድ – ሐሙስ – 11:00 am - Midnight
ዓርብና ቅዳሜ – 11:00 am - 2:00 pm

ለስለስ ያሉ ራት ላይ
የሚደመጡ የባህል ሙዚቃዎች
በመሣሪያ
(ዓርብና ቅዳሜ ምሽቶች)

ኤልሣቤጥ ሙሉጌታ
ዋና ሥራ አስኪያጅ
Elizabeth Mulugeta
Manager

LALIBELA ETHIOPIAN CUISINE
243 Ponce De leon Ave. NE
Atlanta, GA 30308
(404)876-3630

# ማ ው ጫ CONTENTS


3 ከአዘጋጁ

4 ሰላምታ ከወደ አገር ቤት (ወርቃየሁ)

6 ሰላምታ ከባህር ማዶ (ገብርዬ)

12 ከአንባብያን

14 እንዲህ ሆነ (ከዜና ማህደር)

21 አዳምና ሔዋን
“ዕጣዬ” (አብረኸት)

24 የስነ ጽሑፍ ገፀበረከት — ገሞራው

26 ልብ ወለድ
“ፀሐይ ምሽት” (ሰይፉ ላዳነች ብሻው)

31 “አገርንና ሃይማኖትን. . .” (ከበደ አገኘሁ)

36 የግጥም ጉባኤ

38 “ኢትዮጵያና የኦርቶዶክስ ...” (ቀሲስ ኤፍሬም አ. ከበደ)

41 ዜና ቤተ ክርስቲያናት

42 ከአበው (መጋቢ አእላፍ መክብብ አጥናው)

43 ኑሮ በአሜሪካ
“እልፍ ሲሉ እልፍ ሊገኝ” (አትናትዮስ)

45 ቅምሻ (ጥምቀተ አሮዲዮን)

47 የሰንጠረዥ ጨዋታ




ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ (14)



ደራሲ ኃይሉ ገብረዮሐንስ (ገሞራው) — (24)



ሯጭ አረጋ አብርሃ
የእድሜ ልክ እስራት ተበየነበት
(17)

ሽፋን — ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ (ፎቶ የለገሱን — ኢትዮጵያ ሪቪው መጽሄት)


ላንዳፍታ የግል መፅሔት ናት። የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ የአዘጋጁን አመለካከት ወይም እምነት ያንጸባርቃሉ ማለት አይደለም። ጽሑፎቹን በሬዲዮ፤ በቴሌቪዥን ሆነ በተመሳሳይ መንገድ በከፊልም ሆነ በሙሉ አባዝቶ ለማሰራጨት የፀሐፊውንና የአዘጋጁን ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል። በተለይ የፈጠራ ድርሰቶች መብታቸው በሕግ የተጠበቀ መሆኑን መግለጽ እንወዳለን።

© COPYRIGHT LANDAFTA 1997

ላንዳፍታ
ታህሳስ/ጥር ፲፱፻፺
6ኛ ዓመት ቁጥር 3
LANDAFTA
DEC/JAN 1998 Vol. VI - No.3

አዘጋጅና አሳታሚ
መኮንን ገሠሠ
**Publisher/Editor**
*Mekonnen Gessesse*
**Assistant Editor:**
*Genet Wolde*
**Contributors:**
*Workayehu (pen name)*
*Gebrie (Pen Name)*
*Saefu Bishaw*
*Wuhib Tiruneh*
*Kesis Ephrem*
*Rev. Mekbib Atnaw*

**Editorial Advisors**
*Lisanu Simret*
*Dr. Getachew Metaferia*
*Dr. Abera Molla*
*Dr. Tilahun G. Hiwot*
*Dawit Deres*

**Distribution**

Atlanta, GA
California Mart
Sweet Auburn Grocery
H & B Shop
Nazareth Restaurant
Express Food Mart
Merkato Market
Chicago, IL
Ethio-Village Rest.
Dallas, TX
Maru Grocery
Abeba Grocery
Durham, NC
Blue Nile Eth. Cusine
Denver, CO
Emebet Worku
Houston
Queen of Sheba Rest.
Maru Grocery
L.A., CA
Merkato
Coffee Damera
Oak Land, CA
Albo-African Shop
San Diego, CA
Axum Market
San Jose, CA
St. Claire News Stand
Santa Clara, CA
Nathan Graphics
Seatle, WA
Arat Kilo Deli Grocery
St. Louis, MO
A & Z Liquor
St. Paul, MN
Merkato
Washington D.C. area
Addisu Gebeya
Nini Market (Alex.)
Tana (Silver Spring)
Lideta Market (Arlington)
Windsor, Ontario
Tewodros Zewdu
London
St.Gabriel Ethiopian Delicatseen

# ከአዘጋጁ

## እንኳን ለብርሃነ ልደቱ አደረሳችሁ!!

እንዴት ከረማችሁልን? በመጀመሪያ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ተከታዮችን እንኳን ለጌታችንና ለመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል አደረሳችሁ እንላለን።

በዛሬው እትማችን፤ ለረዥም ዓመታት ኬንያ በስደት ላይ የቆዩት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ አሜሪካ መግባታቸውን የሚገልፅ አጭር ዜና አለን። ይህን በተመለከተ ወደፊት ሰፋ ያለ ዘገባ እናቀርባለን። በዚህ እትም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያንን በተመለከተ በርከት ያሉ ጽሑፎች ያቀረብነው የብፁዕነታቸውን ወደዚህ መምጣት በማስመርኮዝ መሆኑንና ይህች ትልቅ ታሪክ ያላት ቤተክርስትያን ኢትዮጵያን ለማዳን ማድረግ ስለምትችለው አስተዋጽዖ ቀደም ሲል የቀረቡት ጽሑፎችን መሠረት በማድረግ ነው።

ወርቃየሁና ገብርዬ በየጊዜው የሚለዋወጡትን ደብዳቤዎች ብዙ አንባብያን በናፍቆት እንደምትጠብቁት ገልጻችሁልናል። እነሱም ይኸው የደብዳቤውን ልውውጥ ቀጥለዋል።

"እልፍ ሲሉ እልፍ ሊገኝ!!" የሚለው የገጠመኝ ታሪክ የመጨረሻው ታሪክ በዚህ እትም ላይ ቀርቧል። ለወደፊቱ ማህበራዊ ጉዳይን ያስመረኮዙ ሌሎች የገጠመኝ ታሪኮችን ለማቅረብ ተዘጋጅተናል። ተቋርጦ የነበረውና ብዙ አንባብያን የጠየቃችሁን "ዕጣዬ" የተሰኘው ተከታታይ ታሪክ ከአሁኑ እትም ጀምሮ ይቀርባል። አብረኸት በየወቅቱ የደረሰባትን ታሪክ ትምህርት እንዲሆነን እየነገረችን ናትና እስቲ እናዳምጣት።

በዜና አምዳችን ባለፉት ሁለት ወራት አገራችንን በተመለከተ የተከናወኑና የደረሱን ዜናዎችን አውጥተናል። ሌሎችም የተለያዩ ዝግጅቶቻችን በየአምዱ አቅርበናል። እንግዲህ መስተናገዱን ለእናንተ ትተን ብንሰናበታችሁስ።

ስለመጽሔታችን ያላችሁን አስተያየትና ስለዕድገቷ
የምትሰጡንን ምክር በአድራሻችን ላኩልን።

የላንዳፍታ መፅሔት ዝግጅት ክፍል
LANDAFTA
P.O.Box 49301, Atlanta, GA 30359
Phone: (404) 508-4657 Fax: (404) 508-2447
E-MAIL- landafta@aol.com
HOME PAGE:
http://www.ethiopic.com/landafta.htm

*Landafta is an independent magazine published bi-monthly in Amharic. Views expressed do not necessarily represent that of its editors and advisors.*

# ሰላምታ ከወደ አገር ቤት
## ከወርቃየሁ

ወዳጄ ገብርዬ!

ሰላምታዬ በአያሌው ይድረስህ፤

እኛ በዚችው በደከመች አገር እንደአቅሚቲ በያቅጣጫው ሩጫ ይዘናል። ኑሮና ብልሃቱ አልጣጣም ሲለን ለማገጣጠም እንታከታለን። የአገራችን ጉዳይና ሁኔታ ቁልቁል የመሄዱን ነገር አሳምሮላታል። በውስጧ የምንኖረው እኛ ደግሞ ሽቅብ ያለው ያምረንና አልሆንልን ሲለን እንመቀኛኛለን፣ ለመጠፋፋት እንሽቀዳደማለን። ለተሾመው፣ መሣሪያ ለያዘው፣ ለጐፈሬያሙ ሁሉ ማጐንበሱ ይቀናናል። ለእኛ የበጀን እየመሰለን ነገ በተራችን መውደቃችንን ሳናውቀው እንገፋፈጣለን፤ አንዳችን በሌላው ጥፋት ለማደግ። ታዲያ የቁልቁል አወራረዳችን ፍጥነት በአሁኑ ጊዜ ሩዋንዳና ሶማሊያ ካልቀደሙን በቀር በዚህ አያያዛችን ነገ በእጥፍ ሳንደርባቸው አንቀርም። አንዳንዴ ምርር ሲለን መፈጠራችንን እንረግምና «ይህችን አገር ጥለን በሄድን» እንላለን። ድሮ ድሮ ያኔ የነበረው ምኞት «ተምሬ፣ ትዳር መስርቼ፣ ቤት ሰርቼ፣ ልጆቼን አሳድጌ ...» ነበር። ዛሬ ግን «ይህችን አገር ለቅቄ፣ ወይ አረብ አገር ወይ አሜሪካ ሄጄ! ተገላግዬ» ሆኗል። በሃሳብ እኮ ወደናንተ ተጉዘን ደርሰን ከተመላለስን ብዙ ጊዜ ሆኗል፤ ግን ይህ ሁሉ ለምን እንደሆነ ሳይገባህ አይቀርምና ዝርዝሩን ልተወው።

ወዳጄ ገብርዬ!

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደብዳቤዎቼ አጠር ያሉ መሆናቸው ከምን እንደመነጨ የገለፅኩልህ አይመስለኝም። አንተም አልጠየቅሽኝም። «ሁሉን ቢያወሩት ሆድ ባዶ ይቀራል» አለ አሉ የአገሬ ሰው። ቀደም ብዬ ብዙ ለፈለፍኩ፣ ብዙ አልኩ። ያኔ ጥንት ይግለጡ የሚባል የብዕር ጓደኛዬ ከወደ እናንተ ሰፈር አፍርቼ የልቤን ስዘከዝክለት ከረምኩና ምን እንዳስቀየምኩት አላውቅም፤ ደህና ሁን እንኳ ሳይለኝ ጠላትህ እልም ይበል በዛው እልም አለ። ሆድ የከፋው የሚናገረውን አያስተውልምና ምናልባት አንድ ነገር ብዬ አስቀይሜው ይሆን? እያለ ሆዴ አሁንም ይፈራል። ደግሞም እኮ የሰው መዋያውና መከረሚያው አይታወቅም፤ ለምን አልፈራ? እና እንደገና እኔም ለአንተ ያንንም ያንንም ሆድ በባሰው አንጀቴ ስቀባጥር ሳላስበው አንተን ወዳጄን የማስቀይም እየመሰለኝ በመፍራት ከወደ ቃላቶቼ ቆጠብ ለማለት መሞከሬ ነበር። ሳይህና ስከታተልህ ግን እንደ ጥንቱ ወዳጄ ይግለጡ ‹‹ሆደ ባሻ›› አልመሰልከኝምና እስቲ እኔም የልቤን ልንገርህ።

ገብርዬ «ደብዳቤዎችህ» ጥሩ ትምህርት ቤት ሆነውልኛል ብል ማጋነን አይሆንብኝም። እኔ ብቻ ሳልሆን በዙሪያዬ ያሉ አድናቂዎችህ በሙሉ ብዙ ዕውቀት እየኮመኮምን ነው። ባለፈው አትም በፃፍከልኝ ውስጥ ብዙ ቁም ነገር አስተማረኝ። በተለይ የሃይማኖት ስነመለኮትን በማስመልከት ቀደም ሲል በመደጋገም ከፃፍከው ጋር በማያያዝ ያለፈው መልዕክትህ ሰሚ ቢያገኝ ከገባንበት ማጥ መውጫ መፍትሔ እንደሚሆን ቁልጭ ብሎ ታይቶኛል። ለጠቅ አድርገህም በስደት ዓለም እያደጉ ያሉና እየተወለዱ ያሉ ልጆቻችን የአስተዳደግ ሁኔታ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ የገለፅከው «እንጀራ ይውጣልህ» የሚያሰኝህ ነው። አንተ እንዳልከው የሃምራዊት ተስፋዬ ደበሳይን ደብዳቤም መልሼ አነበብኩትና ዓይኔ በእንባ ተሞላ። እግዜር ይህን ትውልድ ረግሟል ልበል? ገብርዬ! እዚያ ስላለው ትንሽ ተስፋ ስለጣልንበት ወጣት ይህን ስትነግረኝ እዚህ ያለውንስ ብታይ ምን ልትለው ይሆን? ዛሬ በትላልቅ ከተሞቻችን በተለይ አዲስ አበባ ባህላችን በወጣት ልጆቻችን የመጠበቁን ነገር ተወው፣ ከስርዓት ውጪና ዓላማ ቢስ ሆነው የምዕራቡ ዓለም የባህል ወረርሽኝ ሰለባ እንዲሆኑ እየተገፉፉ ናቸው።

መሸት ሲል የአዲስ አበባ ከተማ ጐዳናዎች ዕድሜያቸው ከ19 ዓመት በታች በሆኑና አጫጭር ባት ገላጭ አጣብቂኝ ልብስ በለበሱ ቆነጃጅት ሕፃናት ሴቶች ልጆች ሲወረሩ ስታይ ምን ይሰማህ ይሆን? አላፊ አግዳሚውን በዓይናቸው ሲያባብሉት ስታይና ከነሱ መሃል አንዷ የአንተ ልጅ ብትሆን ምን ትል ይሆን? ገብርዬ! ዛሬ በሽታው በተስፋፋበት፣ በተለይ ቀሳፊው የኤድስ በሽታ በአገራችን ሕዝቡን ቀስ በቀስ እየፈጀ ባለበት ወቅት እነኚህ የነገ ፍሬዎቻችን፣ የነገ አገር ገንቢ ልጆቻችን፣ የዛሬ አበባነታቸውን እንደዚህ ባለ ሁኔታ ሲቀጥፉት ስታይ ተስፋ አያስቆርጥምን? ምናልባት አዲስ አበባ ውስጥ «የራቁት ትርዒት» (Nudismና Stripping በእናንተ ቋንቋ) ገብቷል፤ ሴቶች ልጆቻችንና እህቶቻችን ለዚህ ባህል ተጋልጠው የዘመናዊነታቸው መለኪያ እያደረጉት ነው ብልህ ራስህን ይዘህ ኡ! ኡ! ትል ይሆናል። ዛሬ የ50ና የ60 ዓመት ሃብታም ሽማግሌዎችና ፈረንጆች የ16ና የ17 ዓመት

ቆንጃጅት ልጆቻችንን በአደባባይ እየያዙ በየምሽት ክለቡ እየዞሩ ሲደሰቱ ስታይ ምን ይሰማሃል? ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ በአሜሪካም ሆነ በሌሎች አገሮች የማይፈቀዱ የብልግና (xxx) ቪዲዮዎች በይፋ በአደባባይ የዕድሜ ገደብ ሳይደረግባቸው ሲሸጡና ሲከራዩ ስታይ ምን ትላለህ?

ገብርዬ! ታዲያ ይህን ሁሉ እነማን እያመጡ የሚያራግፉብን ይመስልሃል? ከእናንተው ጋ የሚመጡት አገሪቷን በ«ስልጣኔ ከፍ ለማድረግ» ቆርጠው የተነሱ የአገሪቷ ልጆች ናቸው!! ዛሬ አገሪቷ ለነፃ ገበያ ክፍት ሆናለች የተባለው ለዚህ ዓይነቱ የርካሽ ባህል ገበያ ብቻ ነው ማለት ይቻላል። አዳዲስ ሆቴሎች፣ የመዝናኛ ቤቶች፣ ውድ የሆኑ የአውሮፓና የአሜሪካ ልብሶች፣ ጫማዎችና ሌሎች የሸቀጥ መደብሮች የሚከፈቱት በማነው ብትለኝ ከወደናንተ ወደዚህ አገር በሚመለሱ የአገር ልጆች ነው። «ሥልጣኔን ለማስፋፋት»፤ «ተቸግሮ ያስተማራቸውን ህዝብ ውለታ ለመመለስ፣ ... » ለአገሬው ህዝብ የስራ መስክ የሚከፍትና አገሪቱን ሊያሻሽል የሚችል ኢንዱስትሪ ሲያቋቁሙ አይታዩም። ሁሉም ዞረው ዞረው እዚሁ ላይ ናቸው። ከሁሉ የሚገርመው ደግሞ ለዚችው ላቋቋሙት ተራና የወጣቱን ትውልድ ጭንቅላት እያጠፋ ላለው የንግድ ድርጅታቸው ሲሉ ለዘረኛው የወያኔ መንግሥት አድረው፣ ለተሾመው ሁሉ እጅ ሲነሱና ሲያሸቃብጡ ስታይ ደምህ ነው የሚፈላው። የንግድ ፍቃድ ስላገኙ ብቻ ስለወያኔ መንግስት ጥሩነት እነሱ ከዚያ መጥተው እኛን እዚህ እሳቱ ላይ ለተጣድነው ሊያስተምሩን ሲዳዱ ስታይ ትስቃለህ ወይስ ታለቅሳለህ?

ወዳጄ ገብርዬ! አሁንም ቢሆን ከወዲያ ከወደናንተ ወደዚህ አገር እየመጡ ለወያኔ እያደሩ ንግድ የሚከፍቱትን «ሆዳሞች» ስነካካ ምናልባት አንዳንድ ወዳጆቼን እንዳላስቀይም እየሰጋሁ ነው። ገብርዬ! እኛ አትምጡ ወይም አገራችሁን አትዩ እንልም፤ ግን የሚበጀውንና ደግ ደጉን ነገር ብቻ አምጡልን ማለታችን ነው። ደግሞ እዚህ ያለው «ሆዳም አድርባይ» ይበቃናል፤ ከዚያ ተጨማሪ አትላኩብን። ዋናው ግን የእነሱ አድርባይነት ጉዳይ የታሪክ አጋጣሚ የፈጠራቸው ጉዶች ሁሉ ትልቁ ዛፍ ሲገነደስ አብረው ይጠፋሉና ብዙም አያሳስበን ይሆናል። ግን በየጊዜው ይዘው የሚገቡትና ወጣት ልጆቻችንን የሚመርዘው ተራና አጉል ባህል ግን በጣም ያሳስበናልና ለዚህም ነው በብዙ አደራ የምለው።

ትዝ ይልህ እንደሆን ወዳጄ ገብርዬ! ደርግ እኮ ወጣቱን ክፍል በት/ቤት፣ በቀበሌ በሚገኝበት ቦታ ሁሉ መከራውን ያበላው የነበረው ለምን እንደሆነ የተረዳነው እኮ እያደር ነበር። ወጣቱ ካመፀ፣ ወጣቱ አልገዛም እምቢየው ካለ በስልጣኑ ላይ የሚፈጥረው ችግር (ኧረ የፈጠረው ችግር) ታይቶት ያንን ለማኮላሸት ሲል ነበር። ያኔ ደርግ በኃይሉ ተጠቅሞ በጉልበቱ በቁጥጥር ስር ያዋለውን አዋለ፤ ያልዋለለት እንደናንተ ያለው ሸሸ፣ ተሰደደ፣ የቀረው ደግሞ እዛው አገሩ ሆኖ እየሰማ እንዳልሰማ ሆኖ አንገቱን ቀበረ። ደርግም ያለ ተቀናቃኝ 17 ዓመት ገዛ። እነኚህ የአሁኖቹ ደግሞ ዘዴውን በራሳቸው ሲስተም ቀየሩት። ይኸውም የወጣቱን አዕምሮ ለማኮላሸት የሥነ ልቦና ጦርነት ያዙ። ስለአገር ጉዳይ እንዳያስብ፤ የአገር ጉዳይ ሲነሳ «ፖለቲካና ኮረንቲ ከርቀት ነው» ብሎ እንዲያስብና እንዲያውም ስለአገሩ መስማት እንዳይፈልግ፤ ተብለጭልጮ ጊዜያዊ ደስታ በሚሰጥ ነገር ብቻ አዕምሮው እንዲመረዝ፤ አዕምሮው በአጓጉል ቪዲዮዎችና ፊልሞች መዝናናት ብዛት ግድየለሽ እንዲሆንና ጥሩ «ባሪያ» እንዲሆን፤ ጥረት እያደረጉ ነው። ለዚህ መሣሪያ የሆኑትና እየሆኑ ያሉት ደግሞ በየምክንያቱ ከወደናንተ የሚመጡ «ሆዳሞች» ናቸው ብዬ መደምደም እችላለሁ። ወያኔ ቀዳዳውን ያሳያቸዋል እነሱ ያሰፉታል። የሚገርምህ ነገር እዚህ ያለውን አንድ ታዳጊ ወጣት ስለአንድ የአገሩ እውቅ ዘፋኝ ከምትጠይቀው ፈረንጅ አገር ስላለው አቀንቃኝ ብትጠይቀው መቼ እንደተወለደ፣ ምን መብላት እንደሚወድ፣ የድሮ ሚስቱ ማን እንደነበረችና አዲሱ ሚስቱ ማን እንደሆነች ... ምናለፋህ ልክ አብሮ ያደገ የአባቱ ልጅ ይመስል ስለ ሁሉም ነገር ደረቱን ነፍቶ ትንትን አድርጐ ይነግርሃል። ታዲያ ይሄ የበጐ ነገር ምልክት ይመስልሃል? በትምህርታቸውስ ሆነ በአስተዳደጋቸው ላይ ተፅዕኖ የማይኖረው ይመስልሃል? ታዲያ እኔስ ወደ እኛ አገር በሚገቡ ሰዎች ላይ ይህን አታድርጉ ብዬ ትኩረት ባደርግ (ከገገርዎቼ በስተቀር) ለምን ይህን አልክ ብሎ የሚፈርድብኝ ይኖራል?

ወዳጄ ገብርዬ! አሁንም የምደግመው ዋናው ነገር አትምጡብን አላልንም፤ ኑልን! ናፍቃችሁናል። ግን ስትመጡ ስለአገራችንና ስለችግራችን እኛ እንንገራችሁና ስሙን እንጂ ‹‹ለቀባሪው አረዱት›› እንዳይሆን እናንተ አትንገሩን በልልኝ፤ ። ስትመጡ ደግሞ የሚበጅ የሚበጀውን ብቻ ይዛችሁልን ኑ በልልን። እዚህ ያሉት ልጆች «የዛሬ አበባዎች የነገ ፍሬዎች» ወደፊት የአገር መሪ ሊሆኑ የሚችሉ ናቸውና ይህንንም አስቡበት በልልኝ።

መልካም የልደት በዓል ይሁንልን!

ወርቃየሁ ነኝ – ከሸገር

# ሠላምታ ከባህር ማዶ ከገብርዬ – ለወርቃየሁ

ያገር ልጅ ወርቃየሁ!

ተስፋ ሳትቆርጥ ሕዝባችንን ለማስተማር የምትፅፋቸው ደብዳቤዎች ኢትዮጵያ የቆራጥና የአስባሳቢ ታጋዮች ድሀ ሀገር እንዳልሆነች ያሳዩናል። ደብዳቤዎችህ ለትግላችን ዕይታ አቅራቢ መነፅርን መለገስ ብቻ ሳይሆን ለማንነታችን ይባቤና ለክብራችን የኢትዮጵያዊነትን ደማቅ ካባ አልብሰውናል፤ «ነፍጠኞች» እያሉ ለሚያሾፉብን «የድንጋይ ዘመን» ጉጠኞች በአንድነት የብዕር ጥንግ አጉኗቸዋል።

የትግላችን አንዱ መልክ ምንነታችንን አንፀባራቂ የሆኑትን የባህል፣ የኪነትና የቅርሳቅርስ ሐብቶች መጠበቅ ነው። የላሊበላ መስቀል መሰረቅ፣ የብራና መፃሕፍትና ክቡር የታሪክ ዕቃዎች መመዝበር በዘመነ ወያኔ የታዩ ታሪክን ደምሳሽ ክስተቶች ናቸው። ከዚህ በፊት የኢትዮጵያ ክቡር ዕቃ የተመዘበረው በአብዛኛው መልኩ በጦርነት ጊዜ ነበር። ኃይለሥላሴም ሆኑ ደርግ የላሊበላን ክቡር የወርቅ መስቀል አላስበሉም፤ በስግብግቦችና ደንታ ቢሶች የተሰረቀው በወያኔ ጊዜ ነው።

ወንድሜ ወርቃየሁ!

ስለታሪክ ቅርሳቅርሶች፣ ሥፍራዎችና ሕንፃዎች ሳነሳ በደርግ የስልጣን ዋዜማ ወቅት በ1971(እአ) የጐበኘኋት የእንጦጦ ማርያም ደብር ትዝ ትለኛለች። በዚያን ጊዜ በብጣሽ ወረቀትና በእርሳስ የገጠምኩትን ግጥም ዛሬም አንዳንዴ እንጐራጉረዋለሁ።

<u>እንጦጦ ማርያም ያደዋ ገዳም</u>

ከፍንፍኔ በፊት አብባ ... መምህርት ሆና ላዲሳባ
ከእምባቦ ዘማች ወለባ ... ያንድነት ፅላትን ጠርባ
ከዘመነ መሳፍንቱ ቱባ ... የጎብረቀለም ክሮች ስባ
ስንቱን ቱሪስት ያባባ ... የድንቅ መስህብነቷ መባ
ከወሎ ሸዋ ከትግሬ ... ከጐጃም ኪነት አኬባ
ከዋሸራና ከዲማ ... ከዜጋመል አልዩ አምባ
ከወረሒመኑ ዘምባባ ... ከተከዜ ሰፊ ዝግባ
በኮኒፈር ጥድ ታጅባ ... በባህር ዛፍ ተሰብስባ፤
መጥኔ ለሰጉን መስቀሏ ... ለአናት አንደበቶቿ
ስንቱን ጉድ ይሆን ታዝባ ... ልብ ብላ በልቦቿ
በኀብረ–ብሔር አርማዋ ... ሁሉን መተር ዓይኖቿ
በአደዋው እይታዋ ... በመነፅር መስታወቶቿ።
ለሰደንቀዋ ድጋፍ መቀነት ... ስንቱን አበጋዝ ሰጥታ
ላይቀሬ የድል ምሷ ... አእላፍ ጀግኖቿን በልታ
ልትነግስ በጥቁር ልብ ... በድል አዋጅ አፈርሳታ
የጎመዝ የነጭ ፊት ... ሽብሽቢቱ ሳይፈታ
በቅዳሴዋ የፀናች ... በሳሕታት ቆማ ተነስታ።
ደመላሽ እግር ተኪውን ... አሰልፋ በተርታ
አስካሪውን የነጭ ለባሽ ... መነጣጥራ ለያይታ
ነክፉ ቀን ሳትዋከብ ... ለማይጨውም በር ከፍታ
በነፍጥ ደም አስነፍጣ ... በጋሻዋ ታንክ መክታ
ቋሚ እርገት ያረገች ... የማይታመን ድል መትታ
ከእንቁላል ተሸካሚነት ... ሃበሻን ነፃ አውጥታ
አይ እንጦጦ ማርያም ... የትውልድ ሁሉ ትዝታ።

ወዳጄ ወርቃየሁ!

እንጦጦ ማርያም የአንድነት የታሪክ ዕምብርት ማስታወሻ ነች። የጥቁር ሕዝቦች አለኝታ በመሆን ኮሎኒያሊዝምን ድብቅ የመታው የእምዬ ምኒሊክ የፀሎቱና የመፅናኛው ምሽግ ነበረች። አደዋ ጦር ግምባር ከመዝመቱ በፊት በጊዜው የነበሩትን ምሑራንና አርበኞች በመሰብሰብ ዝነኛ አዋጁን ከፀሎትና ምህላ በኋላ እምዬ ምኒሊክ ያረቀቀው በእንጦጦ ማርያም ነበር። ባለግርማ ሞገሱን አንፋሮ አጥልቆ የጠፍር ወንበሩ ላይ ዘናና ደገፍ በማለት የአዋጁን ረቂቅ በሊቀመኳሰቹና በፀሐፌ ትዕዛዙ ረዳትነት በመፃፍ አዋጁን አስነገረ። ለዘለዓለም ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ የሚኖረው የእምዬ ምኒሊክ አዋጅ እንዲህ ይል ነበር።

«እግዚአብሔር በቸርነቱ እስካሁን ጠላትን አጥፍቶ አገር አስፍቶ አኖረኝ እኔም እስካሁን በእግዚአብሔር ቸርነት ገዛሁ፤ ተእንግዲህ ግን ብሞትም ሞት የሁሉ ነውና ለኔ ሞት አላዝንም ደግሞም እግዚአብሔር አሳፍሮኝ አያውቅም እንግዲህም ያሳፍረኛል ብዬ አልጠረጥረውም። አሁንም አገር የሚያጠፋ ኃይማኖት የሚለውጥ ጠላት እግዚአብሔር የወሰነልንን ባህር አልፎ መጥቷል እኔም ያገሬን ከብት ማለቅ የሰውን መድከም አይቼ እስካሁን ዝም ብለው ደግሞ እያለፈ መሬት ይቆፍር ጀመር አሁን ግን በእግዚአብሔር ረዳትነት አገሬን አሳልፌ አልሰጠውም ያገሬ ሰው ካሁን ቀደም የበደልሁህ አይመስለኝም አሁንም ጉልበት ያለህ በጉልበትህ እርዳኝ ጉልበትም የሌለህ ለልጅህ ለምሽትህ ለሃይማኖትህ ስትል በኃዘን እርዳኝ ወስልተህ የቀረህ ግን ኋላ ትጣላኛለህ አልተውሽም ማርያምን ለዚህ አማላጅ የለኝም ዘመቻዬም በጥቅምት ነውና የሸዋ ሰው እስከ ጥቅምት እኩሌታ ድረስ ወረይሉ ከትተህ ላግኝህ።» [ማኀተም፦ ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ምኒሊክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ]።

ወዳጄ ወርቃየሁ፤

<u>በእንጦጦ ማርያም ቅጥር ግቢ ስንቱን</u>

እልፍኝ አስከልካይ፣ ስንቱን ዲፕሎማት፣ ስንቱን መኳንንት፣ ስንቱን የቅኔ ሊቅና ጀግና እጅ ያስነሳው የምኒልክ የግብር ቤት ጠጋኝ አጥቶ ተዛሚል፤ በተዛመመው የፖለቲካ ዘመንና ቅጥ አምባሩ በጠፋበት የጊዜው የጉሳ መስተዳደር እንኳን የምኒሊክ እልፍኝ መዝመምና ኢትዮጵያም ተጣማ በመበላላቷ የሚደንቅ ያለ አይመስለኝም። ሆኖም ግን ታሪክ የማንነት ተምኔት ነውና እንጦጦ ማርያምን መንከባከብ ታሪካዊነቷም እንዳይጠፋ መታገል ለትውስታ አብነትም ብቻ ሳይሆን ለማንነት ረድኤት የሚረዳ የኩሩ ሕብረ—ብሔር ዜጋ ፀጋ ነው። በነ ሰዓሊ (ሰዓሊሁ) አለቃ ሕሩይና በመሪጌታ እምአእላፍ ስዕል በሕብራዊ ቀለም የተሸቆጠቆጠችው እንጦጦ ማርያም ምኒሊክን አስንግሳ፣ ንግሥት ዘውዲቱን በንግሥትነት አስመርቃና የስንቱን የአደዋ ጀግና ካባና ላንቃ አሸልማ ላገርና ለወገን ክብር መሰዋት የቱን ያህል ማዕረግ እንዳለው ያስመሰከረች የጥቁር ሕዝብ የደብር ማዕከል፣ እጅግ ውብና ድንቅ የሕዝቦች ክብር (Dignity) እምብርት ናት።

ምንም እንኳ የውጭ ወራሪ ኃይሎችና መልዕክተኞቻቸው የኢትዮጵያን የታሪክ ቅርሳቅርስ፣ መፃሕፍትና ታቦትም ሳይቀር ቢመዘብሩንም የምኒሊክ አልቤን ወጨፎና ጠፍር አልጋቸው እስካሁን መኖሩ ይደንቀኛል። ጠላትን በአደዋው ጦርነት ድባቅ የመቱት የነራስወሌ ብጡል፣ የነደጃዝማች ባልቻ፣ የእነራስ መኮንንና ራስ ጉበና ልብሶች አሁንም በዚህች አስገራሚ ደብር ይገኛሉ። በተለይም እጅግ የሚገርመው የኢትዮጵያን ታሪክና የምኒሊክንም ዝና ለማጥፋት እስካሁን ኢሕአዴግ ያደረገው ቅስቀሳና ትምህርት መሰል ፕሮፓጋንዳ ምንም ዓይነት ውጤት አለማሳየቱ ነው። በላዔሰቡ የ3ኛው ራይክ የሒትለር መንግሥት በፕሮፓጋንዲስቶቹ በጎቤልስና በነሒምለር አነሳሽነት የአይሁድ ደራሲያንን ታሪካዊና ጠቃሚ መፃሕፍት ቢያቃጥሉም እውነተኛ ታሪክንና ዕውቀትን ሊሰርዙ አልቻሉም። በአውሮጳ፣ በአሜሪካና በካናዳ የሻዕቢያና ወያኔ ገንጣዮችና አስገንጣዮች ከመፅሐፍት ታሪካዊ ገፆችን መቅደድን፣ ለእነርሱ ታሪክ ያላደሉትን መፃሕፍት በመዋስ ከቤተመፃህፍት ማጥፋትን በአንድ ወቅት ስራዬ ብለው እንደተያያዙት ከበርካታ ኢትዮጵያውያን ይሰማል፣ ማረጋገጫ መፈለጉ ሊያስቸግር ይችላል። ነገር ግን ይህ እኩይ ተግባር በአደባባይ እንደማይካሄድ ግልጥ ነው።

ከጥቂት ወራት በፊት የላሊበላን መስቀል መሰረቅ ሰምተን እጅግ አዝነን ነበር። ክቡሩ የላሊበላ መስቀል ይሆን ያህል አመት ምንም ሳይነካው የአክሱምን ሐውልት ወደ ሀገር ለመመለስ ቸብ ረብ በሚባልበት ወቅት መሰረቁ ያለውን ያጋደለ ጉሳዊ የቅርሳ ቅርስ እንክብካቤ ያሳያል። ያሁኑ መሪዎቻችን አልተረዱትም እንጂ የአክሱምን አበሊስክ የገነቡት የኢትዮጵያ ሕዝብ አባቶች ነበሩ። የሁላችንም አርአያ ነበሩ። ሆኖም ግን በጉሳ ሸውራራ ዓይን ማየት ያሁኑን መንግሥት ስለተጠናወቱት መስቀልንም ሲያይ በዘር ይተምናል፤ የታሪክ አሻራዎችንም ሲመረምር የጉሳ ጋኔን ይስባል። የእርዳታና የእንክብካቤ አዋጁንም ሲያስነግርና ደጋፊዎቹንም ሲያሰባስብ በጉሳ ሰንሰለት ያያይዛል።

ወንድሜ ወርቃየሁ!

ለመሆኑ የታሪክ ቅርሳ ቅርስ ለምን ይሰረቃሉ? በምን ሁኔታ? እንዴትስ ይጠፋሉ?

ሀ) <u>በጦርነት ጊዜ</u>፦ በርካታ የሀገር የማንነት ቅርሳ ቅርስ በገፍ የሚመዘበሩት በጉልበት (በኃይል) ጠላት ሀገርን ወርሮ ሲያጠፋ ነው። በመቅደላው ጦርነት ጊዜ አፄ ቴዎድሮስ (መይሳው ካሣ) ሲወድቁ የእንግሊዝ ሰራዊት ክቡር ዕቃዎችን፣ የብራና መፃሕፍትንና መገልገያ መሣሪያዎችን ከንጉሡ መኖሪያ መዝብሯል። በአደዋውም ጦርነት ጊዜ ጣልያን አስካሪዎችን በመመልመል ይህ ነው የማይባል ንብረት ዘርፏል። ትልቁ ዘረፋ የተካሄደው ግን በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወይም በትልቁ የአርበኞች ጦርነት(THE GREAT PATRIOTIC WAR) ጊዜ ነበር። ዛሬ በቫቲካን ብቻ ራሱን የቻለ ሕዳገ—መፃህፍት (Bibliography) ተሰጥቶት በቼሩሊ አይቶፒቺ (Cerulli Aetopicci) ስር ብቻ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የብራና መፃህፍት፣ ድርሳናት፣ ክብረነገስቶች፣ ዳዊቶችና ስዕሎች ተመዝግበዋል። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ አሜሪካና እንግሊዝ የጣልያንን ሐገር በአውሮፕላን ሲደበድቡ በርካታውን የኢትዮጵያ ዕቃ ማይክሮ ፊልም በማስቀረጽ የቫቲካን አስተዳደር ወደ አሜሪካ የካቶሊክ ዩኒቨርስቲዎች አሸሽቷል። ይህንንም የታሪክ አጋጣሚ የሚያመሰግኑ ኢትዮጵያውያን አይጠፉም። በርግጥም የተዘረፈ የታሪክ ቅርስ ሲነሳ ከራሴ ጋር የሚያጨቃጭቁኝ ጉዳዮች አሉ። በርካታ የኢትዮጵያ ዕቃዎች በውጭ ሀገር መኖራቸውን በመደገፍ የአጠባበቅን፣ የሳይንሱንና የእንክብካቤውን ሁኔታም በመጥቀስ የሚከራከሩ የውጭ ምሑራን አሉ። በርግጥም የዝናብ ፍሳሽ ሊያጠፋቸው የሚችሉ የብራና ጽሑፎች አሉ። ቴክኖሎጂ ባላደገበት ሐገር እንክብካቤና እድሳት (Preservation) አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። በዚህ አሳብዐ ግን ዘረፋን ተገቢ ማድረግ ትክክል አይሆንም። ዕቃው ሲበላሽበት መጠገን ያለበት ባለቤቱ ነው። መፍትሔም መሻት ያለበት ያው ሕዝቡ ነው። ሕዝብ የሚወደውን

ይንከባከባል። ሕዝብ የላሊበላን መስቀል ጠብቆ ለብዙ መቶ ዓመታት እንደአይኑ ብሌን ተንከባክቦ ይዞትነበር፤ ወያኔ ግን አስበላው። ከደርግና ከኃይለስላሴ መንግሥት በተለየ ሁኔታ ዛሬ የቅርሳቅርስ ደላላና ማፊያ ክቡር ዕቃዎችን ለመስረቅ በየከተማዎች ይርመሰመሳል።

ለ) «<u>በሰላም ጊዜ</u>» — «ሰላም» ለአፍሪቃ ሀገሮች መታየት ያለበት በተጓዳኝነት (relatives) አቀራረቡ ነው። የወያኔ መንግሥት በኢትዮጵያ ሰላም አለ ቢልም እንኳ አሁንም ሰላም ይንሳውና በጕሳ ቅራኔ የተነሳ ፀጥታ የለም። የታሪክ ዕቃዎች በሰላምም ጊዜ ይመዘበራሉ፤ ከላይ እንደጠቀስኩት በሀገር ቤት ደላላዎችና አቀባባዮች ለውጭ ቱሪስትነን ባዮች ይሸጣሉ። ብዙውን ጊዜ እነዚህ ግኑኝነቶች በትርፍ ላይ የተመሰረቱ ናቸው። የውጭ ደላላዎችና ለዋጮች በዶላር ሀብታቸው በመመካት ፓሊሱን፣ ጠባቂውንና ተንከባካቢውን ይገዙታል፤ ከቻሉም በተራቀቀ የሚሽን ኢምፖሲብል «Mission Impossible» ዘዴ በማይታመን መንገድ ቅርሳቅርስን ይዘርፋሉ። በአንዳንድ ሁኔታም ከአልማዝና ከወርቅ የተሰሩ አክሊሎችን፣ መስቀሎችንና ሌሎች ክቡር ዕቃዎችን በመበታተን ጨፍልቀው ንዑሳን ጌጣጌጦችን በማውጣት ይቸረችሩታል። አንዳንዶችም ለሰው ልጅ ዕደ ጥበብ አክብሮታቸውን አሚጠው ያልሸጡ ግለሰቦች ክቡር ዕቃውን አቆይተው ለቤተወመዘክሮችና ለሌሎች ቅርስ ሰብሳቢ ድርጅቶች በክቡር ዋጋ ይሸጣሉ። እነዚህም ዕቃዎች ለዩኒቨርስቲዎቻቸው፣ ቤተመፃህፍቶቻቸውና ለቤተ ወመዘክሮቻቸው ግርማሞገስንና ታዋቂነትን ይለግሳሉ፤ አባቶቻችንና እናቶቻችን እነዚህን ዕቃዎች በዕውቀታቸው እንዳልሰሩ ሁሉ ፈዘን በቁጭት የበይ ተመልካች በመሆን እናደንቃቸዋለን። ከዚህም ጋር በማያያዝ መግለፅ የምፈልገው አንድ ነጥብ አለ። ምናልባትም ከጥቂት ዓመታት በኋላ የላሊበላ የወርቅ መስቀል በኒውዮርክ ወይም በለንደን ሱዝቢ (Suthby) ጨረታ (Auction) ላይ ይሸጥ ይሆናል። ወይም ተጨፍልቆና ተበታትኖ በጌጣጌጥ መልክ ሳይታወቅ ሊቸረቸር ይችላል። አንጀትን የሚያቃጥለው ይኸው ጉዳይ ነው።

ሐ) <u>በጥላቻና በወገናዊነት የአንዱን ባህል በመናቅ የሚካሄድ የቅርሳ ቅርስ ማጥፋት</u>፦ እንደዚህ ዓይነቱ ጥፋት የጕሳና የኃይማኖት ቅራኔ ባለባቸው ስፍራዎች ታይተዋል። በአማራው ላይ «ነፍጠኞች» በማለት ወያኔ በቀሰቀሰው የጕሳ እሳት የተነሳ በአንዳንድ የደቡብ ክፍላተሀገራት አብያተክርስትያናትም አብረው ወድመዋል፤ ቅርሳቅርስም ተቃጥለዋል። ከዚያም በላይ ሴቶች፣ ሕፃናት፣ አሮጌቶችና ሽማግሌዎች ከገደል አፋፍ ተጥለዋል።

ወዳጄ ወርቃየሁ!

ምናልባትም የአዲስ ዘመንን ጋዜጣ ሳትታዘበው አልቀረህምና የላሊበላ መስቀል ከተሰረቀ በኋላ ጳጳስ ተብዬው ጳውሎስና የወያኔ አስተዳደር የታሪክ ተንከባካቢነታቸውን ለማሳየት በፕሮፓጋንዳው መስክ ሽር ጉድ እያሉ ነው። እንዲያውም በቅርቡ ለአፍሪቃ አብያተክርስቲያናት እነአባ ጳውሎስ ያቀረቡት ትርዒት ይህንኑ ቁልጭ አድርጐ የሚያሳይ ነው።

የቅርሳቅርስ መዘረፍን፣ መጕላላትንና መጥፋትን በውጭና በሀገር ውስጥ ያለው ሕዝባችን እንዴት መቋቋም አለበት?

ሀ) የኢትዮጵያ የቅርሳ ቅርስ ኮሚቴ በዓለም አቀፍ ደረጃ ማቋቋም።

ለ) ውስጥና ውጭ ያሉት የኢትዮጵያ ቅርሳቅርሶች በውል እንዲመዘገቡ ከዓለምአቀፍ ትምህርት ተቋሞችና የባህል ድርጅቶች ጋር ቅንጅት መፍጠር።

ሐ) የምዝገባ መፃህፍትንና ስዕሎችን በየዓመቱ መርምሮ የተቀነሰውንና የተጨመረውን መለየት (Update ማድረግ)

መ) የተሰረቁ፣ የተጨፈለቁ፣ የተሸጡ ወይም እንክብካቤ ያልተደረገላቸው ክቡር ዕቃዎች ካሉ እነዚህን ማጋለጥ።

ሠ) ኮሚቴው ከዩኒስኮ (UNESCO) ጋር ለዚህ ለተቀደሰ ዓላማ ግኑኝነት መፍጠር።

ረ) ለዕድሳትና ለዕንክብካቤ ዘላቂ የገንዘብ ምንጭ መፈለግ።

ሰ) በርካታ የፅሁፍ ቅርሳቅርሶች በማይክሮፊልምና ፎቶግራፍ ተቀርፀው ለመጭው ትውልድ እንዲቀመጡ ማድረግ።

ወንድሜ ወርቃየሁ!

የኢትዮጵያን አኩሪ ታሪክ ስንመረምር የታሪክ ቅርሶቻችንና የፀረ ኮሎኒያሊስት ትግላችን በልቦናችን ልዩ ስፍራን ይይዛሉ። ደጋግሜ እንደገለፅኩት የአደዋው ጦርነት ትልቅ ቦታ ይኖረዋል። የአደዋው ታሪክ ለመጭው ትግላችን ብሩህ እይታን የሚሰጥ በመሆኑ ወያኔ ይህንን የህዝብ ተሳትፎ ከትውልድ አእምሮ ለመሰረዝ ያላደረገው ጥረት የለም። ግን አልተሳካለትም። ታጋይ ፀሐፊዎቻችንና የታሪክ ምሁራን ለምን በአደዋውና በትልቁ የአርበኞች ትግል (THE GREAT PATRIOTIC WAR, ANTI-FASCIST PATRIOTIC RESISTANCE OF WORLD WAR II) ላይ ማተኮር ይገባቸዋል?

ሀ) የአደዋው ጦርነት በትግራይ ክፍለሀገር አደዋ ላይ ከጥቂት ባንዳ ሰላዮች (አስካሪ–ASCARI) በስተቀር የሁሉንም ክፍላተሀገራት ሕዝቦች የትግራይንም ታጋይ ልጆች ጨምሮ

ጣልያንን ድባቅ በመምታቱ፤

ለ) ትግሉ በሰፋት ጠላት ለቃጣበት ወረራ ሕብረ—ብሔር ሠራዊት (Multi-ethnic army) በእምዬ ምኒሊክ አስተባባሪነት በመከተቱ፤

ሐ) ወያኔ የምኒሊክን ታሪክ ለመደምሰስ የሚያደርገው ጥረት ሁሉ በአንጋፋ ታሪክ ተመራማሪዎች ዘንድ ተቀባይነትን በማጣቱ፤ «ነፍጠኛ»፣ «ክልልና» «ቋቁና» የሚሉት የአይዲዎሎጂው መሠረታዊ ዋልታዎቹ ስለተናጉበትና በዚህም ላይ በመጉልበት (Capitalize በማድረግ የኢትዮጵያንና የአፍሪቃን ምሑሮች/ሕዝቦች ማሰባሰቡ ተገቢ በመሆኑ፣

መ) «ነፍጠኛ» በሚል አይዲዎሊጂ ላይ የተመሰረተው ነጣይና የሕዝብን ወገን አውጋዥ/ገዳይ ቅስቀሳው ቦታ በማጣቱና ሐፍረትም ውስጥ ስለገባ በአንድ ወቅት ጊዮርጊስ ቤተክርስትያን አጠገብ የሚገኘውን የምኒሊክ ሐውልት ለመደርመስ ጠባብ ወገኖቹን በማሰባሰብ ያቀደው የልጅ ጨዋታ በሕዝብ ቁጣ ግቡን ስላልመታ፤ በተደጋጋሚም ሐውልቱን በጨርቅ ለመሸፈን ተገዶ ይህም ሳይሳካለት የሐፍረት ማቅ እንደገና በመልበሱ፤

ሠ) በእንግሊዝ የሚገኙ የታሪክ ተመራማሪዎች ከድምፅ አታሚ የጥንት መሣሪያ (Phonograh) የተገኘውን የምኒሊክን ድምፅ በሲዲ (CD) ቀርፀው ለማሰማት አቅደው ነበር የተባለው ያልተረጋገጠ ዜና ወያኔን በማስደንገጡ፣ ቢያንስ በጥቁርነታቸው የጉሳ ምሁራኑ ይህንን ምርምር መግፋት ሲኖርባቸው፤ ይህም የውኃ ሽታ ሆኖ በመቅረቱና ደግሞም ወያኔ ለፀረ—ኮሎኒያሊስት ትግል ያለውን ንቀት በውን በማሳየቱ፤

ረ) የአደዋው ትብብር በፅንሰ ሀሳብ (Conceptually) ደረጃና በታሪክ አርዓያነቱ ለወያኔ አመለካከት ፀረ—አቋም (antithesis) በመሆኑ።

ሰ) ከዚህ በፊት እንደተገለፀው መለስን ከወያኔ ታሪክ መነጠል እንደማይቻል ሁሉ ምኒሊክንም ከኢትዮጵያ ሕዝቦች ፀረ—ኮሎኒያሊስቶች ትግልና ከአደዋው ጦርነት ነጥሎ ማየት በምንም ሁኔታ ባለመቻሉ፤ ስለሆነም የአደዋው ዜናና የታሪክ አሻራነት በታሪካዊነቱ ብቻ የሚታይ ሳይሆን የአስካሪዎች፣ ሰላዮችን፣ ኮሊኒያሊስቶችንና ገንጣዮችን ስነልቦና ቁልጭ አድርጎ በማሳየት ማን ወገን—ማን ጠላት እንደሆነ ለታክቲካዊና ስትራቴጂያዊ ግቦች በሩን ወለል አድርጎ ያሳየናል።

አያ ወርቃየሁ!

አብዛኛውን ጊዜ ወያኔ የጥላቻን ጥንስስ ዘሪ ነውና «ማን ትግሬን ጠላ»፣ «ማን ነው ከመረብ ምላሽ ገፍቶ ኤርትራውያንንም ነፃ ያላወጣው» በሚል ሰበብ ምኒሊክን ሊወነጅል ይደፍራል። የጊዜያችንም ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ሆኑ የጥንቱ ምኒሊክ ትግሬን አልጠሉም። ትግሬን የሚጠላ ራሱ ጉሰኛ ነው። የትግራይ ህዝብ ህዝባችን ነው። የምንታገለው ወያኔ የፈጠረውን የዘር ጥላቻና መርዝ ለማስወገድ ነው። ጉሰኝነትና ጠባብ ብሔረተኝነት ወንጀል ነው። ከአጤ ኃይለስላሴ ጀምሮ በተማረው፣ በምሑሩና በሰርቶአደሩ ትግል በመሳተፍ የዴሞክራሲን መፈክር ያነሳነው ጉሰኝነትን በመደገፍ አይደለም። ይህንን ወያኔ ራሱም አይክደውም። ጉሰኝነትና አንዱን ወገን ማጣጣል ማለት ለእኛ ስድብ ስለሆነ ፍርዱን ለዚህች መፅሔት አንባቢያንና ለታሪክ እንሰጣለን። እነሆ ነገ ታሪክ ይፋረደናል!!

አንጀቴ ወርቃየሁ!

ኧረ ለመሆኑ ምኒሊክ ከመረብ ምላሽ ዘልቆ ለምን ኤርትራን አልያዘም? ዘረኛና ጉሰኛ ስለሆነ ነው ወደፊት ያልገፋው? ይህንን ጥያቄ በመመለስ ረገድ በርካታ ታሪክ ፀሐፊዎች እውነቱን ቢፅፉም በተደራጀ መልክ ከአሁኑ የፖለቲካ ሁኔታ ጋር በማያያዝ ያብራሩት የአደዋውን 100ኛ ዓመት አስመልክቶ ጥናታዊ ኮንፈረንስ ያደረጉት ብሩህ የኢትዮጵያ ህዝብ ምሑራን ናቸው። እነዚህ ምሁራን በአፕሪል 1996 በሚሽጋን ዩኒቨርስቲ ያዘጋጁት ኮንፈረንስ ራሱ ትልቅ የትግል ምዕራፍን በመክፈቱ ወያኔን እጅግ አደናግጦት ነበር። ለጊዜያቸውና ለገንዘባቸው ሳይሳሱ ለሁለት ዓመታት ውጣ ውረዱን ድል መተው ያስተማሩን የፖለቲካ፣ የታሪክ፣ የፍልስፍናና የሕብረተሰብ የሚሽጋኑ ኮንፈረንስ ምሁሮቻችን እንደአደዋው ታጋዮቻችን አኩሪ ትግልን በዘመነ ወያኔ አሳይተውናል፤ ታሪክም አይረሳቸውም። ከእነርሱም ሌላ እንዶክተር ሹመት ሲሻኝ፣ እነመምህር ኤርሳ ኢዳዳ ሌሎችም ዕውቅ ታጋዮቻችንና ምሁሮቻችን «ለምኒሊክ የመረብ ምላሽ ሒስ» አስፈላጊውን መልስ ሰጥተውበታል። ላለፉት፣ አሁን ላሉትና ወደፊትም ለሚፈጠሩት ኢትዮጵያን አፍቃሪ ታጋዮችና ምሑራን (Pan-Ethiopianists) ዘለዓለማዊ ክብር (Eternal Glory) ይድረሳቸው!! ተምራችሁ ላስተማራችሁን፣ ነቅታችሁ ላነቃችሁን አሁንም የዘለዓለም ክብር ይስጣችሁ!! የሚቀረን በአንድ ላይ ትግሉን ማቀናጀት ነው።

እምዬ ምኒሊክ ከጦርነቱ በኋላ ወደፊት ላለመግፋቱ ምክንያቶች ነበሩት። እነዚህም፦

ሀ) <u>የበሽታ፣ የድርቅና የምግብ እጥረት</u> – [Epidemiological and Climatic Reasons] ከአደዋው ጦርነት ሶስትና አምስት ዓመታት በፊት የከብት እልቂት፣ የወረርሽኝ መዛመትና ድርቅ እንደነበረ በርካታ የታሪክ ተመራማሪዎች የመዘገቡት ነው። በአፈታሪክ ደረጃም ሳይቀር የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህሬ አባህላዌ የአፈወርቅ ገብረየሱስን ጦቢያ ሲያስተምሩኝ ይህ ክፉ ቀን ከመግባቱ በፊት የነበረውን የሰብል ምርት ከአማረው ስነፅሁፍ ጋር መግበውኝ ነበር። ከአባታቸው የሰሙትን እውነተኛ ታሪክ እስከሰገሌ ጦርነት ጊዜ የነበረውን አንድም ሳያስቀሩ ነግረውኛል። አባሕላዌ ለጦቢያ መታተም ትልቅ አስተዋፅኦ ካደረጉት የስዋሰው የሀገር ቤት ምሁራን አንዱ ነበሩ፤ ነፍሳቸውን ይማራቸው።

ከምኒሊክ የክተት አዋጅም እንደሚታወቀው ፀረ–ጀርም መድኃኒት (antibiotic) ባልነበረበት ዘመን የሰውና የከብት እልቂት ሁኔታ በፊት ሊደረግ የታቀደውን ዘመቻ አደናቅፈውት ነበር። በጐንደር፣ በጐጃም፣ በሰሜን ሽዋ፣ በትግራይና በወሎ፣ ተስቦ፣ ወረርሽኝ፣ ወባ(ንዳድ)፣ የተቅማጥ በሽታና የሳል በሽታ (TB) ከምንጊዜውም በበለጠ ሁኔታ አይለው ነበር። ከአየር ለውጦች ጋር የዝናብ ማነስና የአንበጣ ጉም መሬቱን አጥለቅልቆት እንደነበር ታሪክ ተመራማሪዎች ይናገራሉ። በቀንድና የጋማ ከብቶችም ላይ ይህ ነው የማይባል አደጋ ወደቀ። አንትራክስ (አባሰንጋ)፣ ሬንዴር ፔስትና ሌሎችም በሽታዎች ተዛመቱ። ይህም ቸነፈር ወይም እልቂት ያስከተለው ጣጣ ፊት ሊታቀድ የታሰበውን ዘመቻ ከማስተጓጐሉም በላይ ከጦርነቱም በኋላ ተፅዕኖ አሳደረ። በዚህ ክፉ ዘመን በምኒሊክ አስተባባሪነት የኢትዮጵያ ሕዝብ ጣልያንን ድል መምታቱ ሁለተኛ ድል ነበር። የተፈጥሮን አስከፊ ሁኔታ ታግሎ ጠላትንም ድል መምታት በእውነቱ ትልቅ ታሪክ ነው። በዚህም ዓይነት ሁኔታ የምኒሊክ ወደፊት መግፋት የባሰ እልቂት ውስጥ መግባት ነበር። ይህም ሆኖ ምኒሊክ በብሩህ ተስፋው የቆሰለውን አስታምሞ፣ የተሰበረውን ጠግኖና የከሳውን አደልቦ ወደፊት ለመግፋት ምኞት ነበረው።

ለ) <u>የጠላት እርዳታ ጦር ከሮም መላክና በኤርትራ አካባቢ ጄኔራል አንቶኒዮ ባልዴሴራ የፈጠረው ጠንካራ ምሽግ</u> (The Reinforcement & Baldisera's Defensive Factors)፦ በኢትዮጵያ ድል የተደናገጠው የጣልያን መንግሥት እንዴት «ከዝንጀሮ የማይሻሉ» ኋላ ቀር ሕዝቦች የነጩን ዘር እንደተዳፈሩት በቁጭትና በንዴት በገነ። በቂ መሣሪያና ስንቅ ከጄኔራል ባልዴሰራ ጋር ላከ። ከአደዋው ጦርነት የተረፈው የጣልያ ጦር፣ አዲሱ ጦርና ከአካባቢው የተመለመሉ ባንዳ ወታደሮች (ASCARI) ጠንካራ ምሽግ በአስመራ አካባቢ መሰረቱ። በተለይም ባልዴሰራ በረኸሙ የሚተኩሱ ዘመናዊ መድፎችና መትረየሶችን ይዞ ስለመጣ ምኒሊክ ገገር ቦታ ላይ ያለውን ጠላት ተከትሎ ቢጋፈጠው ውጤቱ የኢትዮጵያ ሠራዊት እልቂት ነበር።

ሐ) በወቅቱ ከሰሜን ትግራይ በመለስ እስከ ኤርትራ ምንም ዓይነት የፀረ–ባልዴሰራ (ጣልያን) እንቅስቃሴ አልነበረም። በጣልያን ላይ በሽፍትነት ያመፀ የለም። በተለይም ኤርትራ ውስጥ ያለው ሕዝብ ጣልያንን ተቀበለ። አመፅ ቢቀጣጠል ምናልባትም ምንም እንኳ ምኒሊክ ችግር ቢኖርበትም ወደፊት ለመግፋት ይሞክር ነበር።

መ) <u>የቁስለኞች ሁኔታና የጦር መሪዎች መስዋዕትነት</u> (THE CASUALITY FACTOR) ፦ ዘመናዊ ሕክምና ባላደገበት የተጐዳውና የሚሰቃየው ሀገር ወዳድ ሠራዊት ቁጥር ብዙ ነበር። የህዝባችንን ሞራል ለመጠበቅና ህሙማንን ለመንከባከብ ምኒሊክ የወሰደው እርምጃ አባታዊና አኩሪም ነበር። ምኒሊክ ወደፊት ገፍቶ ተጨማሪ ቁስለኛና መስዋዕትነት ቢኖር ለኢትዮጵያውያን ሞራል ገንቢ አልነበረም። በርካታ የበላይና ከፍተኛ የጦር አዝማቾችና መኮንኖችም ተሰውተው ነበር።

ሠ) <u>የዓለም አቀፋዊ ድጋፍና ዲፕሎማሲያዊ ምክንያቶች (The Diplomatic Factor)</u> ፦ ኢትዮጵያ በአደዋው ድል የተነሳ በተናጠል ከጥቁር ህዝቦችና በኃይማኖትም ከሩሲያ በስተቀር ድጋፍ አልነበራትም። የነጮች ክብር በመነካቱ አውሮጳውያን ሁሉ ለጣልያን አዘኑ። ለተከታዩ ጦርነት ድጋፍም ለመስጠት ቃል ገቡ። ይህም በምኒሊክ ታክቲካዊና ስትራቴጂያዊ የጦርነት ንድፍ ላይ ተፅዕኖን አሳደረ። መረብን አቋርጦ አለመዝለቁ ተገቢ ነበር።

የአደዋው ጦርነት ለኢትዮጵያ ህዝቦች አኩሪ ታሪክን ሲለግስ በሌላ አንፃሩ መርዝንም ጠነሰሰ። ኋላ ለተነሳው የቤኔቶ ሞሶሎኒ ፋሽሽታዊ መንግሥት የበቀል መነሳሳትን ቀሰቀሰ። በአውሮጳ የነጮች መሰሪነት ኤርትራን መነሻ በማድረግ ታሪክን ከልሶ የመነጣጠልና አንጐል የማጠብን ርኩስ ሴራ በአውሮጳውያን እርሾነት ጠነሰሰ። የኤርትራን ኢትዮጵያዊነትንና ጥቁርነትን በማስካድ ሁኔታውን አባብሶ የጣልያንን ቅኝ–ገዥነት ለኢትዮጵያ ሰጠ። ኤርትራውያኖችም በቅኝ ተገዢነት ያለን ስለሆነ ከኢትዮጵያ ባርነት ነፃ መውጣት አለብን በማለት ሻቢያን ወለዱ፤ ሻቢያም የትግራይን ህዝብ በመጠቀም አብሮ ከኖረው የኢትዮጵያ ህዝብ ለዘመናት እንዲቀያየምና የጐሳ መርዝን ለዓላማው

በመርጨትና በተማሪዎች እንቅስቃሴ ሰርጐ በመግባት ወያኔ እንዲመሰረት አስተዋፅኦ አደረገ። በመጣሪያ፣ በዲፕሎማሲያዊና በታክቲክ አጐለበተው። እኛ እነለማና ከበደ በየዋህነት ወንድሞቻችን ናቸው ስንላቸው በእኛና በዘመዶቻችን መሪነት ጐንደርን፣ ጐጃምንና ወሎን አቋርጠው በአስመራ መንገድ በአዋሽና በደጀን አድርገው አዲስ አበባ ገቡ። ሻቢያም ወዲያውኑ ተመልሶ ኤርትራን ገነጠለ። ይህ በዚህ እንዳለ አቶ መለስ ዜናዊ «አማራው ባይኖር እዚህ ደረጃ ላይ ደርሰን አዲስ አበባ ባልገባን ነበር» የሚለውን ቃላቸውን ለውጠው «በነፍጠኛ መዋቅር ላይ ማመፅ አለብን» የሚለው ንግግራቸው ደምን አስፈልቶና ቁጣን ቀስቅሶ ንፁህ የኢትዮጵያ ድሀ ዜጐችን አማርኛ ስለተናገሩ ብቻ በደቡብ ክፍላተ ሀገራት ተጨፈጨፉ። የአማራውም ህዝብ ሳይወድ በሁኔታዎች ግዴታ ሕዝቡን ለመመከት በአማራነቱ ድርጅት አቋቁሞ ጭፍጨፋውን ለጊዜውም ቢሆን አቆመው። ተገዶ ግን ለመጀመሪያ ጊዜ በጐሳ ድርጅት መሰረተ አማራጭ አልነበረም። እነአቶ መለስም ይህ «ጥሩ» እንደሆነ አዩ። በቀመሙት የዘር መርዝ አማርኛ ተናጋሪውን በአካይስት ሸር አንገት በማስደፋት ስህተተኛ ነህ አሉት። ብላክሜል (Biack mail) ለሚለው ቃል አማርኛ አቻ አጣሁለት እንጂ ነገሩ ባልሰሩት ስህተት አንገትን ማስደፋት ነበር። የዌብስተር መዝገበ ቃላት ብላክ ሜልን እንዲህ በማለት ያፍታታዋል። ተገቢ በመሰለ መንገድ ስህተተኛ አድርጐ አንገት ማሰበር ወይም አንገት ማስደፋት፣ በዛቻና በማጋለጥ ወይም በማስፈራራት የተፈለገውን ግብ መምታት። [Biack mail- Extortion by intimidation, especially by threats or public exposure]) ወያኔም አንዴ ካፈርኩ አይመልሰኝ በማለት የክልልን አይዲዎሎጂ በሕገመንግሥቱ አፀደቀው። የኮሎኒያሊስት ባዕድ ቋንቋ ስር ሳይሰድ ባልረባ ምክንያት የላቲን ፊደል ለጥቁር የኦሮሞ ሕዝቦች መገልገያ ሆነ። የአውሮጳ ነጭም በመደሰት ተሳለቀብን፤ የአደዋውን ቁጭት በመርዝ ጢስ ብቻም ሳይሆን በሳይኮሎጂና በባህል ተረጭ መርዝ ተወጣው፤ «ሕዝብ የፈለገውን ይመርጣል በዴሞክራሲ» ሲል አሾፈብን። ካለምንም መቀስና የቀዶ ጥገና ምላጭ በጥቁሩ የራስ ቅል የነጭ አንጐል አስገባ፤ ወያኔና ሻቢያም በዚህ የፍራንክንስታይን አንጐል ከባድ ጥፋት በኢትዮጵያ ምድር አደረሱ። አውሮጳውያን ነጮችም በፈጠሩት በመደሰት «ይህ መልካም ነው» አሉ። ግን ለጊዜው ነው። የእነርሱን አንጐል ደግሞ ካለምንም መቀስና ምላጭ ቀዶ አውጥቶ እንደገናም የጥቁር ኢትዮጵያዊን አንጐል የሚያስገባ ኃይል ጊዜ ይወልደዋል፤ ይህ ትውልድ ባያመጣው የነገው ትውልድ ይወልደዋል። እውነት ትመነምናለች እንጂ አትሞትም።

አንጀቴ ወርቃየሁ!

ትግል ጨዋታ አይደለም። ዛሬ ገንብቶ ነገ እንደእምቧይ ካብ መናድ ውኃ ቅዳ ውኃ መልስ ይሆናል። ለብዙዎቻችን የአንድነት ግንባሩ መጠናከር፤ በተለይም ከአትላንታው ስብሰባ በኋላ የታየው የቆራጥነት መንፈስ የተስፋችንን ችግኝ የሚያለመልም ነው። ለዚህ ግብ ጠንቃቃ መሆን እንዳለብን ይሰማኛል። በተለይም በኢትዮጵያ፣ በአውሮጳ፣ በካናዳና በአሜሪካ ስብስቡ ሲዋቀር ከፍተኛ ብልህነት መኖር ይገባዋል። ራቅ ካለ ቦታ በስልክ የሚገናኟችሁን በደንብ ካላወቃችኋቸው ጥንቃቄ አድርጉ። አንድ ምሳሌ ልንገርህ፤ አንድ የወያኔ ሰላይና ሰርጐ ገብ ለአንዳንድ ሀገር ወዳድ በመደወል ከእርሱ በላይ ታጋይና ኢትዮጵያን አፍቃሪ እንደሌለ አድርጐ ያቀርባል። ባለበት ቦታ ግን ግኑኝነቱና ሙሉ ህይወቱ ከሻቢያና ከወያኔ ጋር ነው። እንደዚህ ዓይነት ግለሰቦችን ከአካባቢው ኢትዮጵያዊ ህዝብ ጋር ጠንካራ ግኑኝነት በመፍጠር ማጋለጥ ይቻላል። የወያኔን ሰርጐ ገብነት (Penetration) ጠንቅቀን እስካልታገለን ድረስ አሁን የሚደረገው ትግል አመርቂ ውጤትን ላያስገኝ ይችላል። በአብያተ ክርስትያናት ግንባታም መበርታት አለብን። ስለአብያተክርስትያናት እነሆ ትንሽ ግጥም፦

## «ምዕመናን አንትሙ»

አውጡት ታቦቱን ፥ በፅናፅሉ ሽብሻቤ
አልባሳቱ ይድመቁ ፥ ለመለከት ይባቤ
ዘምሩ ሀሌሉያ ፥ ይሰማ ዜማው ንብባቤ
የማኅሌታይ ያሬድ ድምፅ ፥ የዳዊት ክቡር ደብዳቤ።
ተሳለሙ መስቀሉን ፥ እጣን ሞገሩ ይድራ
ያባቶች የናቶች ማተብ ፥ ቃል ኪዳናቸው ይጣራ
ላገራችን ላልታደልነው ፥ ለተፈጠርነው ለመከራ።
ወረቡ ይውጣ ይሰጣ ፥ ድርሳኑ በልብ ይታቀፍ
ጃንጥላው ይክበብ ፅላቱን ፥ የሙሴ ትዕዛዝ ያስልፍ
ዐሥርቱ ትዕዛዘ ቃላት ፥ በሕሊናችን ላይ ይፃፍ።
ፅናው መረዋው ይንሿሿ ፥ ምንጣፌ–ዘርፉ ይቋጭ
መቋሚያው ቅኔ ያቋቁም ፥ ቅርሱ እውቀትን ያመንጭ
ሕብስቱ ሁሉ ይታደል ፥ ሥጋወ–ደሙ ይረጭ
የኢየሱስ ብርኃዊነት ፥ ታጋይነቱ ይሰራጭ።
ሰይጣን ግራ ይግባውና ፥ በተንኮሉ ይርመጥመጥ
የውሸት ምላሱን ያሹል ፥ መንገጭላውን ያጋጥጥ
አርዮስ ያካይስት ልጅ ፥ በጥል ጥንስስ ይንፈራገጥ።

ቸር ይግጠመን፣
ገብርዬ (አትላንታ–ጆርጂያ)

# ከ አ ን ባ ብ ያ ን



ለውድ አዘጋጅ፣

ሰላምና ጤና ከሁላችሁም ጋር ይሆን ዘንድ የዘወትር ምኞቴ ነው። ከአራት ዓመት በኋላ እንደገና ወደ ውድ መጽሔታችሁ ተሳትፎ ለማድረግ እድል በማግኘቴ በጣም ተደስቻለሁ። እናንተም እንኳን ደህና መጣህ ለማለት ይመስለኛል መጽሔታችሁን በአድራሻዬ ስለላካችሁልኝ በጣም አመሰግናለሁ።

መጽሔታችሁ ከበፊቱ በጣም እየሰፋ፣ እየጠነከረ፣ እያስተማረና እያዝናና እንደሆነ ከላካችሁልኝ መጽሔት ላይ ለመገንዘብ ችያለሁ። በዚሁ እንደምትቀጥሉ ሙሉ ተስፋ አለኝ። እኔም ጊዜና አቅም እስከፈቀደ ድረስ ተሳትፎ ለማድረግ ዝግጁ ነኝ።

ታዬ ጥበቡ– ከአሌክሳንደሪያ

---

## ልብ ብለናል ወይ?

እንዴት ናችሁ? መቼም ሁሌ ነገር ትጐነጉናለህ አትበሉኝና ዛሬም የምለው ወይም የምጠይቀው ነገር አለኝ።

እናም ለመሆኑ ይኼ በየከተማችን በየጊዜው ማንነታቸው ባልታወቁ ሰዎች የሚዘጋጁት የምሽት የሙዚቃ ዝግጅቶች ሁኔታ እናንተንም እንደእኔ አጠራጥሯችኋል ወይ?

ያኔ በፊት ትዝ ይላችሁ እንደሆን እንዲሁ ፓርቲ እየተባለ እየተጨፈረና እየተራገጥን ገንዘባችንን ሰጥተን ኤርትራን በራሳችን ብር ማስወሰዳችን ልብ ያላችሁ ልብ ሳትሉ አትቀሩም። ዛሬስ በበራሪ ወረቀት ብቻ በሚመጡ ጽሁፎች እየተሳብን ገቢው ለማን እንደሆነ ለማናውቀው ነገር ገንዘባችንን አናውጣ እላለሁ፤ ገንዘቡ አይደለም የእኔ ችግር ይዞ የሚመጣው ምንድነው ነው? የአበሻ ሆቴል ወይም ሬስቶራንት ከሆነ ባለቤቱ ይታወቃልና ምንም ችግር የለም። ሌላው ግን የሌላ ነውና ልብ በሉ እላለሁ።

ከጠርጥር–ከአትላንታ

---

እንዴት አንጀት እንደምታርሱ በምን ቃል ልንገራችሁ! አንጀታችሁ ይረስ! እደጉ!

የሚገርመው ነገር የመጽሔታችሁ ብዙው ክፍል ከጥቂቱ በስተቀር አምልጦኝ አያውቅም። ምንም እንኳ የዕድል ነገር ሆኖ ኑሮዬ በየመንገዱ በመሆኑ እንደማንኛውም አባል የላንዳፍታ ቤተሰብ ለመሆን ባልታደልም ለአፍቃሪዎቻችሁ ምስጋና ይግባቸውና ጊዜው ካለፈም ቢሆን አላጣውም።

ለነገሩ ምን ያህል ብተባረኩ ነው ፅሁፉ ሁሉ እንዲህ የሚጥምላችሁ? ምነው ታዲያ ያንን ቆንጆ የልብ ወለድ ታሪክ አጠፋችኋት? አልቆባችሁ ከሆነ በደስታ እኔ ያለኝን ልላክላችሁ ግን ያስከፍላችኋል። ዋጋው ፍቅር ነው! ፍቅራችሁን ከፈሉኝ።

ብዙ አልጨቅጭቃችሁና የእኔም ሙያ ከፅሁፍና ከአርት ብዙ አይርቅም ስራዬ ማንጐራጐር ሆኖ ወደ አውሮፓ ሰፈር እንደው እግር እየጣለኝ አዘወትራለሁ። ታዲያ ላንዳፍታን በU.K. London በሚገኘው የቅዱስ ገብርኤል የሀገር ባህል ሱቅ ጉራ ብዬ የOct/Nov 97 ፅሁፋችሁን ዛሬ አገኘሁት። አልፎብኝም ይሆናል ከደረስኩበት ግን ለስንጠረዥ ጨዋታችሁ መልስም እነሆ እላለሁ። መልካም የገና በዓልና 1998 የሰላም፣ የፍቅር፣ የጤናና የብልፅግና ይሁንላችሁ። በተረፈ በቅርቡ አትላንታ ብቅ ማለቴ ስለማይቀር አትላንታ በግንባር እጅ እነሳለሁ።

ቤዛ ታደሰ ነኝ – ከለንደን

---

ይድረስ በአገሬ ቋንቋ እየተዘጋጀች ለምትቀርበው አዝናኝና ትምህርት ሰጭ ለሆነችው ላንዳፍታ አዘጋጆች! ጤናን ዕድሜ ከፀጋ ጋር እየተመኘሁላችሁ ሰላምታና ምስጋና አቀርባለሁ።

ከሁሉም በላይ ደግሞ በነወርቃየሁና ገብርዬ የደብዳቤ ልውውጥና አልፎ አልፎ ብቅ ለሚለው ለውሂብ ከፍ ያለ ምስጋና አድርሱልኝ። እስኪ ሰሚያችሁ ይብዛ እላለሁ። በአጠቃላይ መልኩ እነዚህ የተባረኩ ወጐች ለአገር ለወገን ለቤተሰብና እንዲሁም ለራሳችን የሚጠቅሙ ከመሆናችው ባሻገር አንብበን ሃሳቡን ተረድተን ያንን ነገር በተግባር ለመተርጐም የምንሻ ስንቶቻችን ነን? ዋናው ማወቅ ያለብን እኛ አደግን ማለት አገራችን አደገች ማለት መሆኑን ነው፡፡ እናም ሁሉን ለማጠቃለል አገርን ከ«ወረርሽኝ በሽታዎች» ለማዳን የሁላችንም ግዴታ ስለሆነ በአንድ ልብ የአገራችንን ነገር

እናስብበት፤ የአገራችን ኢትዮጵያ ታሪክና ሁኔታ ሳንዘነጋ ከዚህ ውጥንቅጥ ኑሮ እናድናት ባይ ነኝ። በቅርቡ ከብዙ ዓመት ጆሮ ዳባ ልበስ ኑሮዬ በኋላ ወደ አገሬ ጉራ ብዬ ያየሁትን ጉድ ለማስረዳት ቃላቱ የለኝም። ብቻ ፈረንጆች እንደሚሉት «ቬሪ ወርስት» ሆኖላችኋል። እናም አንድ እንበል እላለሁ።

ኑር ሁሴን – ከዳላስ

---

ውድ ላንዳፍታዎች!

የታሪክ ግስጋሴ በርካታ ፀረ–ህዝቦችንና ፀረ–ዴሞክራሲያውያንን ባጋለጠበት የ20ኛው ክፍለ ዘመን ማገባደጃ በመወለዳችን እድለኞች ነንና አላፊውን መዝነን መጭውን እንድንገመግም ላበራችሁት መብራት ምስጋና ይድረሳችሁ። ወያኔ እኛን ለመከፋፈል የማይፈነቅለው ድንጋይ እንደሌለ ተረድታችሁ የምታበረክቱት አስተዋጽኦ ቀላል አይደለም። ወያኔ የጐሰኝነት መርዙ ግብ ሳይመታ ሲቀርና ሲረክስበት የእርሱን አመለካከት ሌሎች ላይ ለመለጠፍና ለመከፋፈል በሚያደርገው ጥረት ጐንደሬና ጐጃሜ እያለ የመከፋፈልን ፕሮፓጋንዳ በመርጨት ላይ ነው። በተለይም አንድ ሚድዌስት በሚኖር አባሉ ወደተለያዩ ቦታዎች ስልክ በማስደወል ህዝቡ እርስ በእርሱ እንዲጠራጠር፣ ስደተኛው ኢትዮጵያዊ የራሱን ስጋ በመብላት እንዲጨራረስና እንዲጠላላ ብሎም በወያኔ ላይ እንዳይረባረብና ከትግሉ እንዲዘናጋ ከባድ ፕሮፓጋንዳ በማካሄድ ላይ ነው።

ወያኔ ራሱ ጠብቦ ሌሎችን የጠበቡ በማስመሰል በሲቪክ ማኅበራት፣ በፖለቲካ ድርጅቶችና በአብያተክርስቲያናት መካከል የሚረጨው ፕሮፓጋንዳ ግቡን ባይመታም ሙከራው ቀላል ስላልሆነ ሀገር ወዳዶች፣ የፖለቲካ ድርጅቶችና የሲቪክ ማኅበረሰቦች አጥብቀው እንዲታገሉ ጥሪ መቅረብ አለበት። ጀግናውን ኢትዮጵያዊ አማራ እርስ በርሱ ለመከፋፈል የሚደረገውንም ጥረት ማክሸፍ ጊዜ የሚሰጠው አይደለም። የሚያሳዝንም ነገር አለ። በዚህ የወያኔ ፕሮፓጋንዳ በመወናበድ በጣት የሚቆጠሩ ሀገር ወዳዶችም በሰለባው በመውደቅ ሳያውቁት በአሳፋሪ መንገድ የጠላትን የጐሳ መስመር እያራመዱ ስለሆነ ምርምርና ጥናት እንዲደያርጉ ማበረታታት ያስፈልጋል። የዚህ ዓይነቱ ፕሮፓጋንዳ የተመሰረተውን የጋራ ግምባር ስለሚፈታተን አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ሳያሰልስ መጋፈጥ እንዳለበት ማስገንዘብ ይገባል። እኛም አውቀናል ጉድጓድ ምሰናል እንበል!! እባካችሁ አንዋበርበር!!

ኢትዮጵያዊ ጐንደሬ፣ ሸዌ፣ ጐጃሜና ወሎዬ ጠባብነት ሳያጠቃው ለጠላት አልበገርም በማለት የጋራ ትግሉን በማቀጣጠል ላይ ነው። በአማራነቱ ሳይሆን በኢትዮጵያዊነቱ በመሰብሰቡ ጠላትን እጅግ አስደንግጧል። ስለሆነም ይኸ የጐንደሬ ነው፣ ይኼ የወሎዬ ነው ... ወዘተ የሚል የውሸት ቅስቀሳ በሚካሄድበት ወቅት ነገሩ ከወያኔ የፕሮፓጋንዳ መዋቅር መምጣቱን ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ሊረዳ ይገባል። ይህም ብቻ አይደለም። በቅርቡ በሱዳን አካባቢ የተበተነ ወረቀት ነበር። ይህ በራሪ ወረቀት ጐንደሬዎች ለብቻቸው የተደራጁ በማስመሰል ጠባብነትን በወገን ላይ በማላከክ የታጋዮችን አንገት ለማስደፋት የተተለመ ሸር ነው። ሌላውም በአሜሪካ የታቀደው ሸር ህዝባችንን በአዲሳባና በገጠር ልጅ ለመከፋፈል መርዝ እየተረጨ ስለሆነ ክቡር የኢትዮጵያ አርበኞች ሳያሰልሱ መታገል ይኖርባቸዋል። ላንዳፍታም ቅስቀሳዋን በዚሁ መንገድ መቀጠል አለባት እላለሁ ።

ደመላሽ በቀለ (ሲያትል፣ ዋሽንግተን)

---

ይድረስ ለላንዳፍታ አዘጋጆች!!

እንደምን ከረማችሁልኝ። መቼም አዲስ እንግዳ እንደምትቀበሉ እርግጠኛ ነኝ። መጽሔታችሁን ማንበብ ከጀመርኩ 2 ዓመት አለፈኝ በጣም የምትጥም መጽሔት ናት። በርቱ። ግን አንድ ነገር ልጠይቃችሁ እፈልጋለሁ። እኔ የምላችሁ የአብረኸት (ዕጣዬ) ነገር ምን ላይ ደረሰ? ከክፍል 14 በኋላ አላወጣችሁም መጨረሻውን በጣም ማወቅ ስለምፈልግ እባካችሁ መጨረሻውን ንገሩኝ። በተረፈ ዝግጅታችሁ፣ ሁሉም ነገራችሁ በጣም ቆንጆ ነው። በዚሁ ቀጥሉበት። እግዚያብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን።

ራሔል እንዳለ–ከሳንሆዜ/ካሊፎርኒያ

---

ውድ አንባቢዎቻችን፤
እኛ በጣም ደህና ነን። ጥያቄዎቻችሁን በአግባቡ ለማስተናገድ በተቻለን ሁሉ ደፋ ቀና ብለን መልሶቻችንን በየዝግጅቶቻችን ክፍል ውስጥ ለማካተት ሞክረናል።

ከዝግጅት ክፍሉ

# ከዜና ማኅደር
# እንዲህ ሆነ!

## በስደት ላይ ያሉት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ አሜሪካ ገቡ።

ለረዥም ዓመታት ኬንያ በስደት ላይ የቆዩት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ አሜሪካ ገቡ። ኢህአዴግ ሥልጣን እንደያዘ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያንን በቁጥጥሩ ሥር ለማድረግ ከቤተክርስቲያኒቱ ቀኖና ሕግ ውጭ "ፓትርያርክ በሕይወት እያለ ሌላ ፓትሪያርክ መምረጥ አይቻልም፤" የሚለውን በመጣስ የራሱን ፓትሪያርክ የትግራዩን ተወላጅ አቡነ ጳውሎስን ከአሜሪካ አስመጥቶ ሲኖዶሱ ላይ ተፅዕኖ በማሳደር እንዲመረጡ በማድረጉ ሕጋዊው ፓትሪያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ ወደ ኬኒያ ለመሰደድ መብቃታቸው ይታወቃል። ብፁዕነታቸው በስደት ያለውን ሲኖዶስ በመምራት እስካሁን ድረስ የቆዩ ቢሆንም ብዙ አብያተክርስቲያናትና ምዕመናን ወዳሉበት አሜሪካ መምጣታቸው ለብዙ ምዕመናን ታላቅ ቡራኬና ለእሳቸውም ደህንነት የሚያመች መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

## ኢሰመጉ በኦነግ አባልነት ስም ጉዳት ስለሚደርስባቸው የኦሮሞ ተወላጆች ጉዳይ መግለጫ አወጣ።
## ኢሕአዴግ ኦነግን በአሸባሪነት ለመክሰስ ዘመቻ ከፍቷል።

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) ከኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) ጋር በተያያዘ በአዲስ አበባ ከተማ በፀጥታ ኃይሎች ስለተገደሉት፣ ታፍነው ስለተወሰዱትና ከህግ ውጪ በእስር ላይ ስለሚገኙት የኦሮሞ ተወላጆች ጉዳይ ከነስም ዝርዝራቸው በማውጣት በአስቸኳይ ሕጋዊ መፍትሔ እንዲያገኙ አሳሰበ። ኢሰመጉ ባወጣው መግለጫ በአዲስ አበባ መካኒሳ አካባቢ ያለፍርድ የተገደሉት የሶስቱ የኦሮሞ ተወላጆች ጉዳይ ተጣርቶ ገዳዮች ለፍርድ ይቀርቡ ዘንድ ጠይቋል። እንዲሁም የሌሎችም እስረኞች ጉዳይ በህግ እንዲታይ ኢሰመጉ መንግሥትን ጠይቆ የህግ ልዕልናና ሰብአዊ መብቶች በኢትዮጵያ እንዲከበሩ የሚደግፉ በኢትዮጵያም ሆነ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ግለሰቦች፣ የሰብአዊ መብት ድርጅቶች፣ መንግሥታት፣ የዓለም አቀፍ ድርጅቶችና የሃይማኖት ተቋማት ሁሉ ግፊት እንዲያደርጉ ጠይቋል።

ይህ በዚህ እንዳለ የኢህአዴግ አገዛዝ በአዲስ አበባና በሌሎች ከተሞች የሽብር ድርጊት በመፈጸም ጥፋት ያደረሱ ናቸው ያላቸውን 31 የኦነግ አባላት ላይ ክስ መመስረቱ ሲታወቅ የፌዴራሉ ምክትል አቃቢ ህግ በእነዚህ ሰዎች ላይ ባለፈው ዓመት በመጋቢት ወር በአዲስ አበባ በሚገኙት በትግራይ ሆቴልና በብሉቶፕስ ሬስቶራንት፣ በሐረር በበላይነህ ሆቴል እንዲሁም በተለያዩ የመዝናኛ ቦታዎች ላይ ፈንጂ በመጣል በሰውና በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ማድረሳቸውን በመጥቀስ ክስ የመሰረተ ሲሆን፤ ጥፋተኛ ሆነው ከተገኙ ከ5 እስከ 10 ዓመትና ለሞት የሚያደርስ ቅጣት እንደሚበየንባቸውም አስታውቋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያ «ሬዲዮ ፋና» የተሰኘው የኢህአዴግ የሬዲዮ ጣቢያ ባቀረበው ልዩ ዘገባ አንድ ግዙፍ የኦነግ የሽብር ፈጠራ ቡድን መረብ መበጣጠሱን ሲገልፅ በኢትዮጵያ ውስጥ ለተፈጠሩት ችግሮች ኦነግን በዋና ተጠያቂነት ፈርጅታል። የሬዲዮ ጣቢያው የኦነግ የሽብር ፈጣሪ ድርጊት መሪና አስተባባሪ ያላቸውን ራቢ ሁሴን ዮሴፍ፣ ጋዲሳ አበራና አሸናፊ ብሩ የተባሉ ግለሰቦችን በድምፅ አቅርቦ ማናዘዙም ታውቋል። በኦነግና ህወሀት መካከል ለረጅም ጊዜ ሲካሄድ የቆየው ድርድር መቋረጡ በተገለጠ ጥቂት ቀናት ውስጥ የኦነግን አሸባሪነት አቋም ይፋ ለማውጣት የተቀየሰው ፕሮፓጋንዳ የአሜሪካንን መንግስት ድጋፍ ለማግኘት የታቀደ እንደሆነም ይገመታል። የአረብ ሀገሮች በሱዳን አማካይነት ኦነግን ለማጠናከር ያወጡት እቅድ ኢህአዴግን እረፍት የነሳው መሆኑ ሲታወቅ ኦነግ በቤንሻንጉልና ጉሙዝ አካባቢ በሱዳን መንግስት ደጋፊነት የትጥቅ ትግል እያካሄደ መሆኑ ይታወቃል።

በሌላ በኩል በቅርቡ ጀርመን አገር የተደረገው የኦነግ ስብሰባ ለሁለት መከፈሉ የተገለፀ ሲሆን ዋና ፀሐፊው ገለሳ ዲልቦ በወያኔ መንግስት ላይ የሚደረገውን የትጥቅ ትግል እንዲቀጥል ሲደግፉ፤ ምክትሉ ሌንጮ ለታ ደግሞ በተወሰኑ ሁኔታዎች ኦነግን ሕጋዊ አድርጉ መታገል ይቻላል የሚል አቋም እንደያዘ ይነገራል። እንዲሁም ሌንጮ ለታ «ኦነግ የኦሮሚያን ከኢትዮጵያ ተገንጥሎ ነፃነት የማወጅ አቋሙንና ኦሮሞዎች ኢትዮጵያዊ አይደሉም» የሚለው አቋሙን ያነሳ መሆኑን አስታውቀዋል ይላል የደረሰን ሪፖርት።

## አፈ ጉባኤ ዳዊት ዮሐንስ በለንደን ቅሌት ተከናነቡ

በዲሴምበር ወር መጀመሪያ የኢህአዴግ መንግስት አፈ ቀላጤ የሆኑት ዳዊት ዮሐንስ በእንግሊዝ አገር ጉብኝት ባደረጉበት ወቅት ለንደን በሚገኙ

ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ ተቃውሞ ገጠማቸው።

ተቃውሞው የጀመረው በዲሴምበር 3 በለንደን ኢትዮጵያ ኤምባሲ በተደረገው የኮክቴል ግብዣ ወቅት ሲሆን፤ ተቃዋሚዎቹ ሰልፈኞች በኤምባሲው በር ላይ ተገኝተው ተቃውሟቸውን አሰምተዋል። በዚህ ዕለት ለግብዣው ወደ ኤምባሲ ሲገቡ የታዩት ከ5 ያልበለጡ አውሮጳውያኖችና ከ10 ያልበለጡ የወያኔ ደጋፊዎች መሆናቸው ታውቋል። በማግስቱ ዲሴምበር 4 በእንግሊዝ ትሬድ ዮኒየን ዋና መ/ቤት አቶ ዳዊት ዮሐንስና አጃቢዎቻቸው ጉብኝት ባደረጉበት ወቅት በትሬድ ዩኒየኒስቶች በኢትዮጵያ ስላለው የሰብዓዊ መብት መጣስ ጉዳይ ጥያቄዎች የቀረቡላቸው ቢሆንም «በኢትዮጵያ ምንም የሰብዓዊ መብት መጣስ ችግር የለም» በማለት እንደተለመደው የካዱ ሲሆን ነገር ግን «በኢትዮጵያ የሚገኝ አንድ ሰው ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል የውሸት ደብዳቤ እንደሚፅፍ» እንደሚያውቁ ሲናገሩ በትዝብት ተደምጠዋል።

ዋናው የተቃውሞ ሰልፍ ዲሴምበር 6 ነበር። በዕለቱ የወያኔ ወኪሎች አጠቃላይ ስብሰባ በማለት በኢምፔሪያል ኮሌጅ ስብሰባ ጠሩ። በቦታው 20 የሚሆኑ ተቃዋሚ ሰልፈኞች ከአዳራሹ መግቢያ በር ላይ ሆነው ተቃውሟቸውን በጩኸት ሲያሰሙ አቶ ዳዊትና አጃቢዎቻቸው ከቦታው ደርሰው በማየታቸው አቶ ዳዊት በእጃቸው «ውደሙ» የሚል ምልክት አሳይተዋቸው በንቀት ወደ አዳራሹ ሲገቡ በአዳራሹ ውስጥ የነበሩትና ተዘጋጅተው ይጠብቁ የነበሩ ሌሎች ከ300 በላይ የሚሆኑ ተቃዋሚ ኢትዮጵያውያን ገና ከመግባታቸው የተቃውሞ ጩኸት በማሰማት አዳራሹን በማደባለቃቸው አቶ ዳዊትና አጃቢዎቻቸው ከድንጋጤ የተነሳ ወደ አንድ ጥግ እንደመሸሸ ብለው ይቆማሉ። በአዳራሹ ይሰማ የነበረው ጩኸት እያየለ በመሄዱ የመግቢያ ንግግር እንኳ ለማድረግ አልቻሉም ነበር።

አቶ ዳዊት ከውጭ ያሉትን 20 ሰዎች እንደተቃዋሚ በመቁጠርና ከአዳራሹ የተሰበሰበው ከ300 በላይ የሚጠጋ ሰው ደጋፊዬ ነው በማለት ወደ አዳራሹ ሲገቡ ይህ ሲያጋጥማቸው በመደንገጣቸውና ፖሊሶችም ጩኸቱን ሊያስቆሙ ባለመቻላቸው፤ «ስብሰባ ብላችሁ የጠራችሁዋቸው ሰዎች ሁሉ ራሳቸው የስብሰባው ተቃዋሚ ከሆኑ ስብሰባው መበተን አለበት» በማለት የፖሊስ ኮሚሽነሩ ያልተጀመረውን ስብሰባ በዚሁ ሁኔታ እንዲቆም አድርገዋል። በዚህ መሃል ይህንን ሁኔታ በቪዲዮ በመቅረፅ ላይ የነበረውን ኢትዮጵያዊ ጋዜጠኛ አንድ የወያኔ ደጋፊ (ምናልባትም የኤምባሲው ሰራተኛ) ጋዜጠኛውን ደብድቦ ቪዲዮውን ከእጁ በመንጠቅ መሬት ላይ ሲጥለው ፖሊሶች ከቦታው ደርሰው እጁን በሰንሰለት አስረው ሲወስዱት፤ የተጐዳውን ጋዜጠኛና ሌላ ሁለት ጉዳት የደረሰባቸው ኢትዮጵያውያን ለህክምና ወደ ሆስፒታል መወሰዳቸውም ታውቋል።

## በአዲሱ የብር ኖቶች ላይ የተፃፈው ቃል አነጋጋሪ ሆኗል። ኤርትራ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ለማድቀቅ በኮንትሮባንድ መሰማራቱን እንደአማራጭ ይዛለች።

ካለፈው ህዳር ወር ጀምሮ በይፋ ስራ ላይ የዋለው የአዲሱ ብር ኖቶች ለውጥ ጉዳይ የኢትዮጵያን ህዝብ ብዙ እያነጋገረ ሲሆን አነጋጋሪ ያደረገው ዋናው ነጥብ አንዱ አዲስ በታተሙት የብር ኖቶች ላይ በልዩ ዲዛይን በአማርኛ «የሀሰት»፣ በእንግሊዝኛ ደግሞ «VOID» የተሰኙ ቃላት መስፈራቸው ነው። በብር ኖቶቹ ላይ የተጻፉት እነዚህ ቃላት በየትኛውም አገር ታይቶ የማይታወቅ በመሆኑ በፋይናንስ ሙያ የጠለቀ ሙያ ያላቸውን በሳሎች እንኳ ግራ አጋብቷል። የብሔራዊ ባንክ በብር ኖቶቹ ላይ እነዚህ ቃላት ለመጻፋቸው ምክንያት ያደረገው የሀሰት ብር የሚያዘጋጁ ግለሰቦች በሚያባዙበት ወቅት «ሀሰት» እና «VOID» ጐልተው ስለሚታዩ ለመከላከል እንደሆነ ማብራሪያ ቢሰጥም የህዝቡ ጥያቄ ግን መንግስት ሌላ የመከላከያ ምልክት መጠቀም ሲችል ለምን እነዚህን ቃላት መረጠ? የሚል ነው። በዚህ ዋና ነጥብ ላይ ህዝቡ መልስ ሳያገኝ የአሮጌው የብር ኖት በአዲሱ ተቀይሮ ስራ ላይ ውሏል።

ከዚሁ የብር ለውጥ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የኢትዮጵያና የኤርትራ የንግድ ልውውጥ የአገልግሎት ክፍያ ተቀባይነት ባለው የውጭ ምንዛሪ (በአሜሪካ ዶላርና በሌሎች ከባድ ከረንሲዎች) መሆን አለበት ከተባለ ወዲህ የኤርትራ መንግስት በሁሉም መስክ ስጋት አድሮበት የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ለማድቀቅ በኮንትሮባንድ ንግድ ላይ እንደሚሰማራ ፍንጭ እየሰጠ ነው። በህዳር ወር አዲስ አበባ ውስጥ በአዲስ አበባ የሚገኙ የኤርትራ ተወላጆችን በመጥራት የኤርትራ ኤምባሲ ባካሄደው ስብሰባ የኢትዮጵያና የኤርትራ የወደፊት የንግድና የአገልግሎት ክፍያ በዶላር እንዲሆን መወሰኑ የኢትዮጵያን ጥቅም ወደመጠበቁ ያደላ ነው ሲሉ በኢትዮጵያ የኤርትራ አምባሳደር የሆኑት ግርማ አስመሮም ፍንጭ የሰጡ ሲሆን፤ የኤርትራ ነጋዴዎች በተቻላቸው ሁሉ በኮንትሮባንድ ንግድ ላይ እንዲሰማሩ በዕለቱ ለነበሩት ነጋዴዎች ቅስቀሳ አካሂደዋል። ቀደም ሲልም የኤርትራ ባንክ ገዢ አቶ ተክሌ በየነ ከሪፖርተር መጽሔት ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ «ገደብ ከበዛ ኮንትሮባንድ ሊስፋፋ ይችላል። ይህን ደግሞ ለመቆጣጠር ያዳግታል፤ ጉዳዩ በኤርትራ በኩል ችግር አይፈጥርም» ማለታቸው ይታወቃል።

ይህ በኢትዮጵያና በኤርትራ ላይ የሚኖረው የንግድ ልውውጥና የአገልግሎት ክፍያ በዶላር በመሆኑ ምክንያት የኤርትራ መንግስት ቅሬታውን ለማሳየት በአሰብ ወደብ ላይ የታሪፍና የኪራይ ክፍያ ከእጥፍ በላይ መጨመሩን ሲያስታውቅ፤ በአሰብ ከተማ ነዋሪ

የሆኑ ኢትዮጵያውያን በሞት ሲለዩ ለቀብራቸው 200 ብር ግምት ያለው ናቅፋ እንዲከፍሉም መመሪያ ማውጣቱ ታውቋል።

በኢትዮጵያም ከኤርትራ ጋር ለሚደረግ የንግድ ልውውጥና ለጉዞ አስፈላጊ የሆኑ የውጭ ምንዛሪ አገልግሎት የሚሰጥባቸውን ከተሞችና ቢሮዎች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያስታወቀ ሲሆን የኢትዮጵያ መንግስትም በቅርቡ በኢትዮጵያ የሚኖሩ ኤርትራውያን ንብረታቸው እንዲመዘገብ የሚያስችል መመሪያ እንደሚያወጣ ይጠበቃል።

ይህ በዚህ እንዳለ በሁለቱ አገሮች ለሚኖረው ግኑኝነት በይበልጥ መሻከር ወይም መለዘብ በቅርቡ ኢህአዴግ/ህወሀት በሚያደርገው ኮንፈረንስ ላይ እንደሚወሰን ይጠበቃል።

## የኢትዮጵያ የተወካዮች ምክር ቤት በኒውዮርክ ቤት እንዲገዛ ያሳለፈው ውሳኔ ተወገዘ።

## የኢትዮጵያ ህዝብ ችግር ተመልካች አጣ።

7 ሚሊዮን የሚደርስ ህዝብ በረሃብ፣ በበሽታ፣ በጉርፍና በልዩ ልዩ ችግሮች እየተሰቃየ ባለበት ወቅት የኢትዮጵያ የተወካዮች ምክር ቤት በኒውዮርክ አንድ የመኖሪያ ቤት ለመግዛት 24 ሚሊዮን ብር ለማውጣት መወሰኑን የፖለቲካ ኃይሎችና ታዛቢዎች አወገዙ።

የአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት ልሳን የሆነው «አማራጭ» የተሰኘው ጋዜጣ የተወካዮች ምክር ቤት ጥቅምት 20 ቀን ባካሄደው 4ኛ መደበኛ ስብሰባ በተባበሩት መንግስታት የኢትዮጵያ ቋሚ ተጠሪ ለሆነው ግለሰብ መኖሪያ ቤትና ዕቃ መግዣ 24,331,638 ብር እንዲፈቀድ ሲወሰን፤ አንገብጋቢ የሆነው የህዝብ በረሃብና በበሽታ ማለቅ ጉዳይ ግን በጉባኤው ላይ ጨርሶ አለመነሳቱ ለህዝብ ችግር ደንታቢስነትን እንደሚያሳይ ጋዜጣው የፖለቲካ ታዛቢዎች ያደረጉትን ገለፃ በማስታከክ ተችቷል።

በኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ ጊዜውን ያልጠበቀ ጉርፍ አዘል ዝናብ በአገሪቱ በአብዛኛው ክፍል ለአጨዳ የተቃረቡ ሰብሎችን ማበላሸቱ ሲታወቅ በምስራቅ ኢትዮጵያ በዚሁ ሳቢያ የዋቢ ሸበሌ ወንዝ በመሙላቱ በአካባቢው የሚገኙ ከተሞች በውሃ ተጥለቅልቀው ይገኛሉ። በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል ብቻ ጉርፍ ያፈናቀለው ህዝብ ቁጥር ከ200 ሺህ በላይ ሆኗል። እንዲሁም ያቢሎ የሚባል ከተማ ሙሉ በሙሉ በጉርፍ በመጥለቅለቁ ማንኛውም ዓይነት የመገናኛ ዘዴ ከመቋረጡም በላይ ቁጥሩ ተለይቶ ያልታወቀ ህዝብ በጉርፉ ተከቦ በከፍተኛ ችግር ላይ ይገኛል፤ በ1989 የበልግና የክረምት ዝናብ በመቀነሱ በሀገሪቱ ረሀብ ሰፍኗል። ይህን የመሳሰለ ግዙፍ ችግር በአገሪቱ ውስጥ ሰፍኖ እያለ ምክር ቤቱ በአንድም አጋጣሚ ያደረገው ውይይት ያለመኖሩ በጣም የሚያስገርምና አሳዛኝ እንደሆነም እነዚሁ የፖለቲካ ታዛቢዎች ይተቻሉ።

ይህ ወቅቱን ያልጠበቀው ዝናብ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በሶማሊያ በኬንያና በሱዳን ከፍተኛ የጉርፍ ችግር እያደረሰ መሆኑ ታውቋል።

## የአዲስ አበባ አስተዳደር ኃላፊዎች በ40 ሚሊዮን ብር ብክነት ቅሌት ተዘፈቁ።

የአዲስ አበባ አስተዳደር ኃላፊዎች ከሐምሌ 1988 እስከ ሐምሌ 1989 ባለው የአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ብቻ ከ40 ሚሊዮን ብር በላይ ህነ የብክነት ቅሌት መዘፈቃቸው መስተዳደሩ ባካሄደው 7ኛ መደበኛ ጉባኤ ላይ የቀረበው የኦዲት ሪፖርት አጋለጠ።

የኦዲቱ ሪፖርት በትክክል እንዳመለከተው የባከነው ገንዘብ 40,699,373 ብር ሲሆን ብክነቱ የተከሰተው ጥሬ ገንዘብና ንብረት በማጉደል ገንዘብ አገልግሎት ላይ ሳይውል በወጪ በመመዝገብና በመሳሰሉት መሆኑን ጠቅሷል። ይሁን እንጂ የብክነቱ ዜና በመንግስት መገናኛ ዘዴዎች ከተገለጠ ከ4 ቀን በኋላ ብክነቱ ያንን ያህል እንደማይደርስ ለማስተባበል ጥረት ቢደረግም አያሌ ውስጥ አዋቂ ምንጮች መስተዳደሩ ከ40 ሚሊዮን ብር በብዙ እጅ በበለጠ ንቅዘትና ብክነት ሊዘፈቅ እንደሚችል ያረጋግጣሉ።

## የጣሊያን ፕሬዚዳንት ኢትዮጵያን ጐበኙ።

ከኢጣሊያ ወረራ ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ የጣልያን መሪ ለጉብኝት ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ ፕሬዚዳንት ኦስካር ሉጂ አልፋሮ የመጀመሪያው ሲሆኑ ጥሪ የተደረገላቸው በፕሬዚዳንት ነጋሶ ጊዳዳ መሆኑን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ያወጣው መግለጫ ያመለክታል። ከዚህ በፊት በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የተመራ የመንግስት ልዑካን ቡድን ከጥቂት ወራት በፊት ይፋዊ ጉብኝት ለማድረግ ጣሊያን መሄዱ ሲታወቅ ከጉብኝቱ የተገኘ ውጤት ግን እንደሌለ ይነገራል። የአሁኑ የጣሊያኑ ፕሬዚዳንት ጉብኝት ከኢኮኖሚ ተራድኦ ድጋፍ ጥያቄ ጋር የተገናኘ ሲሆን፤ ቀደም ሲል ኢትዮጵያ በጣልያን ላይ የነበራትን ቅያሜና ጣልያን በኢትዮጵያ ያሳደረችውን ቁስል ያገግማል የሚል ግምት እንዳላቸው የመንግስት ባለስልጣናት ገልፀዋል። የጣሊያን ፕሬዚዳንትም በበኩላቸው ጣልያን የወያኔ መንግስት በሶደሬ እያካሄደ ላለው የሶማሊያን የሰላምና የእርቅ ጉባኤ ሂደት ማካሄጃ 240,000 የአሜሪካ ዶላር ዕርዳታ የሚሰጥ መሆኑን ገልፀዋል። እንዲሁም የጣልያኑ ፕሬዚዳንት ከ60 ዓመት በፊት በጣልያን ወረራ ጊዜ ከአክሱም ተወስዶ ሮም ላይ የተተከለው ሐውልት በቅርቡ እንደሚመለስ ቃል ሲገቡ የኢህአዴግ መንግስት በበኩሉ የሁለቱን አገሮች ትስስር የሚያጠናክር ሌላ ሐውልት ሰርቶ ለመስጠት መወሰኑ የሁለቱ ሀገሮች ግኑኝነት መዳበር በር

እንደሚከፍት ይገምታል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ ዜና አንዳንድ ምንጮች የኢህአዴግ መንግስት ለጣልያኑ ፕሬዚዳንት በጉብኝታቸው ወቅት በኢጣልያ ኤምባሲ ውስጥ ተጠልለው ስለሚገኙት የቀድሞ የደርግ ከፍተኛ ሹማምንት ስለነጀነራል ተስፋዬ ገብረኪዳን ጉዳይ ሳያነሳ እንዳልቀረ ይናገራሉ።

## የአማራ ልማት ማኅበር ጽ/ቤት ተቃጠለ።

የ20 ሚሊዮን ብር ብክነት እንደደረሰበት በታወቀ ጥቂት ቀናት ውስጥ በኢህአዴግ የተቋቋመው የአማራ ልማት ማኅበር (አልማ) ጽ/ቤት የእሳት ቃጠሎ ደርሶበታል። አልማ ባካሄደው ጉባኤ ቀርቦ በነበረው የኦዲት ሪፖርት ላይ ከ20 ሚሊዮን ብር በላይ መባከኑን በተረጋገጠ ከጥቂት ቀናት በኋላ በጽህፈት ቤቱ መዝገብ ቤትና ሂሳብ ክፍል የተነሳው ቃጠሎ ሰነድ ለማጥፋት ሆን ተብሎ የተወጠነ ሴራ እንደሆነ ይገመታል። እንዲሁም ይኸው ማኅበር ባካሄደው ጉባዔ ማኅበሩን እንዲመሩ በድጋሚ የተመረጡት የማህበሩ ሊቀመንበር አቶ ህላዌ ዮሴፍና ምክትላቸው ቃጠሎው በተነሳበት ዕለት ከቀኑ 7 ሰዓት ላይ ከባህር ዳር ወደ አዲስ አበባ የመምጣታቸው ጉዳይ አነጋጋሪ ሆኗል።

በጽ/ቤቱ ላይ የእሳት ቃጠሎው በደረሰበት ሰዓት የባህር ዳር ህዝብ ለማጥፋት ያደረገው ሙከራ በታጣቂዎች መክሸፉ ሲታወቅ፣ የከተማው የእሳት አደጋም ብልሽት ደርሶበታል በሚል ሰበብ አገልግሎት ሳይሰጥ በመቅረቱ፣ የአየር መንገድ እሳት አደጋም ቃጠሎው ካለቀ በኋላ በመድረሱና የዚህ ሁሉ ቅንጅት ሲታሰብ የእሳት ቃጠሎው ሆን ተብሎ የተጠነሰሰና ዶክመንቶችን ለማጥፋት የተደረገ ዘዴ እንደሆነ የአካባቢው ህዝብ ሁሉ በቁጭት የሚናገረው መሆኑ ታውቋል።

## በአማራው ክልል ወደ 1.4 ሚሊዮን ህዝብ ተርቧል ተባለ።

የ1989 የበልግ ዝናብ በመጥፋቱና በመኸር ሰብልም ላይ የዝናብ እጥረት በመከሰቱ በአማራው ክልል 1.4 ሚሊዮን ህዝብ ለረሃብ አደጋ መጋለጡን ከሰሞኑ በአማራው ክልል የተካሄደው የምክር ቤት ጉባኤ አስታወቀ። በአነስተኛ የዝናብ መጠንና በአጭር ጊዜ የሚደርሱ የሰብል ምርቶችን ለመጠቀም በክልሉ ከ15 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የተደረገ ቢሆንም ውጤቱ አመርቂ ሆኖ አልተገኘም።

ገበሬው ድርቁ ባደረሰበት ችግርና የአካባቢው መንግሥት በፈጠረበት የፖለቲካ ጫና ምክንያት የትውልዱ መንደሩን እየለቀቀ መሰደድ በመጀመሩ በወለጋ፣ በናዝሬትና በአዲስ አበባ በየቀኑ የሚፈልሱ ገበሬዎች ይታያሉ። ከረሃቡም በተጨማሪ ካድሬዎች ገበሬውን ሽፍቶች ትቀልባላችሁ፣ ወሬ ታቀብላላችሁ በማለት በሚያደርሱበት የእስር እንግልትና በአዲሱ የመሬት ሽንሽና ምክንያት የትውልድ መንደሩን እንዲለቅ አስገድዶታል። ይህም በእንዲህ እንዳለ የአማራው ክልል በብቸኝነት እመራለሁ የሚለው የብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን) በባህር ዳር ዉስጥ ኮንፈረንስ በማካሄድ ላይ ነው።

ም/ጠቅላይ ሚኒስትርና የመከላከያ ሚኒስትር የነበሩት አቶ ታምራት ላይኔ ወደ ወህኒ ከተጣሉ ጀምሮ ብአዴን አመራር ሰጪ ዋና ፀሐፊ ያልተመደበለት በመሆኑ ሕልውናው እየተዳከመ ለመሄድ ችሏል ተብሏል። የባህርዳሩ ኮንፈረንስ በአማራው ክልል ካለው የፀጥታ ችግሮች በተጨማሪ አመራር ሰጭዎችን እንደሚሰይም ተጠብቋል። ድርጅቱን ለመምራት የኤርትራው ተወላጅ አቶ በረከት ሰምኦን አቶ ተፈራ ዋልዋ ወይም አዲሱ ለገሠ ሊሰየሙ እንደሚችሉም ተገምቶአል።

## ሯጭ አረጋ አብርሃ የዕድሜ ልክ እስራት ተፈረደበት።



አስቴር ኃይሌ የተባለችውን የእህቱን ልጅ በ25 ካሊበር ሽጉጥ ገድሏል በመባል የተከሰሰው በአትላንታ ከተማ ነዋሪ የሆነው የ36 ዓመቱ ሯጭ አረጋ አብርሃ ፍርድ ቤት ቀርቦ የእድሜ ልክ እስራት የተበየነበት መሆኑ ታውቋል። የ28 ዓመቷ አስቴር ኃይሌ ባለፈው ጥር 1989 ግንባሯ ላይ በጥይት ተመትታ መገደሏን መግለፃችን ሲታወስ፤ ከ20 ዓመት በፊት ወደ አሜሪካ የመጣው የትግራይ ልጅ አረጋ አብርሃ የተያዘው በፖሊሶች ኦሃዮ አይሮፕላን ማረፊያ ሲንስናቲ ላይ በአይሮፕላን ለመጓዝ ሲል ነበር። ፖሊሶች አስቴርን የገደለበትን ሽጉጥ ከጓደኛው እንደተዋሰ ያረጋገጡ ሲሆን ከአረጋ ቶዮታ ሲሊካ መኪና ላይም የደም ነጠብጣብና ብዙ ማሪዋና የያዙ ከረጢቶች ማግኘታቸውን ገልፀዋል። አረጋ ቀደም ሲልም ማሪዋና በእጁ ተገኝቶ የተያዘና በ2000 ዶላር ዋስትና የተፈታ መሆኑንም ፖሊሶች በተጨማሪ ገልፀዋል፤ Dec. 7 በዋለው ችሎት 2 የሟች ጓደኞች የምስክርነት ቃላቸውን የሰጡ ሲሆን በአቃቤ ሕጉ ከ140 በላይ የሆኑ መረጃዎች መቅረባቸውን አትላንታ የሚታተመው «አትላንታ ጆርናል ኮኒስቲቱሽን» ጋዜጣ በዲሴምበር 17/97 እትሙ ገልጿል። በፍርዱ አረጋ እስከ

14 ዓመት ድረስ የፍርድ አስተያየት (ፓሮል) ሊጠይቅ የማይችል መሆኑ የተጠቀሰ ቢሆንም የአረጋ ጠበቃ ይግባኝ መጠየቁ ታውቋል።

## አርቲስት ከተማ መኩንን አረፈ።

በባህል ጨዋታ ተወዳጅ ድምፃዊውና የአገር ባህል መሣሪያዎችን ተጫዋች የነበረው ከተማ መኩንን በኖቬምበር መጨረሻ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል። አርቲስት ከተማ መኩንን የ66 ዓመት የዕድሜ ባለፀጋና የ6 ልጆች አባት ሲሆን፤ በአገር ፍቅርና በብሔራዊ ትያትር ቤቶች ለበርካታ አመታት ማልግሉ ታውቋል። የአርቲስቱ ስርዓት ቀብር ብዙ የሙያ ጓደኞቹና የሙዚቃ አፍቃሪዎቹ በተገኙበት በአዲስ አበባ በኡራኤል ቤተክርስቲያን መፈጸሙ ታውቋል።

## የኢትዮጵያን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ የመሬት ይዞታው ህግ መለወጥ አለበት ተባለ።

በኢትዮጵያ የምግብ ዋስትና እንዲረጋገጥ ካስፈለገ በቅድሚያ መሰረታዊ ችግር የሆነው የገጠር መሬት ፖሊሲና መዋቅሩ በሙሉ መለወጥ አለበት ተባለ። የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማኅበር ጥቅምት 20 ቀን 1990 "የምግብ ዋስትናና የገጠር መሬት ፖሊሲ" በሚል ርእስ አዲስ አበባ ውስጥ ባካሄደው ውይይት ላይ በርካታ ጥናታዊ ጽሑፎች ቀርበዋል። በምግብ ዋስትናና በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ላይ በርካታ ጥናቶችን በማካሄድ የካበተ ልምድ ያላቸው አቶ ደሳለኝ ራህመቶ የኢህአዴግ መንግስት ተግባራዊ አድርጌዋለሁ የሚለው የምግብ ዋስትና ስልት የዓለም ባንክ በውጭ ዜጐች አማካይነት ባልተሟላ ደረጃ ለኢትዮጵያ ይበጃታል ብሎ ያዘጋጀው ረቂቅ ዶክመንት መንግስት ሆን ብሎ እንዲሁ ተቀበለው እንጂ በኢትዮጵያውያን ምሁራን ተጠንቶ የቀረበ ያለመሆኑን ገልፀዋል። ግብርናንና ገጠሩን ማዕከል ያደረገው የመንግሥት የ8 ዓመት መርሃ ግብርም የመሬት ይዞታውን ችግር ያልፈታና የገበሬውን ህይወት ያልዳሰሰ ሲሆን፣ በተበጣጠሰ ማሳ ላይ የሚካሄደው የእርሻ ስራ ለህይወት ማቆያ እንጂ ትርፍ ሊያስገኝ እንደማይችል በአጽንኦት አስረድተዋል። አቶ ደሣለኝ ለችግሩ የመፍትሔ ሀሳብ ሲሰጡም ፖሊሲውን እንደገና በደንብ መመርመር እንደሚገባም አሳስበዋል። ኢትዮጵያ በምግብ ራስን በመቻል በኩል የገጠማትን ችግር በቀላሉ ለመፍታትና ዘላቂ መፍትሄ ለመስጠት የገጠሩን መሬት ፖሊሲ ከገበሬው ህይወት ጋር በተዛመደ መልኩ መርምሮ አዲስ የመተካትን አስፈላጊነትም ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ትኩረት ሰጥተውታል።

በዚህ የውይይት መድረክ ላይ ወደ አርባ የሚሆኑ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችና ታዋቂ ግለሰቦች ጥናታዊ ጽሁፎችን በማቅረብ ተሳትፎ በማድረግና በተባለው ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ላይ አስተያየታቸውን በመሰንዘር ፕሮግራሙ ለሀገሪቱ አዲስ ያልሆነና ከ30 ዓመት በፊት የተሞከረ መሆኑን በመጥቀስ በብዙ የአፍሪካ አገሮችም ተሞክሮ ያስገኘው ፋይዳ ያለመኖሩ ተተችቶአል።

## አንጋፋው መምህራን ማሰልጠኛ የፖሊስ ማልጠኛ ሆነ

ለ45 ዓመታት መምህራንን በማሰልጠን የታወቀው የሐረር መምህራን ማሰልጠኛ ወደ ፖሊስ ማሰልጠኛነት ተለወጠ። የሐረር መምህራን ማሰልጠኛ በኢትዮጵያ ውስጥ ከተቋቋሙ መምህራን ማሰልጠኛዎች አንጋፋው ሲሆን ሥራውን ከጀመረ ከ1945 አንስቶ ወደ 11,784 መምህራን አስመርቆ በማውጣት በመማር ማስተማሩ ሂደት ትልቅ ድርሻ ያለው ተቋም ነው።

የማሰልጠኛ ተቋሙን የመዝጋት እርምጃ የወሰደው የሐረሪ ክልላዊ መንግሥት ለፖሊስ ማሰልጠኛ ተቋም የሚሆን ምቹ ቦታ ሳያጣ ይህንን ታሪካዊ መምህራን ማሰልጠኛ ለመዝጋት የወሰደውን እርምጃ በአሳዛኝነቱ ተወግዟል። የሐረሪ ክልላዊ መስተዳድር የመምህራን ተቋሙን ለሁለት ዓመታት ከዘጋው በኋላ በአሁኑ ጊዜ 109 ፖሊሶችን ተቀብሎ ያሰለጥንበታል።

## የኖሮዌጂያን ተራድኦ ድርጅት የኢህአዴግን አገዛዝ አደገኛነት አስታወቀ

የሰብአዊ እርዳታዎችን በመስጠት የታወቀው የኖርዌጅያን ቤተክርስትያን የረድዔት ድርጅት የኢህአዴግ አገዛዝ በኢትዮጵያ ያለውን የህዝብ ችግር ለመቅረፍ በሚደረገው ጥረት እንቅፋት ፈጣሪ ነው ሲል አስታወቀ።

ይህ የእርዳታ ድርጅት በቅርቡ ባሰራጨው መግለጫ በኢትዮጵያ የሚታየው ፖለቲካዊ አለመረጋጋት፣ የሰብአዊ መብት መጣስና የኢኮኖሚው እድገት ማዝገም ህዝቡ ራሱን ለመቻል ለሚያደርገው ጥረት ጋሬጣ መሆኑን አጠንክሮ ገልጿል። መግለጫው የሀገሪቱ ፖለቲካ ሰላማዊ እንዳልሆነና ከጐረቤት ሀገሮች ከሱዳንና ከሱማሊያ ጋርም የሻከረ ግኑኙነት መኖር ዋና ችግር መሆኑንና የሰብአዊ መብትን በተመለከተም መንግስት የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት አባላት ናቸው የሚላቸውን በማሰር በማፈንና በመግረፍ እንዲሁም በመግደል፣ የነፃውን ፕሬስ አባላት በማሰርና በማዋከብ የሚያደርሰውን በደል ሁሉ ማጤኑን የግብረሰናይ ድርጅቱ ገልጦ የኢትዮጵያ ህዝብ ራሱን በራሱ መርዳት እንዲችል እገዛ የሚያደርጉ ድርጅቶችን ማገዝና ማበረታታት ሲገባ በአንፃሩ የሚወሰድባቸው እርምጃ ተገቢ ያለመሆኑንም ገልጿል።

# አልሰሙ እንደሆነ !

**ያልሰሙት ዜና ሊሆን ይችላል በሚል ግምት ትንሽ ዘግየት ያሉ ዜናዎችን አጠር አድርገን የምናቀርብበት አምድ ነው**

◈ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ውጭ አገር ለውድድር የሚሄዱትን አትሌቶች ፓስፖርት በመያዝ፣ በውድድር ወቅት በሽልማት መልክ የሚሰጠውን ገንዘብ በከፊል ወይም በፐርሰንት ለፌዴሬሽኑ መስጠት እንዳለባቸው ያስገድዳል በሚል ክስ ብዙ ኢትዮጵያውያን አትሌቶችን የወከለ (ደራርቱ ቱሉን ይጨምራል) አንድ ሰው ክስ ማቅረቡ ታውቋል። ይህንን ክስ የፌዴሬሽኑ ዋና ፀሐፊ አቶ በዛብህ ወልዴ ከእውነት የራቀ ነው በማለት ተቃውመዋል።

◈ የዓለም ባንክ ባለፈው ኖምበር አጋማሽ ላይ ሁለቱን ወደቦች ማለትም አሰብንና ምፅዋን ለማሻሻል ይረዳ ዘንድ የ30.3 ሚሊዮን ብር ብድር ለኤርትራ መንግስት ለመስጠት መስማማቱ ሲገለፅ የኢጣሊያ መንግስትም የ21 ሚሊዮን ዶላር ብድር ለነዚሁ ወደቦች ግንባታ እየሰጠ መሆኑ ታውቋል።

◈ በኢትዮጵያ ውስጥ እየተካሄደ ያለውን ሕገ ወጥ ግድያና የነፃው ፕሬስ አባላት መታሰር እንዲቆም በእንግሊዝ ሀገር የሚታተመው «ኢትዮ ፋይል» የተሰኘ መጽሔት ለጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ጥያቄ አቀረበ። የኢትዮ ፋይል ዝግጅት ክፍል አባላት እ.ኤ.አ. ጥቅምት 26 ቀን 1997 ለጠቅላይ ሚኒስትር በፃፉት ደብዳቤ የፀጥታ ኃይሎች የተለያዩ ሰዎችን ያለ ፍርድ መግደላቸውንና የነፃ ፕሬስ አባላትን በሀሰት የማሰር ሁኔታ መኖሩን እንዳረጋገጠ ጠቅሶ በቅርቡም በርካታ ጋዜጠኞች መታሰራቸውን የስም ዝርዝራቸውን በማቅረብ አስታውቆ፣ ይህ ሁኔታ ከሰብአዊ መብት ውጪ ከመሆኑም በላይ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብትን ድንጋጌን ይቃረናል ብሏል። ኢትዮጵያውያንን በማይረባና ሀሰተኛ በሆነ ምክንያት በፀጥታ ኀይሎችም መቅትን እንዲያስቆሙ እንጠይቃለን ሲል ኢትዮፋይል ለጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ያቀረበው አቤቱታ ግልባጭ ለኢትዮጵያ የፌዴራል ተወካዮች ምክር ቤት ለፕሬዚዳንት ነጋሶ ጊዳዳ ለእንግሊዝ የውጭ ጉዳይና የጋራ ብልፅግና አገሮች ድርጅት ቢሮ ለአውሮፓ ፓርላማ አዲስ አበባ ለሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል ለሰብአዊ መብት ጉባኤ ለተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብት ኮሚሽንና ሌሎችም ለሚመለከታቸው ሁሉ አቅርቧል።

◈ በኤርትራ ከተሞች፣ ከአስመራ፣ ከምፅዋና ከአሰብ ታፍሰው ለወታደራዊ ግዳጅ ስልጠና ሳዋ የገቡ ትግርኛ የሚናገሩ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ስልጠናውን አንቀበልም በማለት አመፅ ማካሄዳቸው ተገልጿል። ወጣቶቹና ቤተሰቦቻቸው በኤርትራ የሚገኘውን የኢትዮጵያ ኤምባሲና ቆንስላ ጽ/ቤትም ስልጠናው ስለማይመለከተን መፍትሄ ይሰጠን የሚል ጥያቄ ቢያቀርቡም ምንም ምላሽ ሳያገኙ ቢቆዩም ቆራጥ አቋም ይዘው «እኛ የኤርትራ ጉዳይ አያገባንም» በማለታቸው ለጊዜው ከኤርትራውያን ሠልጣኝ ወጣቶች አርቀው ያስቀመጧቸው ሲሆን በግድ የማሰልጠኑ ጉዳይ የሚያስከትለውንም ችግር በመገንዘብ ወጣቶቹን ወደመጡበት የመመለስ አቋም እንደያዙም ታውቋል። የኤርትራ መንግሥት ከሱዳን መንግሥትና ከራሱ ተቃዋሚ ኃይሎች ጋር በሰፊው ለተዘረጋበት ግጭት ከፍተኛ ቁጥር ያለው የሰው ኃይል ያስፈልገዋል ተብሏል። በዚሁም ምክንያት የኤርትራ መንግሥት ለወታደራዊ ግዳጅ የሚሰለጥነውን ህዝብ የእድሜ ገደብ ከ4 ዓመት ወደ 50 ዓመት ከፍ ማድረጉም ታውቋል።

◈ በሐረር ባቢሌ ሚኒራል ውኃ ፋብሪካ ውስጥ ባለፈው ጥቅምት 24 ቀን 2 የቦምብ ፍንዳታዎች ደርሰዋል። ከምሽቱ 2 ሰዓት አካባቢ የፈነዱት ሁለት ፈንጂዎች የፋብሪካውን የውኃ ማስተንፈሻ ግንብ በጣም ጉድተውታል ተብሏል። ፍንዳታዎቹ በፋብሪካው መሃል ደርሰው ቢሆን ኖሮ ሙሉ በሙሉ ያወድሙት እንደነበረ የተገኙ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በቦምቦቹ ፍንዳታ በሰው ላይ የደረሰ ጉዳት አልተመዘገበም። ለፍንዳታዎቹ ተጠያቂ ነኝ የሚል አካል ባይኖርም የአካባቢው መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ግን የእስልምና አክራሪ ቡድኖች ድርጊት ሳይሆን እንደማይቀር ይገምታሉ።

◈ ባለፈው ጥቅምት ወር አስመራ ውስጥ በአንድ ቡና ቤት ላይ የተጣለ ፈንጂ 2 የሻዕቢያ የፀጥታ ሠራተኞችንና የቡና ቤት ባለቤቱን ወዲያውኑ መግደሉን የደረሰን የዜና ምንጭ አረጋግጦአል። መሐል አስመራ ውስጥ የሚገኘው ምሕረት በሚል ስም በሚጠራው ቡና ቤት ላይ አደጋውን ያደረሰው ክፍል እስካሁን ያልታወቀ ሲሆን፣ የውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቃቱን ያደረሱት የእስልምና አክራሪ ቡድኖች ወይም የሻዕቢያን አመራር የሚቃወሙ ራሳቸው የሻዕቢያ አባላት ሊሆኑ እንደሚችሉ ይገምታሉ። የኤርትራ የውስጥና የውጭ ችግር እየተባባሰ በሄደበት በአሁኑ ወቅት የቦምብ አደጋ መድረሱ የፕሬዚዳንት ኢሳያስን አገዛዝ ክፉኛ አስደንብሮአል። በሌላም በኩል በቅርቡ ምፅዋ ውስጥ በመደበኛና በብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት ሠራዊት አባላት መካከል ለሰዓታት የተካሄደው የእርስ በርስ ውጊያ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የሰው ኃይል መሞቱንና መቁሰሉን ተመዝግቧል። ግጭቱን የቀሰቀሰው በጦርነት መሳተፋችን የማይቀርልን ከሆነ ከመደበኛው ሠራዊት እኩል ክፍያ ማግኘት አለብን በማለት የብሔራዊ አገልግሎት ዘማቾች ያነሱት አመፅ ነው ተብሏል።

## የሚነፍስ ወሬ!!

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በራሳቸው ጓዶች በቤታቸው የቁም እስር ላይ ናቸው ይባስ ብሎም ከስልጣን ተወገዱ የሚል ወሬ ከሰማችሁ ውሸት በሉ፤ ይልቅስ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ከፍተኛ የውስጥ ችግር እንዳለበትና በተለይም በጦሩ ውስጥ ጉምጉምታ እንዳለ ይወራልና ይህችን ያዝ አድርጉ።

የኮማንዶር ኃየሉም አርአያ በኤርትራዊው ጀሚል ያሲን መገደል የሚያብከነክነው የህወሀት ጦር ለኮማንደሩ መገደል የመለስና የኢሳያስ እጅ አለበት በሚል ማጉረምረም ከጀመረ ውሎ አድሯል ይላሉ።

ወታደሮቹ በተጨማሪ ለምን ይህን ያህል ግጭትና ጦርነት በዛ? ለምንና ለማን ነው በየቦታው እየሄድን የምንሞተው? በጦሩ ውስጥ ደግሞ በኤርትራውያንና በትግሬ የጦር አባላት መካከል እኩልነት አይታይም? ለምን ኤርትራውያን የበለጠ ይደገፋሉ? ለምንድነው ህዝቡ መንግስትን ይህን ያህል የሚጠላው? የሚሉና የመሳሰሉ ጥያቄዎች በጦሩ አካባቢ አንስቷል የሚል ወሬ ይነፍሳል።

መለስ በቅርቡ ካደረጉት የታንዛኒያ ጉብኝታቸው መልስ ያልተለመደ ከባድ የሴኩሪቲ አጠባበቅ እንደነበራቸው ሲታይ ፍርሃት እንዳለባቸው ይጠቁማል የሚል ወሬ አለ።

መለስ ተቃዋሚዎቻቸውን እንደ መንግስቱ ኃይለማርያም ቀስ በቀስ እያጠፉ ናቸውም ይባላል። በዚህም ምክንያት ተይዘው የት እንደተወሰዱ ያልታወቁ የቀድሞ ተዋጊዎችና ሹማምንት እነ አብርሃም ደስታ፣ አክሊሉ ተጠምቀንና ሳቢርን የመሰሉትን መጥቀስ ይቻላል። ሌላው ሹም የነበረ ብስራት አማረ የተባለው አገር ለቆ መጥፋቱ ይነገራል። የኢህአፓ ወኪሎች ናችሁ በመባል አዲ ኢሮብ በመባል በሚታወቀው ቦታ የሚኖሩ ሳሆዎችና እንደ አክሊሉ ተጠምቀ ያሉ የአክሱም ልጆች ላይ የመለስ ዜናዊ አስተዳደር የሚያደርገውን አፈና በማየት መለስ የአድዋንና የኤርትራን ልጆች ብቻ እንደሚያቀርቡ ሌላው እንደሚያገሉ ያሳማቸዋል።

የኢትዮጵያን ሀብት በመዝረፍ፣ የግል ጥቅምን በማዳበርና በመከበር ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ፤ ባለቤታቸው (የሚጋ ኔት ባለቤት)ና ዘመዶቻቸውና የቅርብ ጓደኞቻቸው ከፉኛ ይታማሉ። በሌላው መልኩ በኢትዮጵያዊነታቸው የሚኮሩና በእነዚህ ከሃዲ የትግራይ ልጆች የሚደረገውን ግፍ በማየት የሚያፍሩ ሀቀኛ የትግራይ ልጆች ይህ ሁኔታ ክፉኛ እያሳሰባቸው በመምጣቱ «አባካችሁ ተሻሻሉ፣ እባካችሁን ግፉን አቁሙና ትክክለኛ ነገር ለህዝቡ በእኩልነት ተግብሩት» እያሉ የሚመክሩ እንደ አባይ ፀሐይ ያሉ አዛውንቶች መኖራቸው ይነገራል።

የቲፒኤልኤፍ ከፍተኛ አመራር አባላት የተባሉት መለስ ዜናዊ፣ ስዬም መስፍን፣ ፃድቃን ገብረ ትንሳኤ፣ ተወልደ ወ/ማርያም፣ ዓለም ሰገድ ገብረአምላክ፣ ገብሩ አስራት፣ ስዬ አብርሃ፣ ስብሃት ነጋ፣ አባይ ፀሃይ፣ ክንፈ ገብረመድህን መሆናቸው ሲታወቅ እነ ሃሰን ሺፋ፣ የማነ ኪዳኔ አራንሺና አዋሎም የተባሉት ደግሞ ቀስ በቀስ ከአመራሩ እየተገፈተሩና እየተተፉ መሆናቸው በገሃድ እየታየ ነው።

ይህ ከፍተኛ አመራር በአሁኑ ወቅት መከፋፈል እየታየበት እንዳለ ሲነገር የመለስ ዜናዊ ክሊኮች ወይም ቡድኖች የሆኑት ተወልደ፣ ዓለም ሰገድና ስዩም መስፍን የሴኩሪቲ ኃላፊውን ሙሉጌታ አስግድን ጨምሮ በአንድ ወገን ሲሆኑ፣ በሌላው ወገን ደግሞ አባይ ፀሀይ፣ ስብሃተ ነጋ፣ ገብሩ አስራትና ስዬ አብርሃ ሌላውን የሴኩሪቱ ኃላፊውን ክንፈ ገብረመድህንንና የመከላከያ ኃላፊውን ፃድቃንን ጨምሮ በሌላው ወገን የመለስ ተቃዋሚዎች በመምሰል የሚታዩ መሆናቸው ይነገራል።

የመለስ ስልጣን እንደሚወራውና እንደሚታየው እያጠረ ይሆን? በቤተመንግስት የመፈንቅለ መንግስት ሙከራስ ተደርጐ ይሆን? ቲፒኤልኤፍ ከውስጥ እየተናጋ ይሆን? ከሚነፍሰው ሹክሹክታ በመነሳት ይህ ልክ ነው፣ ይህ ልክ አይደለም ለማለት ቢያስቸግርም በእርግጥ አንድ ነገር እንዳለና በቲፒኤልኤፍ ሹማምንት መሃል በጥቅምም ይሁን በስልጣን መከፋፈል ያለ ይመስላል። እነዚህና የሚወሩት የውስጥ ሹክሹክታዎች ሁሉ ምን ያህል እውነት ናቸው? በእርግጥ የተባለው መከፋፈል በወያኔ ሹማምንት መሃል አለ ወይስ በእነሱ ላይ የሚደረገውን የተቃውሞ ትግል ለማቀዝቀዝና ለማዳከም ሆን ተብሎ በእነሱ በራሳቸው የሚወራ የፖለቲካ ዲስ ኢንፎርሜሽን ይሆን? ሁሉንም አዙሮ ማየቱ ይበጃል።

# አዳምና ሔዋን

አዳምና ሔዋን የተሰኘው አምዳችን የሚያተኩረው በተቃራኒ ጾታዎች መሃል በሚኖረው ግኑኝነት ላይ ነው። በዚህ አምድ የገጠመኝ ታሪኮችና አስተያየቶች የመሳሰሉት ይቀርባሉ። በእውነተኛ ገጠመኝ ላይ የተመሰረቱ የፍቅር ታሪኮችም እናቀርባለን። በአምዱን የመወያያና የመማሪያ አምድ ለማድረግ እንዲቻል አንባብያን አስተዋጽኦችሁን እንጠይቃለን። በአምዱ ላይ በተለይ ካልተጠቀሰ በስተቀር የሚቀርቡት አስተያየቶችም ሆኑ የገጠመኝ ታሪኮች አንባብያን የሚልኩልን መሆኑ ይታወቅልን።

## «ዕጣዬ»

### ከአብረኸት

«ዕጣዬ» በተሰኘ ርዕስ አብረኸት (የብዕር ስሟ ነው) በስደት ኑሮዋ የገጠማትን በተከታታይ እያቀረበችልን መቆየቷና በመሃል በአንዳንድ ምክንያቶች በመቋረጡ ከብዙ የአምዱ ተከታታዮች የቅሬታ መልዕክቶች ደርሰውናል። ለሁሉም ትልቅ ይቅርታ እየጠየቅን፤ ዛሬ አብረኸት ታሪኳን ካቋመችበት ትቀጥልልናለች። ይህን አሳዛኝ የፍቅርና የስደት ታሪክ ለአንባብያን ስናቀርብ አቀራረቡን እንዲጥም ከማድረግ በቀር በታሪኳ ላይ የጨመርነውም ሆነ የቀነስነው ነገር የለም። እሷ በአሁኑ ወቅት በአሜሪካ አገር በስደት ላይ ናት።

ክፍል 17

«ሆድ ለባሰው ማጭድ አታውሰው» ይላል አማራ ሲተርት። ለምን «አማራ ሲተርት» አልሽ፤ ለምን እንደተለምዶው ይላል «የአገሬ ልጅ» አላልሽም ብላችሁዋል በሆዳችሁ። አይደል? ፋሽኑ ነው ብዬችሁ እርፍ ብልስ። እናም ለረዥም ጊዜ፣ ጥንት ያኔ፣ ማለቴ በዚያ በደጉ ዘመን የነበሩት አገሬ፤ ኢትዮጵያ፤ ... የሚሉ የአገር ፍቅር መግለጫ ቃላቶች ዛሬ ጠበው ወርደው የዘር ፍቅርን መግለጫ በሆኑ ቃላት መተካታቸውን የምታውቁ መስሎኝ ብዬ መልስ ብሰጣችሁስ?

የዚህ ሁሉ ዳር ዳር እንግዲህ ያን የገጠመኝ ታሪኬን ቀደም ሲል ካቆምኩበት በተረት ልጀምርላችሁ ብዬ ነው «ሆድ ለባሰው ማጭድ አታውሰው» ያልኩት። ለምን ይህን አልሽ ብትሉኝ ይገባኛል። ምክንያቱን ቀስ ብላችሁ ትረዳላችሁ አትቸኩሉ እንጂ። ዛሬ እንደድሮው አልምስላችሁ። ብልጥ ሆኛለሁ። በፍቅር ታውሬ የማደርገውና የምሰራው ሁሉ ከቁጥጥሬ ውጭ የሆነ አይምሰላችሁ። ፍቅር አንገላውዶኝ የቁም እንቅልፍ የሆንኩም አይምሰላችሁ። ምኞቻችሁን ፈልጉ።

ቀደም ሲል በነገርኳችሁ ታሪኬ ከአዲስ አበባ እናት አባቴ ቤት ወጥቼ፣ ሰይፉን አግኝቼ፣ ከዚያም ወደ ሱዳን ጠፍቼ፣ እዚያም በስደት ኖሬ በመጨረሻም ቀደም ሲል ወደ አሜሪካ በመጣችው ታናሽ እህቴ ዕርዳታ ወደ አሜሪካ መጥቼ የምወደውን የትዳር ጓደኛዬን ሰይፍዬን እኔ ወዳለሁበት አገር ለማስመጣት የደከምኩት ጥረትና በዚህ ጥረቴ መሃል ሰይፉ አማራ በመሆኑ በእህቴና በሌሎች ጓደኞቿ የደረሰብኝ ተፅዕኖ፤ በእኔና በእህቴ መካከል በተፈጠረው አለመግባባት ከእህቴ ጋር መጣላቴና መለያየቴ፣ ሰይፉንም እኔ ወዳለሁበት አሜሪካ ማስመጣቴ ከዚያም ረጋ ያለ የትዳር ኑሮ ጣዕም ማጣጣም ስንጀምር የምፅዋ በሻዕቢያ መያዝ፣ ቀጥሎም የወያኔ አዲስ አበባ መግባት፣ የኤርትራ መገንጠል በየደረጃው ውጭ አገር ባሉ ኢትዮጵያውያን መካከል መከፋፈል እያመጣ የእያንዳንዱን በርና መስኮት ማንኳኳት ሲጀምር እኔም የዚህ ችግር ሰለባ መሆን መጀመሬን ገልጬላችሁዋለሁ።

ሰይፉና እኔ ቀደም ሲል የነበረንን መተማመንና ፍቅር ብሎም መተሳሰብ ታሪኬን የተከታተላችሁ ሁሉ ታውቃላችሁ። ዛሬ ያ ሁሉ ቀስ በቀስ እየደበዘዘ መምጣቱ አብሮ ብዙ ከመኖርና ከመሰላቸት የመጣ አይምሰላችሁ። በእኔ ና በሰይፉ መካከል እየተፈጠረ የመጣው አለመግባባት መነሻው በብዙ ፍቅረኞች መካከል እንደተፈጠረው «እኔ ያልኩት ልክ! እኔ ያልኩት ብቻ!» ከሚል እልህ የመነጨ ዕለታዊ ተራ ግጭት ሳይሆን ታሪኩ ሌላ ነው።

በኤርትራውያን (ትግርኛ ተናጋሪዎችን ጨምሮ)ና በሌሎች ኢትዮጵያውያን መካከል ክፍፍል እየተፈጠረ፤ ድሮ ጓደኞሞች የነበሩ እየተለያዩና የጐሪጥ እየተያዩ፣ መምጣት ሲጀመር የእያንዳንዱ አበሻ ቤት መንኳኳት ይጀምራል። የአማራ ጓደኛ ያለው ኤርትራዊ በሌሎች ኤርትራውያን ዘንድ ሲወገዝና ሲኮነን ብሎም አድማ ሲመታበት፤ በተመሳሳዩ ኤርትራዊ ጓደኛ ያለው አማራ ደግሞ በሌሎች አማሮች ዘንድ ሲወገዝና ሲኮነን ማየት እየተለመደ መምጣት ይጀምራል። የእኔን ደግሞ ትንሽ ጠንከር የሚያደርገው እህቴ በኤርትራውያኑ መንደር ከፍተኛ ሚና የምትጫወትና በሻቢያ ደጋፊዎች ዘንድ በትልቅ ደረጃ የምትታይ በመሆኗ፤ እሷ፣

ተከታይ ጓደኞቿና ዘመዶቻችን በሌሎች ኢትዮጵያውያን ዘንድ ምን ዓይነት ግጭት ሊኖራቸው እንደሚችል ገምቱ። እኔ ደግሞ ባሌ አማራ በመሆኑ፤ ያደግሁት አዲስ አበባ በመሆኑና በዚህ የመገንጣጠሉ ነገር ላይ ጥሩ ስሜት ስለሌለኝና ይህም በግልፅ ስለሚታወቅ በኤርትራውያን ዘንድ ከፍተኛ ተቃውሞ አትርፎብኝ የጥላቻው ቀስት ከተወረወረብኝ ሰንብቷል፤ በሌላው አበሻ ክፍል ደግሞ በዘሬ ኤርትራዊ በመሆኔ፤ እህቴ አቋዋሚም ሆነ ድምጿ በከፍተኛ ደረጃ የሚሰማ የሻዕቢያ ደጋፊ በመሆኗ በዚህም በኩል ሁለተኛ የጥላቻ ቀስት ተወርውሮብኝ አጣብቂኝ ውስጥ ገብቻለሁ። በሌላው በኩል ደግሞ ሰይፉ እኔ ሚስቱ ኤርትራዊ በመሆኔ እሱም በሌሎች ኢትዮጵያውያን ዘንድ ሁልጊዜ በጥርጣሬና በጥላቻ የሚታይ በመሆኑና በኤርትራውያን ዘንድ ደግሞ አማራ በመሆኑ ስለሚጠላ ... ይህ ሁሉ ተደማምሮ በቤታችን ላይ ሊያሳድር የሚችለው የኑሮ ችግርና ተፅዕኖ እናንተው ገምቱት። በእነዚህና በመሳሰሉት ተፅዕኖዎች ቤት ስንገባ በትንሹ በትልቁ መነጫነጭ፣ «የት ነበርክ? የት ነበርሽ?» እየተባባሉ መጨቃጨቅ ቀስ በቀስ እየጀመረ መጣ።

ወይ ሥራ ወይ አንድ ቦታ ሄጄ እሱ ቤት ቀድሞኝ ከገባ ስመለስ «የት ነበርሽ? ...» እያለ ቀደም ሲል አድርጐ የማያውቀውን ነገር መጠየቅ ከጀመረ በኋላ እኔም እሱ ዘግይቶ ሲገባ ተመሳሳይ ጥያቄ አነሳበትና ጭቅጭቅ እንጀምራለን። ሰይፉ እኔን ጥሎ ሌላ ሴት ጋ ይሄዳል የሚል የቅናት መንፈስ ይዞኝ ሳይሆን እኔ የተቀሰቀስኩበት ነገር ስላለ እሱ አዕምሮዬ ውስጥ ገብቶ ጥርጣሬ እየፈጠረብኝ ነበር። በእህቴና በሌሎቹ ጓደኞቿ የሚነገረኝ እሱ ከሌሎች አማሮች ጋር ተደራጅቶ ትግሬዎችንና ኤርትራውያንን ለመቃወም የሚያደርጉዋቸው ስብሰባዎች እንዳሉዋቸውና ፀረ–ትግሬ እንቅስቃሴ እንደሚያካሂዱና እሱም የዚህ ተካፋይ በመሆኑ ነበር። ቅሬ ታዬ ተቃውሞ ለምን አሰማ ሳይሆን፤ በመጀመሪያ ጀረጃ ለምን ደበቀኝ፣ ሌላው ደግሞ በፖለቲካ ስራ ተሳትፎ ከጀመረ ኑሮአችን ብላሽ ይሆናል ብዬ ስለገመትኩ (ብዙ ጊዜ በእህቴና ጓደኞቿ የሚነገረኝ ይህ ነው)፣ እንደተባለው ፀረ–ትግሬዎች እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳትፎ ከሆነ እኔንስ እንዴት ሊያደርገኝ ነው? የሚል ፍርሃት ስላደረብኝ ነው። እንግዲህ በዚህ ጥርጣሬዬና ፍርሃቴ ላይ የውጭ ቅስቀሳ ሲጨመርበት ኑሮዬ ምን ያህል እንደተበጠበጠ ለመንገር ቃላት ያጥሩኛል።

መከራረፉ ቀስ በቀስ ወደ ጭቅጭቅ እያመራ መሄድ በጀመረበት ሰሞን አንድ ቀን ስራ አመሸሁና እግረ መንገዴን ከአንድ ግሮሰሪ ጐራ ብዬ እቤት ስገባ ሰይፉ ከእኔ ቀድሞ ገብቶ ኖሮ ስልክ ሲያወራ ደረስኩ። ልክ ቤት ገብቼ እሱ ያለበትን ክፍል በር ከፈት ሳደርግ «በል በቃህ ኋላ እደውልልሃለሁ» ብሎ ከመቅፅበት ስልኩን ሲዘጋና ቀና ሲል ዓይን ለዓይን ተፋጠጥን።

«ምነው ወሬአችሁን አቋረጥኩባችሁ እንዴ ድንገት መጥቼ?» አልኩት። እኔ በመምጣቴ የስልኩን ወሬ እንዳቋረጠ ስለተረዳሁ።

«ምን ለማለት ፈልገሽ ነው?» አለኝ

«ያልኩት ግልፅ ነው፤ ምን ትርጉም ያስፈልገዋል?» አልኩት

«የት አመሸሽ ብዬ እንዳልጠይቅ የጠነሰስሽው ዘዴ ነው?» አለኝ

«እኔ የትም አላመሸሁ፤ ያው ከሥራ ነው የምመጣው። ርዕሱን ለመቀየር ባትሞክር ይሻላል ይልቅስ ከማን ጋር ነበር የምታወራው?» አልኩት ስልኩን የዘጋበት ምክንያት ሆድ ሆዴን እየበላው።

መልስ ሳይሰጠኝ ከተቀመጠበት ተነስቶ ወደ ሌላ ክፍል ሊሄድ ሲል ከተል አልኩና ትከሻውን ያዝ አደረግሁት።

«ልቀቂኝ!» ብሎ በመጮህ አመናጭቆኝ ትቶኝ ሲወጣ – ንዴት፣ እልህ፣ ተስፋ መቁረጥ ተረባርበውብኝ ዘልዬ ከወንበሩ ላይ ቁጭ በማለት ጭንቅላቴን ከጉልበቴ ላይ በመድፋት ለቅሶ ጀመርኩ።

ምንም ይሁን ምን ሰይፍዬ እንደዚህ ሆኖብኝ፣ እንደዚህ ድምፁን ከፍ አድርጎ ተናግሮኝ አያውቅም ነበር። ይህን ኃይለ ቃል ያለበት ቁጣ ሲያወርድ መሬት የተደበላለቀብኝ መሰለኝ። በአንድ ጊዜ ዓይኔን የሞላውን እንባ ጠራርጌ ሮጥ ብዬ እሱ ወደገባበት ክፍል ሄድኩ። ክፍሉ ጥግ ካለ የምግብ ጠረጴዛው ካለ ወንበር ላይ ቁጭ ብሎ አንገቱን ጠረጴዛ ላይ ድፍት አድርጓል። ሁኔታውን ሳየው አሳዘነኝ። ዘልዬ እንደገባሁ ወደ እሱ ሄድኩና እተቀመጠበት እጆቼን ዘርግቼ እንደማቀፍ አደረግሁ።

«ምን እየሆን ነን ሰይፍዬ? ምን መጣብን?» አልኩት እንባ በተናነቀው ድምፅ።

መልስ አልሰጠኝም። ፊቱን ከኔ ዘወር አደረገ።

«ንገረኝ እንጂ! ዝም አትበል እባክህ ሰይፍዬ» አልኩት።

ቀና ብሎ አየኝ። ዓይኑ ፍም መስሎ እንባ አዝሏል። እኒያ የሚያባብሉት ዓይኖቹ እንባ ሞልተዋቸው ሳይ ፍረሽ ፍረሽ አለኝ። እቅፍ አድርጌ ዓይኖቹ ላይ ሳምኩት። እሱም አቀፈኝ። ተመስገን።

ተቃቅፈን ትንሽ ከቆየን በኋላ፤ «አብረኸትዬ ትልቅ ችግር እየገጠመን ነው ያለው። ስለዚህ ጠንካሮች እንድንሆን ምንም ነገር እንደባበቅ» አለኝ ዓይን ዓይኔን እያየ።

«እኔ ምን ደብቄህ አውቃለሁ ሰይፍዬ» አልኩት።

«አሁን ስላለው ሁኔታ ምን ይሰማሻል?» አለኝ።

«የትኛው ሁኔታ?» አልኩት

«ብቃ የዚህ የፖለቲካ ጉዳይ፤ የአገር ጉዳይ» አለኝ።

‹‹ሰይፍዬ እኔ ስለፖለቲካ ምንም እንደማይገባኝ ታውቃለህ። ምን ብዬ ልንገርህ?» አልኩት በማስተዛዘን።

«ኢሺ! ልጠይቅሽ ስብሰባ ...፣ ማለቴ እኔ የማላውቀው ስብሰባ የምትሄጂበት አለ?» አለኝ በተጓተተ ድምፅ ፈራ ተባ እያለ።

«የምን ስብሰባ? ሰይፍዬ» አልኩት

‹‹ከኤርትራውያን ጋር ትሰበሰቢያለሽ ወይ?»

«ብነግርህስ ታምነኛለህ?» አልኩት

«እውነቱን ከነገርሺኝ ለምን አላምንሽም?»

«ከዚህ በፊት በእህቴም በኩል ሆነ በብዙ መንገድ ስብሰባ ላይ እንድካፈል፣ ገንዘብም እንዳዋጣ ከድሮ ጀምሮ ይጠይቁኝ እንደነበር ነግሬሃለሁ አይደል?»

«አሁንም እየጠየቁሽ ናቸው ማለት ነው?»

‹‹አዎና! አንተ እንዳትጨነቅ ብዬ አልነግርህም እንጂ አጋጣሚ ባገኙ ቁጥር መጠየቅ ብቻ ሳይሆን ያስፈራሩኛል።» አልኩት።

‹‹እና ግን አንቺ አልሄድሽማ? አትዋሺኝ!» አለኝ ኮስተር ብሎ።

«ምነው አንተ እንዲህ ተጠራጠርከኝ? እምነቴን በደንብ ታውቀው የለ እንዴ?» አልኩ እኔም ኮስተር ብዬ።

‹‹ጥያቄዬን መልሺልኝ፣ ሄደሻል አልሄድሽም?»

«እውነቱን ለመናገር አንድ ቀን አታለው ወስደውኛል። ከዚያ በኋላ አልሄድኩም፣ ዓላማቸውና ሁኔታቸው ደስ ስላላለኝ ቀረሁ።»

«ያለፈው ሶስት ሳምንት እሁድ ዕለት እኔ ሥራ ላይ የነበርኩ ጊዜ ነበር አይደለም?» አለኝ አይኑን አፍጥጦ።

«አዎ!» አልኩት።

«ማለት ያለወትሮው ማኔጀሩ እኔ እሁድ ቀን ሥራ እንድገባ ያዘዘኝ ዕለት?» አለ

‹‹እንዴት ያለ ወትሮው?›› አልኩት የሚለውን ለመስማት በመጓጓት።

«አዎ! ማኔጀሩ ተስፋማርያም የዚያን ቀን ሥራ መግባት እንዳለብኝ አጥብቆ ያዘዘኝ አንደኛ እኛ ጋ የሚሰራው የኤርትራ ልጅ ስብሰባው ላይ እንዲገኝ ነፃ ሊያደርገው፣ በተጨማሪ ደግሞ እኔ ኤርትራዊቷ ባለቤቴ በስብሰባው ላይ ባሏ ሳያውቅ እንድትካፈል ለማድረግ እንዲቻል ያለውን ስልጣን በመጠቀም እኔን በሥራ ማጥመድ ነበረበት። አያ ጅሎ ምንም ሳልጠረጥር በእረፍት ቀኔ እሺ ብዬ ከቤቴ ወጣሁ።» አለ ከራሱ ጋር እንደሚነጋገር አይነት።

ሰይፍዬ የሚሰራው አንድ ፓርኪንግ ሎት (የመኪና ማቆሚያ) ሲሆን የዚህ ቦታ ማኔጀር ተስፋማርያም የሚባል የኤርትራ ልጅ ነው።

«ሰይፉ ምንድነው የምትነግረኝ?» አልኩት ድንጋጤና ፍርሃት በተመላበት ሁኔታ

«እና እንደሰማሁትና እንደተነገረኝ ይህን ዘዴ አንቺ ነሽ አሉ ለተስፋማርያም የነገርሽው።» አለ ፊቱን ቅጭም አድርጐ።

ከመቅፅበት ከዓይኔ እምባ ዱብ ዱብ ሲል ተሰማኝ። የምናገረው ጠፍቶኝ ትንሽ ጊዜ ከቆየሁ በኋላ «እና ታዲያ አንተ አመንካቸው፣ ሰይፍዬ?» አልኩት እንባ እየተናነቀኝ።

«እቤት ደግሞ የአንቺ ሁኔታ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሲቀየር ሳይ ...»

«እእ! አንተ አመንካቸው ...» አልኩት በድጋሚ ዓይኔን አፍጥቼ በቁጣ።

‹‹የማምነውንና የማላምነውን እንኳ መለየት ተስኖኛል። አብረኸት፤ ከጥቂት ጊዜ ወዲህ በኔ ላይ የምታሳዩኝ ሁኔታ ለመሆኑ አንቺን ተሰምቶሻል?» አለኝ ድክም ባለ ድምፅ።

" በእርግጥ ባጋጣሚ ነገሮች ሲገጣጠሙ ሊያሳምኑህ የሚችሉ ሁኔታዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ። አንተስ ሰይፍዬ ያንተን ሁኔታ ልብ ብለህ አይተኸዋል?" አልኩት ዓይን ዓይኑን ትክ ብዬ እያየሁ።

"እንዳልሺው ሊሆን ይችላል፤ ግን እኮ ..."

"በል በቃህ አናንሳው!" አልኩት አቋርጬው።

ይህን ስል ዓላማዬ ግልጽ ሳይሆንላችሁ አልቀረም። ያለፈውን ነገር አስረሳ እያነሱ መለፋለፉ የበለጠ አለመግባባት ይፈጥርና መፍትሔ ለማግኘት ይቸግራል።

"እሺ እንዳልሽው ይሁን?" አለኝና እቅፍ አድርጎ ያዘኝ።

ሰይፉን እንድወደው ከሚያደርጉኝ ባህሪዎቹ አንዱ ይህ ነው። "እሺ! ..." የሚላት ልብን የምታረጋጋው ቃሉ።

ከዚህ ቀን በኋላ በሁሉ ነገር ጥንቃቄ ማድረግ ጀመርኩ። ዋናው ነገር የሰው ወሬ ጨርሶ አለመስማት። የራስን ሕሊና መስማትን የሚያህል ምን ቁም ነገር አለና። ሰይፉም በዚህ ተስማማና ሰላም ተፈጠረ።

ግን ለምን ያህል ጊዜ?

(በሚቀጥለው እትም ይቀጥላል)

## የስነ ፅሑፍ ገፀ በረከት ለወገኖቹ ያበረከተን ኢትዮጵያዊ ሥራዎች ህያው ለማድረግ የቀረበ የጋራ ጥሪ

ውድ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን!

ይህን የጋራ ጥሪ ለማስራጨት ያነሳሳን ዋናው ምክንያት በአሁኑ ሰዓት በየቦታው ላገራቸውና ለወገኖቻቸው መልካም ተግባራትን ሲያከናውኑ የነበሩ ግለሰቦች በአገራችን በደረሰው የሥርዓት መዛባት የተነሳ ጥረታቸው ከብዙሀኑ ፊት እየተሰወረና እየተገለለ እነሱም እየተዘነጉ በመምጣታቸው በተለይም አዲሱ ትውልድ ከእንደነዚህ ካሉ ግለሰቦች ጋር መተዋወቅ ይኖርበታል በሚል መሠረታዊ ግፊት ነው። በዚህም መሠረት የዚህ ጥሪ መልእክት ዝነኛውን ደራሲ ኃይሉ ገብረዮሐንስን የሚመለከት ነው። በዚህ አጋጣሚ የኃይሉ ገ/ዮሐንስን ብርቅዬ የሆኑ ድርሰቶች እንዲሁም ቀደም ባሉት ዓመታት ዝናን ያተረፉ መድበልቶችና መጣጥፎች ለማያውቁ ለማስተዋወቅ ለሚያውቁም እንዲሁ የደራሲውን ድርሣን በረከቶች በትዝታ ፍላፃ እንዲቃኙ ዕድል ለመስጠት በመቻላችን ደስታ ይሰማናል።

ውድ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን!

ደራሲ ኃይሉ ገብረዮሐንስ ላለፉት ሰላሳ አምስት ዓመታት በርከት ያሉ ቁም ነገር ያዘሉ መፃህፍት በተለያዩ ቋንቋዎች ደርሰው ለህዝብ ያበረከቱ ግለሰብ ናቸው። የሰው ልጅ በተፈጥሮው የማየት የመስማት የማሽተት የመዳሰስና የመቅመስ ልዩ ስሜት ተሰጥቶታል። ደራሲ ኃይሉ ገ/ዮሐንስን ከማንኛውም ግለሰብ ልዩ ከሚያደርጋቸው ባህሪያት አንዳንዶቹን መጥቀስ እንወዳለን። ደራሲ ኃይሉ በተፈጥሮአቸው ማየት ብቻ ሳይሆን ያስተውላሉ። መስማት ብቻ ሳይሆን ጉዳዩን ያጤናሉ፣ ያብሰለስላሉ፣ በሚያስደስተውና የምስራች በሆነው ዜና ሁሉ ይፈካሉ። በሚያሳዝነውና ሰቆቃ በተሞላው ትዕይንት ሁሉ ያዝናሉ። ልባቸው በሀዘን ከመሞላቱ የተነሳ ይቆዝማሉ። ማሽተት ብቻ ሳይሆን በመዓዛው ይሸፍታሉ። መዳሰስ ብቻ ሳይሆን ዘልቀው ይፈትሻሉ። መቅመስ ብቻ ሳይሆን ያጣጥማሉ፣ ብሎም የእነዚህን ስሜታዊ ሂደቶች ይዘት በተዋበው የድርሰት ችሎታቸው ቀርፀው ያኖራሉ።

ደራሲ ኃይሉ ለህይወት ያላቸው ፈላስፋዊ አመለካከት በእመርታ በትግል በተሀድሶ በተፃራሪ ኃይላት ፍጭት ላይ የተመሰረተ ነው። በዚህም አመለካከታቸው የተነሳ ይሉኝታና መሞዳሞድ የሰው ልጆችን ነፃ አስተሳሰብ ለመቅበር መከፈኛዎች እንደሆኑ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ያስተምራሉ። ህይወት እሳት ነው ይለኮሳል፣ ይቀጣጠላል፣ ይነዳል፣ ይፈካል ብሎም ይከስማል ብለው የሚያምኑት ደራሲ ኃይሉ በዚህ ኃይልና ኃያልነት በተመላው አመለከካከታቸው የተነሳ «ገሞራው» በሚል የቅፅል ስም ታዋቂ ሆነዋል። በእርግጥም ህይወት ለሰው ልጅም ሆነ የመኖርን ፀጋ ለተካኑ የተፈጥሮ አካላት ህያውነትን የምትሰጥ ልዩ ተፈጥሮ ናት። ህይወት



**ደራሲ ኃይሉ ገብረዮሐንስ**
**(ገሞራው)**

የምታብብ፣ የምታፈራ፣ የምታረጅ፣ የምትረግፍ ብሎም ለመጪው ትውልድ ህያውነትን የምታስተላልፍ ልዩ ተክል ናት። የህያውነት ሳቢያ በመሆኗም መቀየጂያ አልቦ በሆነ የኑሮ ቀለበት ዙሪያ የምትሽከረከር ናት። የገሞራው ድርሳናት ውስጣዊ ይዘትና መልዕክት የሚያተኩረው በዚሁ በህይወትና በህያውነት ዙሪያ ነው።

የፍጡራን ትግልና የፉክክር ፈሊጥ በተለይ የሰውን ልጅ ስሜት ቀይዶ በመያዝ ህይወቱን በቀቢፅ ተስፋ ወጥሮ ፈጠቁን እንደቆጠረ እንዲኖር ይገፋፋዋል። በደስታና በፍስሀ ለመሞሽር አለያም ስሜትን በሚሰብር ሀዘን ለመንገላታት የሚፈረድባት ህይወት ግን በሰላምና በጦርነት መሀል ተሾልካ ለማለፍ የራሷን ዘዴ ትቀይሳለች። ይህን መሳዩን የህይወት ጣጣ ደራሲ ኃይሉ እንደሚከተለው ይገጥሙበታል።

«ችግርና ደዌ ከቶም ድንቁርና በምድር ሲፈነድቅ
የሚሰራ ሞልቶ ስንቱ ተግባር ሳያልቅ
የምድሩ ሳይሞላ አዳሜ ሳይረካ የጠፈሩን ማወቅ
ሮኬት ሲፒትኒክ ሳተላይት ጋጋሪን
እያለ በከንቱ ዝናን ለማዳነቅ
ጀማሪያቸው ሆነህ ይህን በማድረግህ የደንቆሮቹ ሊቅ
ጋኔሉ ጋሊሉ በሞተው ስጋህ ላይ ይብረቅበት መብረቅ»

በረከተ መርገም/1957

ይህን ዓይነቱ የህይወት አመለካከት ገና በወጣትነት ዕድሜያቸው የቀሰሙት ደራሲ ኃይሉ ከዩኒቨርስቲ የተማሪነት ወቅት አንስቶ ደከመኝ ታከተኝ ሳይሉ ከምንምና ከማንም በላይ ለሚወዱዋት ውድ አገራቸውና ለሚያፈቅሩት ወገናቸው የተንሰራፋ መብትና ነፃነት ለማስገኘት ባደረባቸው ልዩ ፍላጐት ይኸው እስከዛሬ ሲብሰለሰሉ፣ ሲቆረቆሩ፣ ሲፅፉ፣ ሲያስተምሩ፣ ሲታገሉ፣ ሲታሰሩና ሲሰደዱ ቆይተዋል።

ደራሲ ኃይሉ እንደማንኛውም ግለሰብ የተደላደለ የግል ኑሮ መስርተው የተረጋጋ ህይወት

ለመምራት እየቻሉ ከግል ምኞት ይልቅ የወገንና የሀገርን ጉዳይ አስቀድመው በመያዝ ደፋ ቀና ይላሉ። ከሰሜን ዋልታ ብዙ ርቃ በምትገኝ አገራችን ውስጥ የሚካሄደውንም ትግል በአንክሮ ከመታዘብ አልፎ ወቅታዊ የሆኑ ብዙ መልዕክቶችን ይፅፋሉ። የዓይን ማረፊያ፣ የልብ ተስፋ፣ የስነልቡና ማርኪያ የስነጥበብና የኪነት መለኪያ የሆኑት የደራሲ ኃይሉ ብርቅዬ ድርሰቶች የኢትዮጵያን ልዩ መልክአ ምድራዊ ውበትና የህዝቡዋን ጀግንነት በረቀቀ በተመጠነና በሰመረ የግጥም ስልትና ቅኝት አዋህደው ያቀርባሉ። በሦስት ፈርጅ ሊፈታ በሚችል ሁኔታ የሚቀርቡት ስንኞች በሳቅና በደስታ፣ በቁጣና በምሬት፣ በእሮሮና በሀዘን፣ በፌዝና በሽሙጥ፣ በግልፅና በድብቅ ተጉዘው መልዕክታቸውን ያደርሳሉ። ልቡና ያሸፍታሉ፣ እምቢኝ አሻፈረኝ ባይነትን ያጎለምሳሉ፣ በንዴት ያጋያሉ። እየዘገዩም የሚከነክን ደወላቸውን በእያንዳንዱ አዕምሮ ውስጥ ያንቃጭላሉ።

በዓለም ዙሪያ በሚገኙ ወገናቻችንን ዘንድ ታዋቂነትና ዝናን ካተረፉት የደራሲው ወቅታዊ መነጣጥፎች መድበልቶችና ድርሳናች በጣም ጥቂቶቹን ብቻ መዝዞ ለማስተዋወቅና ሀሳቡን ለማሰባሰብ ያህል የሚቀጥሉትን ስራዎች መጥቀስ እንወዳለን።

<u>በረከተ መርገም፣</u>
<u>ዜሮ ፈታውራሪ፣</u>
<u>እናትን በሉልኝ፣</u>
<u>ቆርጠሃት ጣልልኝ፣</u>
<u>ዛር ነው በሽታዋ፣</u>
<u>ወይዘሪት ወይዘሮ፣</u>
<u>የሽግግር ደባ፣</u>
<u>ላሚቱ፣</u>
<u>የማዳም ቀበቶ፣</u>

እና የመሳሰሉት ድርሰቶች በሀገራችንና በዓለማችን በየወቅቱ የታዩና የሚታዩ ጉልህ ክስተቶችን የጊዜን አጥር እየጣሱ አስቀድመው የተነበዩና የሚተነብዩም ናቸው።

ደራሲ ኃይሉ ሀገራችንንና አህጉራችንን በሚመለከት ከአማርኛ ሌላ በእንግሊዝኛ (እንግልጣርኛ)፣ በቻይኒዝ (ሀንኛ) እንዲሁም በግዕዝ ድርሳናትን አዘጋጅተው አሳትመዋል። ደራሲ ኃይሉን በብዙሀን ዘንድ እንዲታወሱ ካደረጉዋቸው ፅሁፎች መሀል ለምሳሌ የሚቀጥለውን መጥቀስ እንወዳለን።

«ከጥንት ጀምሮ እኛ እንዳየነው
ሲነድ ሲቃጠል የሚስቅ እሳት ነው»

«ያሰብከው ዓላማ አልሆን ብሉህ ሲከሽፍ
ሁኔታው ሲጠጥር ጠጣሩ እንዲላላ
የላላውን ወጥር።»
ይላል።

ኃይሉ ገሞራውን እንደምሁር ልዩና ጠንካራ የሚያደርጋቸው ባህሪ ቢኖር በእናት ሀገራቸው ኢትዮጵያ ላይ ፊታቸውን ያላዞሩና ለማናቸውም ዓይነት ጥቅም ተሸንፈው ለሚወዱት ህዝብ ያልተሸራረፈ መብት ከመጠየቅና ከመታገል ተቆጥበው የተቀመጡ የህዝብን ወላኝነት እምነታቸውንም ለድርድር የሚያቀርቡ አለመሆናቸው ነው። ከትናንት በስቲያም፣ ትናንትም፣ ዛሬም መብትና ሚዛናዊ ነፃነት ለተነፈገው፣ ለተጉሳቆለውና ለተዘነጋው ወገን ሁሉ ጠበቃ በመሆን ይግባኝ እንዳሉ አሉ።

እኛ ኢትዮጵያውያን ብዙ ጊዜ የሀገራችንን ባለውለተኞች የምንዘክራቸው በህይወት እያሉ አይደለም ይህን አይነቱን የተለምዶ አሰራር ለማስወገድ በደራሲ ኃይሉ ስራዎች ላይ የምንወስደው እርምጃ አዲስ ፈለግ የሚቀድ ነው። ስለዚህም እነሆ! በዚህ አጋጣሚ በፅሁፍ ተዘጋጅተው ለመታተም የቀረቡት የደራሲው ስራዎች እንዲታተሙ ለማድረግ እያንዳንዱ ወገን ኢትዮጵያዊ በኢኮኖሚው ድጋፍ ላይ ትብብር እንዲያደርግ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ከስቶክሆልም ውጭ የምትገኙ ኢትዮጵያውያን ሀሳባችንን የምትደግፉ ሁሉ ደራሲውን ለመርዳት በምናደርገው ጥረት እንድትተባበሩን እንጠይቃለን። በዚህም መሰረት እርዳታችሁን ከዚህ በሚቀጥለው የባንክ ሂሳብ መዝገብ እንድታኖሩ እናሳስባለን።

Account No. 15570818-1721
Nord Banken
Box 34
162 11 Vällingby

ለምታሳዩን መተባበርም ሆነ ለምትለግሱን እርዳታ ሁሉ ከልብ የጠለቀ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

አዘጋጅ ኮሚቴው


የእትመትና
የትርጉም ሥራ

በኮምፒውተር የአማርኛና
የእንግሊዝኛ የጽሑፍ ሥራዎች
በተቀላጠፈ ሁኔታ

ከለር ማስታወቂያዎች፣ መጽሐፍት፣
መጽሔቶችና
የተለያዩ የአማርኛና
የእንግሊዝኛ ጽሑፎችን በጥሩ ዋጋ
በፍጥነትና ጥራት ባለው ሁኔታ
ለማሰራት ከፈለጉ ደውለው
ገንትን ያነጋግሩ።
በተጨማሪ የትርጉም ሥራዎችን እንሠራለን

ስልክ — (404)508-4657
ፋክስ — (404)508-2447

# ልብ ወለድ

## ፀሐይምሽት

### *ከተምሳሊት ጨዋታ*

በሰይፉ ኣዳነች ብሻው

(መ) መብቱ የተጠበቀ ፲፱፻፹፩/፹፱

SAEFU © Copyright 1989/97

ትሁቴ ከሸዋነሽ አጠገብ ተቀምጧል ። በእጁ የያዘውን ጋዜጣ ያገለባብጠዋል እንጂ የሚያነብብ አልመሰላትም ። ሰዉ የመቁነጥነጥ ስሜት ስለያዘው ወንበሮች ሲንቋቁ ይሰማሉ የሚንሾካሾኩት ተደማምሮ የገበያ ውይይት ያህል ደምቆ ይሰማ ነበር ። "ቴአትሩ ምነው አይጀምርም? ሰዎቹ አልመጡም ማለት ነው?" ስትል ባሏን ጠየቀችው ፤ ሸዋ'ነሰሽ ።

"ማስጠበቅ እኮ የተለመደ ሆል። ገንዘብ ከፍሎ ጥበቃም የሚገርም ነው ።" አላት ትሁቴ ጋዜጣውን ሲያጣጥፍ ኢያንኳኳ እንገቱን አስግጎ ባሏን እየት አደረገው ። "ቶሎ ካልጀመሩ እኔ ትቼላቸው ነው የምሄደው ።"

"ምነው ገንዘቦትን ከፍለውማ አይመልስሎት ፤ እን ደተለመደው ማድረግ ነው እንጂ ።" አለችው የከፈለው ገን ዘብ ዋጋ አጥቶ እንዳይቀር በማሰብ ። ወደ ባሏም ዞር ብላ "ሰዉ በስንት ነገር ይማረራል? እንዲት ዓይነቱ ጊዜ ላይ ነው የጣለን እቴ?" አለችው ፤ ልክ በሌላ ሕይወት ውስጥ የተሻለ ኑሮን እን -ዳሳለፈች ያህል ።

"ባደባባይ ላይ ፖለቲከኛ ወጣሽ!" ሲል ጎሸም አደረጋት ባሏ ።

"ወይ መከራዬ እንዲህ በቅን ሲናገሩ እየተሰሙ ነው ለካ ሰንቶቹ ለጥፋት የተዳረጉት!" ድምጿን አጥፍታ ነበር የተናገረችው ።' ተሰምታ እንደሆነ በመስጋት የባሏን ትከሻ ተደግፋ ወደ ኋላዋ ገልመጥ ብላ ተመለከተች ። ተረከኝ እን ደምታየው ሲያይ ፊቱን ወደ ጎን አዞረ ።

የአዳራሹን መሙላት ሲጠባበቅ የነበረው የመድረክ አዘጋጅ አድነው ትርዒቱ እንዲጀምር ለመብራት ኃላፊው ለአምባር ምልክት ሰጠው ። ከዚህ መንደርደሪያ በኋላ ትርኢቱ እስከተፈፀመ ድረስ አምባር ሲያጠና በከረመው ስልት በሙዚቃ፣ በዱካ፣ በንግግር ጥቆማ እየተመራ ከደብተሩ ላይ ተውኔቱን እያጣቀሰ ተገቢውን የብርሃን ቅንጅት ይከታተላል ። የድምፅ ተቆጣጣሪውም ባልተለየ ስልት እያገናዘበና እያሰማማ ድጋፉን ይሰጣል ። እነኚህ ምትሃተኞች በስውር ለትርዒቱ ሕይወትን እየዘሩለት የከያኒው ባህርይና አድራጎት ጎልቶ እን ዲታይ የደራሲውና የአዘጋጁው ሊቀ-መላዕክት ሆነው ያገለግላሉ ። ለሸዋ'ነሰሽ ግን ራሱ በራሱ የሚሠራ ትንግርት ነው ።

መብራቱ እየደበዘዘ ሲመጣ የሸዋ'ነሰሽ ዐይኖች በጨለማው እየተዋጡ መሄዳቸውን አሳወቃት ። በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ትሁቴ ይቅርታ በመጠየቅ ከመሃል መተላለፊያው ላይ እንደደረሰ የአምባር ረዳት በተንቀሳቃሽ ፈሳሽ ብርሃን አጠመቀው ። "ውይ ሲያቀብጣቸው ተነስተው ሲይዟቸው ነው ።" ስትል ሰጋቷን ለባሏ ነገረችው ። ይለፍህ እየተደናበረ እንደደረሰ የአዕምሮን ባህሪ ለብሶ ነበር ። "ባንተ ላይ ቅሬታ አለኝ ህሊና ።" ሲል ህሊናን ጎንተለው ።

"አይ መከራዬ!" ብሎ አምባር ራሱን ሲወቅስ የሰማው የድምፅ ተቆጣጣሪው ወረጋ "ምን ታደርገዋለህ? ያንተ ጥፋት አይደለም ። ይለፍህ በወቅቱ ከቦታው መገኘት ነበረበት" ሲል አፅናናው ። "አይዞህ! ማንም የሚያስተውለው ስህተት አይደለም ።"

ይለፍህ ከተወሰነለት ሥፍራ ጥቂት ስከንዶች ዘግይቶ በመድረሱ ነበር አምባር ብስጭት ላይ የወደቀው ። ወረጋ የድምፅ መቆጣጠሪያ መደብ ላይ ያሉትን መቆጣጠሪያዎች ከጨለማው ክፍል ሆኖ በሰማያዊ ብርሃን እየተጠቀመ ከአልቦ እንስቶት እስከ ሰባተኛው እፅቅ ድረስ አደረሰው ። ከቡና ቤት ደጃፍ ሲያልፉ የሚሰማው ድምፅ አልፎ አልፎ የተሸከርካሪዎችን ጨምሮ ያሰማ ነበር ።

"ደንታ ይሰጠኛል ብለህ ነው!" ሲል ለአዕምሮ መለሰለት ።

"ለቀበሌ ምርጫ ድምፅህን እንኳን አልሰጠኸኝም ።"

"አንተ ተራማጅ እኔ ሯጭ ሆንንና ተቀዳደምን ።"

"አሹፍ አንተ ።"

"አይምሮ፣ አይምሮ ።" አለው ተንገድግጎ ሄዶ የአዕምሮን ክንድ ለመያዝ እየሞከረ። አዕምሮ ሲሸሽ ከተመልካቹ ላይ ሊወድቅ ደርሶ ነበር ።

*"ጤነኛው ሲያብድ ነው ቴአትር የሚባለው?" ስትል ሸዋ'ነሰሽ ድጋፌን ጠየቀችው ።*

*"ምን ማለትሽ ነው?" ሲል እሱም ወደ ጆሮዋ ቀረብ ብሎ በማንሾካሾክ ።*

*"ሰውዬው እኮ አሁን ጤነኛ ሆነው ከ'ኔ ጋር ሲያወሩ የነበሩት አይደሉም እንዲህ የሚንገዳገዱትም?"*

*"ሥራቸውን ብቻ ተመልከችላቸው ።" በማለት ጥያቄዋን ያላዋዳቀባት መሆኑን ለማሳወቅ ክንዱን በትከሻዋ ላይ አሳልፎ ዕቅፍ አደረጋት ።*

"ስሜ አዕምሮ ነው ። አይምሮ አይደለም ።" አለ አዕምሮ እጁን እያወናጨፈው በመራቅ። "እኔ ከ'ንግዲህ መቀለጃህ አልሆንምና"

"እሺ ሊቀመንበር መንበርዎን እጠርግልዎታለሁ ።"

*"ወየው ጉድ አሳምሮ ነገራቸውም አይዶል!" አለች የሸዋ'ነሰሽ ለራሷ ያህል ።*

"በኔ መቀለድ ባብዮቱ መቀለድ ነው ። እኔ ላብዮቱ የቆምኩ ነኝ ።" የአዕምሮ ተግሳፅ ጥቆማ የሆነለት ወረጋ ከርቀት እንደሚሰማ በመጠነው መጠን የአብዮቱን መዝሙር ከፈተው ።

"ተራማጅ መሰለኸኝ ። አትቁም እንራመድ ። መራመድ እንኳን አልቻልክም ፤ ተሳከረህ ።"

"እኔ አልሰከርኩም ። ከፈለክ እናዳርጋው በዳቦ እገለበጣለሁ ።"

"አለመሰከርህን ካሳመንከኝ በሕይወትህ አይተኸው

የማታውቀው ተዓምር አሳይሃለሁ።"

የድምፅ ተቆጣጣሪው የጉራጊኛው ዜማ የአብዮቱን ውጦት እንዲሰማ ሲያደርግ አዕምሮ ጉራጊኛ ለመጨፈር ይሞከራል። ይህንንም ውዝዋዜ ምክንያት አድርጎ ወደ ቅጥል መድረኩ እየተፈናጠረ ይሄዳል። ህሊናም አጫፋሪ በመሆን ተከተለው።

"ተራው ያንተ ነው። ምንድነው ታምርህ?" ሲል አዕምሮ ጭፈራውን አቋርጦ ጠየቀው።

"አፌን ሳልከፍት እናገራለሁ።"

"አትናገርም።"

"እናገራለሁ።"

"አትናገርም።" አዕምሮ ለመስማት ተጠባበቀ። ምንም ነገር የሰማው ግን አልነበረም። "በላ ተናገራ!" አለው አፉን ገጥሞ ድምፅ ሲያወጣ እሰማለሁ ብሎ በመገመት።

"ተናገርኩ እኮ።"

"ምንም አልተሰማኝም።"

"እርሱ የአንተ ችግር ነው። ጆሮህን መመርመር ያስፈልገሃል።"

"ጆሮዬ በደንብ ይሰማል።"

"ዐይንህስ?"

"ዐይኔም በደንብ ያያል።"

"ታዲያ ቮልሴን የት ነው ያቆምናት?"

አዕምሮ ለቅፅበት አሰብ አድርጎ "ከቀበሌው በር ላይነ" አለው።

*"ጉድ እኮ ነው!" አለች ሸዋ'ንበሸ።*

*"ምኑ የ'ኔ ፍቅር?" ሲል ድጋፌ ጠየቃት። በጆሮዋ የሰማችው ነገር እናቷ ውስጥ ተናግቶ እካላቷን በመዝለቅ እስከ እግሯ ድረስ ነዘራት። 'የ'ኔ ፍቅር!' የሚለው ማር ቀመስ አባባሉ መላ ሰውነቷን አንጠረጠዘው።*

*"ባይናቸውም ጭምር ያስባሉ ማለት ነው ቴአትር ሲሰሩ? ስላይኑ ሲጠይቀው ሃሳብ ውስጥ የገባው?" አለችው በመገረም።*

*"አካላቸውን ሁሉ ነው የሚጠቀሙት።" ሲል በአጭሩ ገለፀላት።*

"ከአብዮቱ ደጃፍ? እርሷንም የማርክስ ሠርቶ አደሮች እንደሠሯት ታውቃለህ? ሁለቱም ጀርመናዊ ናቸው።"

"ማርክስ ራሺያዊ ነው!"

"ፑሽኪንስ?"

"ፀረ-አብዮተኛ ነበር።" ከማርክስ፣ ሌኒን፣ እንግልስና ጓድ መንግሥቱ ስሞች ሌላ ሁሉ ፀረ-አብዮተኛ ነው፤ ለአዕምሮ። ግራ ክንዱ እስኪ.ወልቅ መፈክር የፈከረባቸውን ባህርያት አጠቃልሎ አልመረመራቸውም።

ህሊና ቀስ በቀስ ማስተማር ስለነበረበት ፑሽኪንን ሊያስተዋውቀው ፈለገ። "ፑሽኪን በአያቱ ኢትዮጵያዊ የሆነ በሥነ-ፅሁፉ በዓለም የታወቀ ሰው ነበር።"

"አበሻ የገባበት ነገር ሁሉ መበላሸቱ አይቀርም።"

"ሃሰት። የአበሻን ደረጃ የሚያዋድቁና የሚንቁ ናቸው የአበሻን ታላቅነት የሚጥሉት። የራሳቸውን ውድቀት በኅብረተሰቡ የሚያሳብቡት፤ የራሳቸውን ድክመት መሸፈኛ የሚፈጥሩት።"

"ይኼ ቁምነገርህ ነው ትንፋሽህን የሚጠብቅልህ" አባባሉ የለበጣ ነበር። በአንድ የታሸገ የጠርሙስ ጠላ መገላገል ስለማይችል ወደ ጠጁ ቤት ጎራ ማለት ሲጀምር ነው ከአዕምሮ ጋር ዕውቂያ የፈጠሩት።

"ከዘነቡሽ ቤት ጎራ ብለን በሰፊው እንወያይ።"

"ስላብዮቱ እንስተህ ማውራት አይኖርብህም።" ሲል አስጠንቀቀው። በትምህርት ደረጃቸው ምን ያህል እንደ ሚለያዩ ያውቃል። በጓደኝነት ይህ ልዩነታቸው ተውጦ የጠበቀ አቀራረብ ነበራቸው።

"ይኼማ የመናገር መብቴን ተነፈግሁ ማለት ነው።"

"አፍ አላፊ ከሌለበት ተቃውሞ የለኝም።"

"እኔ ግን ተቃውሞ አለኝ።" አለ ህሊና። "የነፃነት ገደብ የለውም። ገዳቢም አይኖረውም።"

"ሕግና ዳኛ ይኖራል።" እህቱን እያደበደበ ያስቸገረውን ባሏን ድንጋይ አሸክሞ እግሯን ካሳመው በኋላ ከዛፍ ላይ አስሮ ጀርባው እስቲተላ ድረስ በመግረፉ በፖሊስ ተይዞ ፍርድ ቤት በቀጠሮ በቀረበ ወቅት ለምን ወንጀሉን እንደፈፀመ ዳኛው ሲጠይቁት "እኔ እህያዬን እንኳን ከፊቷ ሆኜ እኅትታለሁ እንጂ ሂጂ ብዬ አልደበድብም። እናቱን እህያ አድርጎ የሚያስደበድብ ገልቱ ካለ ክብር አይገባውም" ሲል ይመልስላቸዋል። ዳኛውም እህቱ እንጂ እናቱ እንዳልነበረች ያስታውሱታል። እህቱ ልጅዋን ይዛ እንድትመጣ አዝዟት ስለነበር ወደ ህፃኑ በጣቱ ጠቁሞ "ተፋረድልኝ ያለኝ ይሄ የ'ህቴ ልጅ ነው።" ሲል ቢመልስላቸው ፍርድ ቤቱን ሳቅና ሁካታ ዋጠው። ዳኛውም ጠረጴዛቸውን ደብድበው ፀጥታው ሲመለስ በምን ቋንቋ እንደነገረው ሲጠይቁት "ሁሉንም እኔ በሱ ቦታ ሆኜ እየሁት።" አላቸው። "አንተ ግን ሕግና ዳኛ ይኖራል ብለህ አላሰብክም።" ብለው ፍርዱን አከናንበውት ከርቸሌ ገብቶ ነበር የወጣው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ *'ሕግና ዳኛ'* ፈሊጡ ሆኖ ቀረ።

"የህዝቡን ደኅንነት፣ የአገሪቱን አንድነትና ነፃነት ለመጠበቅ በርግጥ ሕግና ዳኛ ይኖራል።"

"ይህም የነፃነትን ገደብ ይፈጥራል።"

"ለምን ወደየቤታችን አንሄድም።"

"ዘነቡሽን ሳታይ እንቅልፍ ይወስደኛል ብለህ ነው። ይልቅ ለርሷ የፃፍኩትን ግጥም ዝፈንልኝ።"

"ለምን ራስህ አትዘፍነውም።"

"እኔ በደንብ አልሰከርኩም ገና። እኔ እወርዳለሁ፤ አንተ ተቀበለኝ።" እየተንገዳገዱ ከቅጥሉ መድረክ ደረሱ። አምባር የመመሪያ ደብተሩን ተመልክቶ ተንቀሳቃሹን የብርሃን ፍላሽ ከእናት ላይ ከሚፈስሰው ብርሃን ጋር ከአዋኸደው በኋላ በሦስት ሰከንዶች ቆጠራ አስወገደው። በእናት የብርሃን ባህር እየተጠመቁ ትሁቴና ይለዩህ በተኮላተፈ ልሣን እውራጅና ተቀባይ ሆነው ይዘፍኑ ጀመር።

ደረቷን ደረቷን የተኛሁበትን
ሳላለብሰው ቀረሁ ቀርታለች ዕራቃኗን፤
አትዩት፣ አትዩት፣ አትዩት ከንፈሯን
ተስሜአለሁ ብሎ ሲያጋልጥ ምስጢሯን።
ያመላልሰኛል ድግምት አዙራብኝ
እሷን፣እሷን እንጂ ቆንጆ መቼ ታየኝ።
ያም አይቶ፣ ያም አይቶ ልሳምሽ ያላት
አትጠጊኝ አላት ቀምሶ ቢንቃት።
ጡቷን እንተርሳኝ ጡቷን ብታለብሰኝ
የሞቀ ጎጆዬን ትዳሬን አስጠላኝ።

ተዳከመው እንደተያያዙ ያጠመቃቸው ብርሃን ይጠፋል። ኮቴአቸውን ሳያሰሙ ተውኔቶቹ ከነበሩበት መድረክ ይሰወራሉ።

* * *

ቀዳሚው መጋረጃ ወደ ግራና ቀኝ እየተተረተረ

በመከፈት የብርሃን ፍንጣቂ ከመድረኩ መሃል መታየት ይጀምራል። የክፍሉ ግድግዳ ከትልልቅ ፎቴዎችና መጋረጃው ወደ ጎን ሸብ ከተደረገ መስኮት የጓዳና የመኝታ ቤቱ በሮች ጨምሮ የተደላደለ እልፍኝነቱን በብርሃኑ ውስጥ ይመሰክራል። ከክፍሉ መሃል ላይ ሶፋና ጠረጴዛ ይታያል።

ፀሐይምሸት ሽጉጡን የምትደብቅበት ሥፍራ ትፈልጋለች። በመጨረሻም ከሶፋው ሥር ትሸጉጥና ከትራሱ ላይ ጉብ ትልበታለች። ትንሽ እንደቆየችም ታላዝናለች። ወረቃ ሌላ ክር ከማጫወቻው ውስጥ አስገብቶ ይጠባበቅ ስለነበር የድምፅ መቆጣጠሪያውን እጀታ በቁንጥ አገፋፍ ከአልቦ ወደ ዘጠኝ አፅቅ ገፍቶ ልክ በወቅቱ እንደተጠናው በማድረጉ እምባርን የድል ምልክት በጣቱ አሳየው። የተሽከርካሪ ግጭት፣ የበር መከፈትና መዘጋት ተሰማ።

ህሊና ከመድረኩ ላይ ሲገባ የአንድ እግሩን ጫማ በቀኝ እጁ በሌላኛው እጁ ያወለቀውን ሱሪ እንደያዘ ነበር። እየዘፈነ ወደ መኝታ ቤት በር ሲያቋርጥ ሚስቱ በመገረም ትመለከተዋለች። ፀሐይምሸት እንቅልፏን ማጣቷ ነው እንጂ ያልጠበቀችው እንግዳ ነገር ባለመሆኑ እያዛጋችና ዐይኖቿን እያሻሸች ከመመልከት ሌላ ምንም አላለችውም። እርሱ ግን የአለማየሁ እሸቴንና የጥላሁን ገሠሠን ዘፈኖች ለመዝፈን እየሞከረና የራሱን ግጥም እየደረደረ የመኝታ ቤቱን በር ይቆረቁራል።

ባለቤቴ፣ ባለቤቴ፣ ውዷ ባለቤቴ...
ኳ፣ ኳ፣ ኳ፣ኳ!
ሃሳቤ ሰፍቶ ልቆ
ከውቅያኖስ ጠልቆ
ወደ ጎዋ አምጥቆ፤
በየእቅጣጫው ተበታትኖ
ውስብስቡን በምናኖ
ችግሩን በጉዞ ሲወጣው
ኃይሉን አስተባብሮ ሲታገለው።

*"ስካራም እንዴት የሚያስጠላበትን አያውቅም? ለምን አያስወጧቸውም? ቴአትሩ ሲመጣ እኮ ይበላሻል።" ስትል ሸዋ'ነሰሽ ለባሏ ሹክ አለችው። ቴአትሩን እንዲሠራ ከተከፈላቸው አንዱ እርሱ እንደሆነ ሲገልፅላት "እንዴ ከዚህም አይደል ብድግ ብለው የሄዱት?"*

*አዎን! በተመልካችነት የሰውን ህልውና በማጥናት ከሕይወታቸው ጋር አገናዝበውትና አዛምደውት በጥናት የሚያንፀባርቁት ግብረ-ገፅታ ያለው ሥራ ነው። ከተመልካችነት ወደ ተካፋይነት ያንፀባረቀባት ይቅርታ ጠይቋት ከተለያት ጊዜ ጀምሮ ነበር። 'ሰው እንዲህ በደቂቃ ይለወጣል?' ጥያቄው ጭንቅላቷ ውስጥ እየተጉላላ መመልከቷን ቀጠለች።*

ኳ፣ ኳ፣ ኳ፣ኳ!
አለሞት ጉዞ አያቆመኝም
እስከሞት ድረስ ደግሞ መኖሬን አውቃለሁ።
ኳ፣ ኳ፣ ኳ፣ኳ!
በሃሳብ ተይዤ
ባለሁበት ደንዝዤ
በቀለም ውስጥ መዋዠቄ
አዕምሮዬ በሌላ ዓለም ሲከለል
ዐይኔ ፈጥጦ አካባቢዬን ማየት ሳይችል
ሳልረዳው ሳላውቀው
ወደነበርኩበት ስመለሰው
አሁንም ብቻዬን ነው።

ኳ፣ ኳ፣ ኳ፣ኳ!
ወይ እሺ በይ ወይ እንቢ በይ
በመግደርደር ሰው አትግደይ
አለሙሺ ማሞቦ፣ አለሙሺ ማሞቦ፤ አለሙሺ
ጀነኑሽ ውስኪ፣ ጀነኑሺ
ባለቤቴ፣ ባለቤቴ፣ ውዷ ባለቤቴ

እየዘፈነ ዞር ሲል ሚስቱን ከሶፋው ላይ ነቅታ ስትመለከተው ያያታል።

"ከደጅ ደግሞ ምን ታደርጊያለሽ? ህፃን ልጅ መሰልኩሽ ከውጪ የምትጠብቂኝ። የእኔይቱ ፀሐይምሸት የእጥሩን በር የሚከፍትልኝ አጥቼ ከደጅ ነው ያቆምኳት።" በእጁ ምልክት እያሳያት "ነይ ቤት እንግባ።" አላት። አልመለሰችለትም። በዝምታ ስትመለከተው ፈራት። ሳትቀድመኝ ልቅደም በማለት "እኔ ሰላም ነው የምፈልገው። እዚህ ቤት ሰላም የለም ከተባልኩ ሽጉጤን አምጡልኝ።" ሲል ደነፋ። ወደ መኝታ ቤቱም ደረሰ ብሎ በመመለስ "ዛሬስ አን ደበትሽ ታስሯል። *'ሰጋት ላይ ጣልከኝ፤ ምነው አመሸህ!'* ማለትሽ ምነው ቀረ?"

"አሁንስ ጨርቅህን ለመጣል ምንም አልቀረህም።" አለችው የትዝብቷን።

"ሞኝሽን ፈልጊ። እንደገባሁ ከንበል ልል ከበሩ ላይ ነው ያወለቅሁት።" ሲል መለሰላት በራሱ ብልጠት እንደ-መኩራት ብሎ። ጥቂት ቆይቶ ግን አባባሏ ቆረቆረው። "እሃ! ጨርቁን የሚጥል ያበደ ነው? ባልሽ ያበደ መሰለሽ? ያበድሺውስ አንቺው ነሽ።"

በዕብደት አርዕስት ላይ ልትቀጥልበት አልፈለገችም። ነገሯን ለመለወጥና የማይቀርላትን ኃላፊነት ለመወጣት "ራትህን ላሙቅልህ?" አለችው፤ መጠጥ የሞላው አንጀት የምግብ ፍላጎት እን-ደማይኖረው ብታውቅም። በተለይ እሱ አስቀድሞ ሳይበላ አልኮል ከቀመሰ ስለሚፀናወተው ከአንድ ጉርሻ በላይ ፊፅሞ አይነካትም። ቁርጥና ክትፎ ሲሆን ግን ሆዱ አልጨከን ብሎ እንብርቱ እስቲገለበጥ ድረስ ይበላና ሌሊት በምጥሚጣውና ቅመሙ በቃር ሲቃጠልና አንጀቱ የገባውን ሥጋ አልፈጭልህ እያለው በቁንጣን ሲጨነቅ ያድራል።

"ሙቅ ነው የምፈልግነ የተሞቀ አልፈልግም።"

"እጥሚት ለ'መጫት ነው!" ለማሾፍ ነበር የተናገረችው።

"እኔም እመጫት ነኝ እኮ!"

*"ድንቄም እቴ! የዘንድሮ ወንዶች" ስትል ሳይታወቃት ሸዋ'ነሰሽ ጮኸች። ህሊና ወዲያው ቀጥሎ "ስንቱን ባጎሬይ ነው አርግዤ የተገላገልኩት።" ሲል ብትሰማው ሃፍረት ተሰማት። በዚህን ጊዜ ባሏ ወደ ጆሮዋ ቀረቦ "አይዞሽ አትፈሪ። ተመልካቹ አንቺም ቴአትሩ ውስጥ ያለሽ ነው የሚመስለው።' በማለት አፅናናት።*

"ወረቀት ላይ የሚቀሩ አመፀኞች ትወልዳለህ።" አለች ፀሐይምሸት ሥራውን በማጥላላት ሳይሆን ሕይወታቸው አልታይሽ እያሉ ስለሚያስቸግሯት።

የፀሐይምሸትን ባህርይ የምትጫወታት የታወቀችው ተዋኒት ማድነቂያሽ ነች። ም'ረቴ እንደፃፋት ከወረቀት ላይ አልቀረችም። ከወልቃዬ ጋር ተመካከረው ፅሁፏ በፅሁፍ ታድሳ የኪነት ባለሙያተኞች በጠረጴዛ ዙሪያ አንብበዋት። በችሎታና በምልመላ ዕድል የደረሳት ማድነቂያሽ ጥናት አድርጋባት፣ መርምራትና ተጠያይቃበት ነው ከልሙጥ ወረቀት ሕይወት አላቅቃት አምላክ በእስትንፋሱ ሕይወትን

እንደዘራባት በእስትንፋሷ ሕይወትን የሰጠቻት። ቤቷንም አቶ ታምራት በጥናት ተመርኩዘው ከነደፏቸው ንድፎች በቴአትሩ አዘጋጅ የተመረጠውን በመድረክ ገፅ ቅብ አሳምረው የሰሩላት። ህልውናዋ በዚህ ብቻ የተደገፈ አይደለም። የመብራት አዘጋጁ ወጣት ቀልቡ ተንጠልጣይ የጣሪያና የጎን እንዲሁም ተንቀሳቃሽ መብራቶችን ሲያዘጋጅ ለቴአትሩ ተስማሚ የሚሆነውን ገፅታ ለመፍጠር የሚሰካቸውን የተለያዩ ባለቀለም የላስቲክ ማፈኛዎች ለጠይም፣ ለጥቁር፣ ለቀይ-ዳማ ሰውና ለአልባሳቱና ለቁሳቁሱ የሚስማማ መሆኑን በእጁ የጀርባ ቆዳ ላይ እያበራ በመለካትና በማጥናት ነበር ያዘጋጀው። ተዋንያኑ ከንባብ ጀምረው በቁም መውረዱን አልፈው የጥናት ደብተራቸውን ጥለው ባህርይን ለብሰው እኛ ነን እስኪሉ ድረስ የጥናት መሪያቸው ጉራባቸው መስመር በመስመር እየተከታተለ ይረዳቸው ነበር። እንዲያውም እሱ ቴአትሩን ከዳር እስከ ዳር በቁሙ ከማንብነብ ደርሶ ነበር። ማድነቂያሽ ፀሐይምሸትን መሆን ስትጀምር ልጅ ይታጠቁ አልባሳቱን በወቅቱ ለማድረስ መቀስ፣ መርፌና ክሩን አዘጋጅቶ ረዘሙ ሲሉት እያሳጠረ፤ ሲጠብብ እያሰፋ ተስማሚ እስኪሆን ድረስ እያማረጠና እየተወያየ ፈፅሞ አቅርቧል። ቤቷን በየጊዜው የምታዘጋጅላት በመድረክ አዘጋጁ አድነው ሥር ያለችው ቁሳቁስ አዘጋጅዋ ብርንጉድ ነች። ቴአትሩ ከመጀመሩ በፊትም ሆነ መጋረጃ ከተዘጋ በኋላ ቁሳቁሶችን ከሚፈለጉበት ቦታ በማስቀመጥ ታዘጋጃለች። ትርኢቱ ከመጀመሩ በፊት በገፅ ቅብ ባለሙያዋ በወጋየሸ ከመደበኛ የፊት ቅባት አንስቶ ፊቷ በብርሃኑ እንዳይወዛና እንዳይወረዛ ትክክለኛ ዕድሜዋን ሊያንፀባርቅ በሚችል አኳኋል ታዘጋጃታለች። ደራሲው ግን በድኑን ፅሁፍ እንዳለ ከመድረክ ላይ አውጥቶ ሕይወት እን ዲያገኙ የኪነት አርበኞችን አስተባብሯል። ጎያዋን ህሊናቸውን ቀብረው በሌላው ሕይወት በራሳቸው ገፅታ በተመልካቾቻቸው ዐይኖች ፊት በመቅረብ መላ መንፈሣቸውን እየሳቡ ህልውናቸውን ያስመሰክራሉ። ሸዋ'ነሰሽ ከነዚህ ሕይወትን ከሚያሳዩ የወረቀት አመፀኞች ጋር በመተዋወቅ መንፈሷን ከመድረኩ ላይ አቅርበዋለች። ላውራችሁ፤ ላርማችሁ ትላለች።

"ከእውነት ያልራቀ ነገር አሁን ተናገርሽ። ከምጣድ ላይ እንደተውኩሽ አልቀረሽም። እየበሰልሽ ነው።" ህሊና ነበር የተናገረው።

"እንዳንዴም እውነት አላቸው።" ፀሐይምሸት ለጭቅጭቁ ተዘጋጅታለች።

"ምኖቹ?"

"ደመኞችህ።"

"እኔ ደመኛ የለኝም።"

"ሌት ከቀን የሚያባርሩህ ታዲያ ምኖችህ ናቸው? ወዳጆችህ?"

*"ሰው ጠላቱን ካልለየ ባመነው ሰው ነው የሚጠፋው።" አለች ሸዋ'ነሰሽ ድምጿን ዝቅ አድርጋ።*

"እነሱ የሣቅ ደመኞች ናቸው። እኔን በማጥፋት ሣቅ (ሰርቅታ)..... ሣቅ የምትጠፋ ትመስላቸዋለች። ባይሆንማ ኖሮ ከእኔ ጋር ትንንቅ ምን ገድዷቸው?"

"እንተም የእነሱን ቁስል ከመንካት አልቦዘንክም።"

"እንነጋገር ከተባለ..." ትኩር ብሎ ካስተዋላት በኋላ "አትድከሚ። እኔ እንደሆንኩ ከንቱ ሆኛለሁ። ማስቴ ተዳክሜአለሁ።" ፀሐይምሸት ካለበት እንደተገተረ ጥላው ወደ ውጪ ወጣች። ህሊና ህሊናው ተምዘግዝጎ በመሄድ በአዕምሮ ውስጥ የጀመረውን ምርምር በሃሳቡ እያውጠነጠነ ልሣኑ ሲከፈት የመድረኩን ላይና ታች ግራና ቀኝ ያለበሰው ብርሃን እንደጉም እየተነነ እንደ ቀትር ፀሐይ በእናቱ ላይ የበራው ብቻ ቀርቷል። አምባር ከጨለማው ክፍሉ ከወረጋ ጎን ቁጭ እንዳለ ህሊናን ተቀፅሎ ማነብነብ ጀምሯል። ሥራውን ከጀመረ አንስቶ አሁን ይበልጥ ተዝናንቶ ይገኛልን ፀሐይምሸት ተመልሳ ስትገባ ህሊና በተራው ወደ ውጪ ወጣ ብሎ ይመለሳል።

አስተያየቷ ጥያቄን የያዘ መሆኑን ስለተረዳ "የደጁን መብራት ሳታበሪው ቀርተሽ ነዋ!" አላት ጥፋቱን በእሷ ላይ አድርጎ።

"ምክንያትህ አጥጋቢ አይደለም።"

"ትወራረጃለሽ?"

"የመኪናዋ መብራት ምን ሆኖ ነው?"

"እንደኛው ተጋጭቶ ተሰብሯል።"

"ሌላኛውስ?"

"እርሱ ደግሞ ተቃጥሏል።" ጥፋተኛ ሆኖ ላለመገኘት ምክንያቱን ይደረድርላት ጀመር።

"አልሞትኩም እንጂ እኔም እየተቃጠልኩኝ ነው።" አለች ተሰፋ ስትቆርጥበት።

ይሄ የዘዴ ማሸነፊያዋ ስለሆነበት የእዞ ዕንባውን ማን ባቱን ቀጠለ። "ሰላም እመቤቴ፣ እግዚኦ ፈጣሪዬ፣ አቤት ጌታዬ፤ ሰንቱን ተማፅኖ ይቻላል።"

"ከንቱ ነህ አንተን ፍፁም ለሰው አታስብም።" ፈልጋ አልነበረም የተናገረችው። የትዝብት ህሊናዋ እንደበቱን ከፍቶ ስለተሟገታት ብቻ ነበር።

"ነገር እንደዚህ ሊጠብቀኝ እዚያው ከጠጅ ቤት ስጨቃጨቅ አላድረውም ነበር።"

"ታዲያ ምን መንገድ አለፋህ። እዚያው ያተላ ጥራጊ አትሆነውም ነበር!"

*"የሰላም ገበያዋ አቤት ነው ማለት ነው?" ሸዋ'ነሰሽ ነበረች በትዝብት የተናገረችው።*

"እንቺን ብዬ፣ እንቺ አለሽኝ ብዬ።"

"ከቤትህ ሶፋ ላይ እንቅልፍ እያዳፋት የምትጠብቅህን ሚስትህን እንኳን መለየት ተስኖህ በስካር መንፈስ አልፈሃት የመኝታ ቤቱን በር ነበር ስትቆረቁር የነበርከው።"

"እትቀልጂ! ክምርሽ እንዳይሆን። ለእኔና እንቺ የተድላና የደስታ ምንጭ ገነታችን መኝታ ቤታችን መሆኑን አታውቂም?"

"ሌላውስ ኑሯቺን በምን ላይ የተመረኮዘ ነው?"

"እንቺ ልብስ ስታጥቢ እኔ ታሪክ እፅፋለሁ። እንቺ ወጥ ስትወጠውጭ እኔ ጋዜጣ እነብባለሁ። እንቺ እንጀራ ስትጋግሪ እኔ ለተባዕቱ ዲስኩር እሰጣለሁ።"

*"ፀሐይምሸት ደ'ም ምን የሚሉት ስም ነው?" ብላ ሸዋ'ነሰሽ መንገድ ላይ ታክሲ ውስጥ እያሉ ለጠየቀችው ጥያቄ የሰጣት መልስ ትዝ አላት። "ደራሲው የሰጣት ስም ነው።"*

*"የክርስትና አባቷ መሆኑ ነው።"*

*"አምላኳም ጭምር ነውን እሱ ነው በፅሁፍ ሕይወትን የሰጣትን ባሏ ደራሲ ነው።"*

*"ስለምን ስለደራሲ ፃፈ?"*

*"ደራሲ በመሆኑ ስለደራሲ ችግር ስለሚያውቅ።' መን ገዱ ከጎማው ሥር እየተጠቀለለና ሀንፃዎች፣ ሌሎች ተሽከርካሪዎች፣ መንገደኞችና አውቶቡስ ጠባቂዎች ወደ*

*ኋላቸው እየተንሸራተቱ ሲሄዱ ወደ ውጪው ስትመለከት ቆይታ መለስ ብላ አየችው። በመልሱ እንዳልረካችና እራሷ በራሷ ልትረዳ እንደተቸገረችበት ገፅታዋ ላይ ይነበብ ነበር። በድንገት ፈገግ አለችና ድጋፌ በጥርጣሬ ተመለከታት።*

*"በልጅ አመሃኝቶ አሉ!" አለችው።*

*"ምኑ?" ሲል ግራ በተጋባ መልክ ጠየቃት።*

*"የመናገር መብት ለሌለ የሚናገርለትን አስመስሎ ፈጠረ። አሁን አሉ አሉ ተብሎ እንደሚወራ ወሬ መልዕክቱ እንዲዳረስ ነው ስለ ሌላው ፀሀፊ የፃፈው።" በአድናቆት ከመመልከት ሌላ ምንም አላላትም። እሷም ሆነች እሱ አሁን የማያውቁት ፀሀፊው ስለደራሲው ሕይወት ከፃፈው ታሪክ ጋር የተሳተፉትና በመድረክ ላይ እንዲታዩ ካደረጉቸው ሰዎች ጋር አክሎ ከኋላቸው የተቀመጠው ሌላ ፀሀፊ አቶ ተረከኝ በጎሊና ማጎደሩ ላይ እየፃፈ መሆኑን ነው። አቶ ታረከኝ ደግሞ ከእነሱ ጋር አከየው ስለፃፍኩት ይህንን ፅሁፍ ሲያነብ ሳይገርመው አይቀርም።*

"ምን የሚሉት ሥርዓት ነው?" አለች ፀሐይምሸት።

"የሥራ ድርሻችንን የምንወጣበት ሥርዓት።" ከኋላዋ ሄዶ ያቅፉታል። ከኋላዋ እጆቹን በወገቧ በኩል አሳልፎ አን ደኛው እንብርቷን ሲያሽ ሌላኛው ጡቷን ያፍረጠርጥ ነበር። ፀጉሯን ከአንገቷ ጋር በጉንጩ እያሻሸ አልፎ ጉንጯን በጨዋታ መልክ ነከስ ያደርጋታልን ከዚያም የግጥም ድርደራውን ይቀጥላል።

"የትንፍሽ ግብዣ ከእንገት ሥር
የልብ ትርታው ሲንር
የፍቅር ስሜት ዕርካታው
የመንፈስ ዕረፍት ደስታው"

ፀሐይምሸት ከዕቅፉ ትወጣለች።

*"ሰው መኖሩንም ረስቶታል ልበል? ወይንስ ንቀት ይዞት ነው።" ስትል ሸዋ'ነሰሸ ሹክ አለች።*

*"ሥራው ነው። ይከፈለው የለም እንዴ!" ሲል መለሰላት ድጋፌ።*

*"ነውር አያውቅም እቴ!" ብላ ዝም አለች።*

ህሊና ራሱን በራሱ እንዳቀፈ ከመድረኩ መሃል ላይ ከር ላይ እንደተንጠለጠለች እንዝርት እየተሸከረከረ ግጥሙን ያወርደዋል።

"የጎዋሳት ተድላ ፍንጪታ
የጥምር አካል ጨዋታ
ገጥመው ሲታዩ ከደረት
በፍቅር ቅምሻ ስሜት
ገላን ከገላ ማጣበቅ
በፍቅር ንዳድ መቅለጥ
ከዓለም ውጪ ሌላ ዓለም
በእቅፍ ተያይዞ መስለምለም
መምጠጥ ሲይዙ ምላስን
ላንቃ ጠረጋ የውስጡን
በፍቅር ተውጦ በለበቅ
በላብ ተነክሮ መዘፈቅ
ከወዳጅ አካል በፍቅር ምልዓት
የሕይወትን መዓዛ መቅመስ ከፀእዲት።"

ለፀሐይምሸት ምንም አልጣማትምን እንዲያው ለነገሩ ያህል "ራትህን ትበላለህ፣ አትበላም?" ስትል ጠየቀችው፤ በትዝብት እያስተዋለችው።

"የሚላስ የሚቀመስ ተገኘ ወይንስ የአልጋውን አውድማ ነው የምትመክሪኝ። አትድከሚ። እኔ እንደሆንኩ ከንቱ ሁኛለሁን።ማለቴ ተዳክሜአለሁን" ከሶፋው ላይ ተቀምጦ ሱሪውን ይታጠቃል።

"ገብተህ አትተኛም?" ብቻዋን ማደር አስጠልቷታል። ጠረኑ ከራቃት ከርሟል። በምታውቀው መዓዛ ሽታ ልትሰክርበት ከፈለገች ከርማለች። ኃጢአትነቱን ፈርታ፤ ነፍሴን ብላ እን ጂ ቀበሌ ውስጥ ለጥቂት ጊዜ ታስሮ ላየችው ልጅ ገፁብረከት ብትሆንላት ደስ ባላት ነበር። መንፈሷ የስሜት ዑደት ውስጥ ገብቶ መላ አካሏን ሲያወራጭባት ግን ካንቺ ሌላ ሕይወት ስታሰኘው በህልሟና በሃሳቧ ሽው ይልባታል።

"በዝግ ችሎት ከምትጨቀጭቂኝ እኔ እዚሁ ብተኛ ይሻለኛል።"

ከፎቴው ላይ ጋደም ሲል ትታው ወደ መኝታ ቤቷ ገባች። ከዚያም ሆና ጠራችው። "ህሊና፣ ህሊና፣ ህሊና!"

"ምን ፈለግሽ!" በድካም መልክ ነበር የመለሰላት። ጥሩ እንቅልፍ አግኝቶ ቢያድር እየተመኘ ሰውነቱን ከሶፋው ላይ አስተካከለ።

"አልጋውን ወደ ሳሎን ላዛውረው ነው።" አብዳለች ሲል አሰበ።

"ምን አስጨነቀሽ?"

"ተኝተህበት ስለማታውቅ ናፈቅሁት ይላል።"

"ከአልጋው ፍቅር የለኝም።"

አልወድሽም ያላት ያህል መንፈሷ ተሰበረ። በዕድሷም እያማረረች አልጋዋ ላይ ወጣችና ጥቂት ካመዛዘነች በኋላ እን ዲመጣላት በተለየ መልክ ልትነግረው ፈለገች። "ሶፋውን ስለማልጋራህ ነው የወደድከው፤ አይደለም?"

"ለጎኔ ስለሚስማማኝ ብቻ ነው።"

"ለጎንህስ የምስማማህ እኔው ነበርኩ። እንደ ዕቃ ቆጥረህ ተውከኝ እንጂ።"

ነገር እየከረረ መምጣቱ ታወቀው፤ ህሊና። "የሴሊቱን ፀጥታ የሚያደፈርስ የጅብ ጩኸት ብቻ ነው።" አላት።

"ጂቡ መጮሁን ቀንም ቢሆን አልተወም። በፖለቲካው አብደህ፣ በቀለም ተሳክረህ፣ ትዕቢት ተሞልተህ፣ በብረት የታጠረን መንግሥት ባፍህ ለመጣል ስትጥር፤ ትችቱን፣ መበዝበዙን፣ መጉላላቱንና መደፈሩን የቻልኩት እኔ ነኝ።"

ቅንቅን የወረረው መሰለው። ሰውነቱ ከተኛበት ዕረፍት አጣ። እንቅልፋ እየከዳው መጣ። ቀና በማለትም "ሽጉጥ ገዝቼ የሰጠሁሽ ለምንድነው? በርሽን ደፍሮ የገባውን ሁሉ እንደ ቄጤማ ለምን አትጎዘጉዢውም?" አላት በጭቅጭቁ በመሰላቸት።

መሳቅ አሰኝቷት ነበር። "አንተን ጥዬ የት ለመኖር? ነፍሴን ገነት አትጠብቃት፤ ገሃነብ ገብቼም መጥተህ አትጠይቀኝ። የሰቃይ የሰቃዩ እዚሁ ልሰቃይልህ ብዬ ነዋ!"

*"ፈርዶብሽ፤ አፈር ልሁንልሽ።" ስትል ሸዋ'ነሰሸ ከን ፈሯን መጠጠች።*

"ወይ ሰበብሽ!" አለ ህሊና ጎኑን እያመቻቸ። አሁን ም ለመተኛት ይታገላል።

"ያማረብህ መስሎህ ነው የምታሾፈው?"

"መንፈሴን አድኼው ጠዋት በጥሞና እንነጋገራለን።" በጀርባው ሆኖ ያንጋጥጣል።

"ለቀጠሮው እንዳትዘገይ።"

(ወደ ገፅ 34 ይዞራል።)

# አገርንና ሃይማኖትን ለመጠበቅ አማንያንን ማዳን ከሃይማኖት አባቶች ይጠበቃል

ከበደ አገኘሁ – ከፖርትላንድ ኦሬገን

የሃይማኖት አባቶች ሃይማኖት እንዳይጠፋ የግድ የሃይማኖት ተከታይ የሆነውን ህዝብ ስጋዊ ህልውናውም ፍትሀ–ርት በሰፈነበት፤ የዘርና የጎሳ አድልዎ በሌለበት ምድራዊ በሆነው መንግስታዊ አስተዳደር እንዲኖር አቤቱታቸውን ለሰማያዊው ንጉሥ ብቻ ሳይሆን በዚህ አለም በምእመናንን መእመናት ላይ ኢሰብአዊ ግፍ የሚፈጽሙትን፤ የህዝቦችን አንድነት በጎሳ፣ በዘርና በሃይማኖት እየከፋፈሉ በህዝቦች መካከል ብዙ እልቂት እንዲደርስ ምክንያት የሆኑትን ስጋውያን አምባገነን መሪዎችንም ያለ ምንም ፍርሃት ማውገዝና መታገል አለባቸው። ‹‹ሥጋን ከመግደል አልፈው ነፍስን መግደል የማይችሉትን ሰዎች አትፍሩ›› ይላል ጌታ በማቴዎስ ወንጌል ም. 10 ቁ. 28።

በመሪር አገዛዝ ተይዘው በምድራዊ ኩነኔ በጨለማ ኃይሎች በደይን ውስጥ ተውጠው ለሚኖሩ ምዕመን ቤዛ መሆን ከመንፈሳዊ አባቶች ያልተጠበቀ ከማንም ስጋዊ መሪ አይጠበቅም። ምክንያቱም ህዝቦችን ከዚህ አይነቱ አስከፊ ቄቆና ለማለቀቅ ኃቀኛ የሆኑ ዓለማዊ መሪዎች ለህዝብ ቤዛ እየሆኑ ቢሰውም፤ ቢታሰሩም፤ ቢገረፉም ወይም ቢሰደዱም መቸም አለማውያን ናቸውና የፖለቲካ ስልጣን ለመጨበጥ ብለው ነው የሚል ስም ሊሰጣቸው ይችል ይሆናል። ጠላትም የፖለቲካ ተቀናቃኞች ናቸው እያለ በሰበብ ባስባቡ ለማጥፋት ይሞክራል። ለዚህም ነው እንደነ ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ፣ ዶክተር ታዬ ወልደሰማያትና አበራ የማነአብ ወዘተ ... የመሳሰሉት የነፃነት አርበኞች በወያኔ/ሻዕቢያ ወህኒ ቤት የሚማቅቁት። ቁጥራቸው በወል የማይታወቅላቸውም በገጠርም በከተማም አንዳንዴም በግልጽ አለያም በድብቅ የጥይት እራት በመሆን የሚያልቁት።

ዛሬ ኢትዮጵያውያን ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ በሃቅ ለሃቅ የቆመ መንፈሳዊ አባት ከጎናቸው ቁሞ ለመከራ ሥጋ የዳረጋቸውን ሰይጣናዊ ሃል የሚገስጽላቸው እንደውኃ የተጠሙበት እንደ እንጀራ የተራቡበት ወቅት ነው። ዛሬ ኢትዮጵያውያን ለብዙ ሺህ ዘመናት ባምቻ በጋብቻ በአንድነትና በፍቅር እንደሰንሰለት ተሳስረው አንድነታቸውን፤ ሃይማኖታቸውንና ነፃነታቸውን ለመግፈፍ በየጊዜው የመጣውን የውጭ ጠላት በመከላከልና በማጥቃት የኖሩትን ህዝቦች አንድ አይደላችሁም ሁናችሁም አታውቁም፣ ያ ጎሳ ለዚህ ጎሳ ጠላት ነው ስለሆነም በክልል ተቆራርጣችሁ የክልሉን ድንበር አንተ ገፋኸኝ አንተ ገፋኸኝ በመባባል ለዘለዓለም ደም በመፋሰስ እንዲኖሩና የተረጋጋ የፖለቲካ፤ የምጣኔ ሀብትና ማህበራዊ ኑሮ ህይወታቸው ከረሃብ፣ ድንቁርናና ከበሽታ የሚላቀቁበትን መንገድ እንዳይፈልጉ እያዘጋጃቸው ያለውን ጸረ–አንድነትና ጸረ–ፍቅር የሆነውን የጎሳ ስራተ–መንግሥት ሃቀኛ የሃይማኖት አባቶች ያላቸውን መንፈሳዊ ስልጣን በመጠቀም በየመድረኩ ሁሉ ማውገዝ አለባቸው።

በአለባበስና በማዕረግ እነሱን መስለው በተግባር ግን አርዮሳውያን፣ ንስጥሮሳውያንና መቅዶንዮሳውያን የሆኑትን እንደ ጥንት የሃይማኖት አባቶች ከመካከላቸው እያወገዙ መለየት አለባቸው። የሰውን ልጆች ፍቅርና አንድነት ከመናድ የበለጠ መናፍቅነት የለምና። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ወደዚህ ዓለም መጥቶ በመስቀል ላይ እንደወንጀለኛ የተሰቀለው በሰው ልጆች ፍቅር አስገዳጅነት ነው። ፍቅሩም በአርያውና በአምሳሉ ለፈጠራቸው ለአለም ህዝቦች ሁሉ ነው እንጂ ለነጮች፣ ለጥቁሮች ወይም ለቢጫዎች አይደለም። “እንደ የኛው ፓትሪያርክ” ፍቅሩ ለአንድ ጎሳ ወይም ለአንድ ጎጥ ህዝብም አይደለም።

በህዝቦች መካከል አንድነት ከሌለ ፍቅር አይኖርም። ፍቅር ከሌለ መተሳሰብ፤ መረዳዳት፤ ርህራሄና መተዛዘን የተባሉት የጽድቅ ምክንያቶች ሙልጭ ብለው ይጠፉና በምትካቸው ቂም በቀልን፣ ጭካኔን፣ አብሮ አለመኖርን፣ አብሮ አለመብላትንና አለመጠጣትን እንዲሁም አብሮ አለመጸለይን በአጠቃላይ ለመንግስተ ሰማያት መግቢያ ብቁ የሚያደርጉት መልካም ስነምግባሮች ሁሉ ከእኛ ይጠፋሉ ማለት ነው። ለነዚህ አስከፊ ለሆኑ መንፈሳዊና ስጋዊ ጠንቆች ነው ዛሬ እኛ ኢትዮጵያውያን የተጋለጥነው።

ለመሆኑ ዛሬ በዚህ ባለንበት የስደት አገር ትግርኛ ቋንቋዋ ተናጋሪ የሆኑት መነኮሳትና ካህናት ከተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ወያኔ አገሪቱን ወሮ ለወራሪ ከሰጣት ወዲህ አብረው ይቀድሳሉ? አብረው ይጸልያሉ? መልሱ ሁላችንም እንደምናውቀው ያማ በመልካሙ ጊዜ ቀረ ነው። ይህን ሃቅ አንዳንድ አድርባዮች ባጥፊውና በተከላካዩ መካከል ከሚዋልሉ አስመሳይ ጻድቃን በስተቀር ምክንያቶቹ እነሱ መሆናቸውን ባይቀበሉም አባ ጳውሎስና ድርጅታቸው ወያኔ አይክዱትም።

“ከዚህ ከስደት አገር ያሉ ፖለቲከኛ ጳጳሳትና ካህናት እየከፋፈሉን ነው እንጂ አገር ቤትማ እንደዚህ ልዩነት የለም።» የሚሉን የሃሰት መስካሪዎችም አልጠፉም። ሃቁ ግን አገር ቤት በቤተክርስቲያን ውስጥ አንድነትና ሰላም ካለ ለምን እነባህታዊ ፈቃደ ሥላሴ በአባ ጳውሎስ የክብር ዘበኞች ጥይት በደጀሰላም ውስጥ ወደቁ? ሰላም ካለ ፓትሪያርክ ነኝ ባዩ ለምን እንደ ጥንቱ መቁዋሚያቸውን በሚይዙ ንጹሃን ደናግልና መነኮሳት እንደቅዱስ አባት መታጀብ ሲገባቸው የጦር መሳሪያ በታጠቁ ነብሰ ገዳዮች በቤተ መቅደስ ውስጥ ምን አሳጀባቸው? ወይስ መቁዋሚያቸውን ወደ ሽጉጥ፣ አጃቢ መነኮሳትን ወደ ነብሰ ገዳይነት የሚለውጥና ትምህርተ መስቀል የያዙ ባህታውያንን የሚያስገድል “የብጹዕነታቸው” ብቃት ነው ማለት ነው? ከተባለም የዚህ አይነቱ ብቃት የመንፈስ ርኩስ እንጂ የመንፈስ ቅዱስ አይደለም።

ዛሬ ምዕመናን እንደ አንድ ኢትዮጵያ ልጆች በማየት ፍርድ ጐደለባችሁ፣ ድሆች ተበደላችሁ ብሎ የሚያስተዳድር ምድራዊ መንግስት ብቻ ሳይሆን ያጡት የሰማያዊው መንግሥት እንደራሴ የሆነችውን ቤተክርስቲያን መሪም ጭምር ነው ያጡት። አባ ጳውሎስ የሲኖዶሱን መንፈሳዊ የቀኖና ህግ ጥሰው ሥጋውያኑ የጎጥ ወንድሞቻቸው እነመለስ መፈንቅለ መንግስት አድርገው ሃገረ-እግዝአብሄር ኢትዮጵያን በጎሳ ሰይፍ ቆራርጠው፤ በዘረኛ መርዝ መርዘው፤ አንዱ ካንዱ እንዳይገናኝ ጣሊያን በሰጣቸው ትሪኩ ዋላታ አጥር አጥረው፣ ለጥቂቶች ጥብቅና ቆመው ብዙሃኑን ረግጠው ይዘው አጆሃ ወዳደይ በሎ ቅተሎ ነዚ አድጊ ከሚሉት ጋር እጅና ጓንት ሆነው የጥንታዊት ቤተክርስቲናያችን ንዋየ ቅድሳት እየተመዘበሩ ለበላይ ጠባቂዎቻቸው ነሮች ቤተመዘክር(ሙዚየም) ማሸብረቂያ ሆነዋል። ላሊበላ ውስጥ ብቻ ከ23 የሚበልጡ ጥንታውያን የሆኑ ንዋየ ቅዱሳት ደብዛቸው እንደጠፋ መገለጡን ለምሳሌ መጥቀስ በቂ ነው። ስለዚህ ነሮች ራሳቸው ዘምተው ያልተሳካላቸውን ዛሬ በትውልድ ኢትዮጵያዊ በግብር ግን ሮማዊ የሆኑትን የፖለቲካውንና የመንፈሳዊውን አመራር አስጨብጠው ሁሉ በእጃቸው ሁሉ በደጃቸው ሁኗል።

የአባ ጳውሎስ የጎጥ ልጅ መለስ ከነሮች በተሰጠው ምክር መሰረት ኢትዮጵያን ለማጥፋት የግድ የአንድነት፣ የፍቅር፣ የሰላም፣ የአኩሪ ታሪክና የባህል አውታር የሆነችውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንን ማዳከም ከዚያም ጨርሶ ማጥፋት ስላለበት ለዚህ እርኩስ ዓላማ የሚተባበረውን ከጎሳው ብቻ ሳይሆን ከልዩ ጎጡና መንደሩ ከአድዋ የተወለደ፣ በፈረንጆች እውቅ ዩኒቨርስቲ የተማረና ለፈረንጆቹ ጥቅም አስጠባቂ ለመሆን ቀደም ብሎ ቃል የገባ፤ እንደሱ ጸረ-ኢትዮጵያ የሆነ፤ የሥላሴን በመለኮት አንድ መሆን እንደካደው ሁሉ የኢትዮጵያን አንድነትም የካደውን የቤተክርስቲያኒቱ መሪ ፓትሪያርክ እንዲሆን አድርጓል።

በትውልድም በግብርም ኢትዮጵያውያን የሆኑት የቤተክርስቲያኒቱ ልጆችማ ለዚህ ርካሽና አምላክ ብቻ ሳይሆን ታሪክ ይቅርታ ለማያደርጉለት የክህደት ተግባር እንደማይተባበሩ ስለታወቀ ከሃገረ ስብከታቸውና ከመንፈሳዊ አመራር ቦታቸው እንዲፈናቀሉና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ እንዲሰደዱ ተገደዋል። ታዲያ ይህ አይነቱ የክህደት ተግባር መወገዝ ይነሰው? የተሰደዱት አባቶች ብቻ ሳይሆኑ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን፤ የቤተክርስቲያኒቱ ካህናትና ምዕመናን ክፍለሃገር፣ ቁዋንቁዋና ጎጥ ሳይከልለን እንደ ጥንቱ አባቶቻችንና እናቶቻችን በአንድነት ተባብረን ይህን የጥፋት ሴራ የማክሸፍ መንፈሳዊና ታሪካዊ ግዴታ አለብን። አገራችሁንና ምንነታችሁን ለማዳን ተባበሩ የሚሉትን ሃቀኛ የሃይማኖት አባቶች ትምህርት ጠማማ ትርጉም ሳንሰጥ መቀበል አለብን። አገር ከሌለ ነዋሪ ህዝብ፣ ነዋሪ ህዝብ ከሌለ እምነተ እግዚአብሔር አይኖርምና።

ይህን የመሰለ ጸረ-ኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ጸረ ሃይማኖት የሆነ አመራር «ለእመይሰድዱክሙ ሁሩ ወጉዩ ውስተ ካለእታ ሃገር» መድኃኒታችን ክርስቶስ ባለው መሰረት ቅድስት ሃገራቸውን ጥለው በስደት የሚኖሩትን ጳጳሳት ቅዱስና ብጹእ ብላችሁ ህገወጡን ፓትሪያርክ መቀበል አለባችሁ የሚሉ አንዳንድ ከመሃል የሚንሳፈፉ በዚህ በአሜሪካ የሚኖሩ የቤተ ክህነት ሰዎች አልጠፉም። እነዚህ ሰዎች ከፋፋይነትን፣ ዘረኛነትን፣ አድሏዊነትን፣ ጎጠኛነትንና ቀኖና አፍራሽነትን የሚቃወሙትን አባቶች በተገላቢጦሽ ያዩአቸዋል። አጥፊዎቹን መገሰጽ ሲገባቸው ተከላካዩቹን ውስጥ ውስጡን አንዳንዴም በግልጽ ያጠቋቸዋል። በዚህ ጊዜ ምዕመናን ግራ ይጋባሉ፣ የሃቀኛ አባቶች መልእክት በምእመናን ዘንድ ቢቻል ጨርሶ እንዲነቀፍ ካልሆነም በጥርጣሬ መልክ እንዲታይና የመልእክቱ ገንቢነት ዋጋ ቢስ ሆኖ እንዲቀር ያደርጋሉ። የሲኖዶሱ መንፈሳዊ የቀኖና ህግን ማን እንደጣሰው እያወቁ እነዚህን አባቶች ሲኖዶስ የጣሱና አፈንጋጮች ይሏቸዋል። በነሱ አመለካከት የአባ ጳውሎስን አፍራሽ ተልእኮ ያልተቀበለ ሁሉ ከእናት ቤተክርስቲያን እንደተገነጠለ አድርገው ይመለከቱታል።

እጅግ የሚያሳዝነው ደግሞ መፈንቅለ ፓትሪያርክ የተካሄደባቸው አባትና ከዚህ ከእኛ ጋር በስደት የሚኖሩት አባቶች የአንድ ክፍለሃገር ሰዎች በመሆናቸው ነው እንጂ አባ ጳውሎስን የሚያወግዙት እውነት ለሃገርና ለቤተክርስቲያኒቱ ጥፋት ተቆርቁረው እንዳልሆነ እነዚህ ካህናትና የክህነት ሙያ አለን የሚሉ «ስደተኛ» ወገኖች ያስወራሉ። ልክ የእነዚህ አብቶች ክፍለሃገር ህዝብ ለኢትዮጵያ አንድነት ለብዙ ዘመናት ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ወገኖቹ ጋር በመተባበር ደሙን እንዳላፈሰሰ፣ ሊቃውንቱም ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ጥንካሬ አስተዋጽኦ እንዳላደረጉና በአጠቃላይ የቤተክርስቲያናችንና ቤተመንግሥታችን ኪነጥበብና ስነጥበብ ምንጮች እንዳልሆነ አድርገው በመቁጠር እንደጠበቡት ሳይሆን እንደጠባቡ ይመለከቱዋቸዋል።

በእውነቱ የዚህ ክፍለሃገር ህዝብ ከየት መጣችሁ? ጎሳችሁ፣ ጎጣችሁ ብሎ ሳይጠይቅ ከሁሉም ክፍለሃገር ከኤርትራም ጭምር የሚመጡትን መንፈሳዊ ተማሪዎች በየገጠሩ፣ በየአድባራቱና ገዳማቱ ሊቃውንቱን እየቀጠረ ድጉዋውን፣ ዜማውን፣ ቅኔውን፣ ብሉያቱንና አዲሳቱን የተማሪውንም የመምህሩንም ቀለብ በመቻል ዘመናዊ ትምህርት መጥቶ ይሄው ለዚህ እስከሚያደርሰን ጊዜ ድረስ ለቤተክህነቱ ብቻ ሳይሆን ለቤተመንግስቱም ታላላቅ መሪዎችን እንዳፈራ እነዚህ በጣት የሚቆጠሩ ራሳቸውን ጻድቅ ሌላውን ኃጥእ ከሚያደርጉ ግለሰቦች ወይም አባ ጳውሎስና ወያኔ ካልሆኑ በስተቀር መላው የኢትዮጵያ ህዝብ የማይክደው ሃቅ ነው።

እነዚህ ግለሰቦች በስደት የሚኖሩት አባቶችና የቤተክህነት ሰዎች ወያኔና አባ ጳውሎስ በሃገራችንና በቤተክርስቲያናችን ላይ እያደረሱት ያለውን ጥፋት ባንድ ድምፅ እንዳናወግዝ እንቅፋት እየሆኑ ነው።

ታሪክና እግዚአብሔር የጣለባቸውን አደራ በመወጣት ፈንታ አደራ በሌ በመሆን ሌሎች የሚያደርጉትን ተጋድሎ ያጥላሉ፤ ያደናቅፋሉ።

አንድ አባት «የቁዋሚ ምስክርነት» የሚል መጽሃፍ ቢጽፉ ስህተት ነው የሚሉትን ነጥብ ገጽ በገጽ ምዕራፍ በምዕራፍ እየጠቀሱ የነሱን አማራጭ ምስክርነት በማቅረብ ገንቢና ወንድማዊ በሆነ አቀራረብ እርማት በመስጠት ፈንታ ጸሃፊውን ብቻ ሳይሆን ከላይ እንደተገለጸው ከጸሃፊው ክፍለሃገር የተወለዱትን ጳጳሳት፣ ቀሳውስትና ዲያቆናት በጅምላ ተራ ስድብ በመሳደብና ስማቸውን በማጥፋት «መድፍን–ጸር» በሚል ርእስ የጠንቋይ ጽሁፍ እየጻፉ እንደሰላምታ ደብዳቤ በየአድራሻችን ይልኩልናል። እጅግ የሚያሳስፍር ነው።

ነገር ግን በእንዚህ አይሰሩ አያሰሩ ጥቂት ግለሰቦች የስም ማጥፋት ዘመቻ አደጋ ያንዣበበባትን ቤተክርስቲያንና አገር ለማዳን የሚያደርጉትን ገንቢ ጥረት አላቆሙም። ከምዕመናን ጋር በመሆን በየሰላማዊ ሰልፉ ወያኔንና አባ ጳውሎስን ለሚንከባከቡ ምድራዊ ሃያላን መንግስታት አቤቱታቸውን ከማሰማት ወደኋላ አላሉም፤ ማለትም አይገባቸውም። ምክንያቱም መንፈሳዊ አባት እንደመሆናቸው መጠን ከሁሉም የበለጠ ኃላፊነት አለባቸው። ክርስቶስ በዚህ ዓለም የእኛን ስጋ ለብሶ በነበረበት ጊዜ ከደጋፊዎቹና ከተከታዮቹ ይልቅ ተቃዋሚዎቹ በዝተው ለሞት አሳልፈው እንደሰጡት ሁሉ ዛሬም ሃቀኛ አባቶች የሁሉን ፍቅር እናገኛለን ብለው እውነትን ከመናገር መቆጠብ የለባቸውም። እውነትን በመመስከር የዘመኑን ሰማዕትነት (መስዋእትነት) በዘመኑ የክህደት መልክ መክፈል አለባቸው እንጂ።

የዛሬ አምባገነንና ከሃዲ መሪዎች እንደጥንቱ ለእኔና እኔ ለሰራሁት ጣኦት ካላመለካችሁ ትሰየፋላችሁ አይሉም። እንደዘመኑና እንደወቅቱ ያገዳደልና የጭቆና ዘዴያቸው ተቀይሮአል። እንኩዋንስ የዛሬ ሁለት ሺህ አመት የተካሄደው የግድያ ዘዴ ከመንግስት የግልጽ የቀይ ሽብር ርሸና የመለስ ድብቅ የጨለማ ሽብር ጭፍጨፋ ተለውጧል። ትንሽ ያልተለወጠው በአባ ጳውሎስ የባህታዊ ፈቃደ ስላሴ በመንግሥቱ አይነት ነጻ እርምጃ ያውም በቤተመቅደስ ውስጥ የዲያቆኑና በመጀመሪያው ሰማዕት እስጢፋኖስ የ1953ኛው የሰማዕትነት መታሰቢያ በአሉ ተከብሮ በሚውልበት ዕለት ነው ግድያው የተፈጸመው።

ጽሁፌን ለማጠቃለል የሃይማኖት አባቶች ከሁሉ የበለጠ የኢትዮጵያውያንን ህዝባዊና አገራዊ አንድነት ለመጠበቅ ከእግዚአብሔር የተረከቡት ከፍተኛ ኃላፊነት ስላላባቸው በእውነት ለእውነት ቆመው የህዝባቸውን በፍቅርና በወንድማማችነት ጸንቶ የኖረውን አንድነት ለመናድ ለውጭ ጠላት መሳሪያ የሆኑት የመለስንና የአባ ጳውሎስን ኀጢኛ፣ ዘረኛና ህግ አፍራሽ አገዛዝ አጥብቀው መኮነን አለባቸው። አባ ጳውሎስ፣ ሄሮድስና ሄሮዲያዳ ህግን በመጣስ ተመሳሳዮች ስለሆኑ መንፈሳውያን አባቶች እን መጥመቁ ዮሐንስ ለሄሮድስ የወንድምህን የፊልጶስን ሚሽት ሄሮዲያዳን ማግባት ህገ እግዚአብሔር አይፈቅድልህም ብሎ ስላወገዘው ህግ አፍራሾቹ ሄሮድስና ሄሮዳይዳ አንገቱን በሰይፍ ሰይፈው ስጋውን ሲገድሉ ነብሱ ግን በክብር በመለኮት አምላኩ፣ በስጋ ቅርብ ወንድሙ መድኃኒታችን ክርስቶስ ባዘጋጀለት መንግስተ ሰማያት ትኖራለች። (መጥመቁ ዮሃንስ የክርስቶስ እናት የድንግል ማርያም አክስት የኤልሳቤጥ ልጅ ነው)

ዛሬም በስደት የሚኖሩ የሃይማኖት አባቶች አባ ጳውሎስን የፓትሪያርኩ መንበር በሲኖዶስ ህግ የተመረጡት የወንድማቸው ሙሽራ ስለሆነች ሳይሞቱ በቁም መውረስ እንደማይገባቸው ቅዱስ ሲኖዶስ የከለከላቸው ስለሆነ ርእሰ ሊቃነ ጳጳስነታቸውን ወይም ፓትሪያርክነታቸውን አውግዘው ከሲኖዶሳቸው ማግለላቸው የመጥመቁ ዮሐንስን አርአያ መከተላቸው የሚያኮራ እንጂ የሚያሳፍር ስላልሆነ ካህናትና ምዕመናን የነዚህን ሀቀኛ መንፈሳውያን የሃይማኖት አባቶች አቁዋም ሳንከፋፈል በአንድነት ከልብ መደገፍ አለብን። ማህል ሰፋሪ የሆኑ ወገኖችም የእርምጃ እንቅፋት ከመሆን ይልቅ አገርንና ሃይማኖትን ለማዳን በሚደረገው ጥረት ተሳታፊዎች ቢሆኑ የተጋድሎውን መራራና ረጅም ጉዞ ሊያሳጥረው ይችላል። በሃገርና በሃይማኖት ጥፋት እየተፈጸመ ተቃውሞ አለማሰማት የጥፋቱ ደጋፊ መሆናችንን ማወቅ አለብን። እግዚአብሔርና ታሪክም በደላችንን ይቅር እንደማይሉት ተረድተን የጥፋት መንስኤዎችን ሁሉ መቃወም እንጅ ተከላካዮችን አናደናቅፍ።

አግርር ጸራ ታህተ እገሪሃ፤ እቀብ ህዝባ ወካህናቲሃ ለሃገሪትነ ኢትዮጵያ (እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፣ የሀገራችን የኢትዮጵያን ጠላቶች ከጫማዋ እግር ስር ጣላቸው! ህዝብዋንና ካህናትዋን ለዘለአለም ጠብቅ አሜን።)

ከበደ አገኘሁ – ከፖርትላንድ ኦሬገን

## ፀሐይምሸት

(ከገፅ 31 የዞረ)

"ፀሀፊዬ ታስታውቪኛለሽ ።"

በንዴት ተስፈንጥራ ገብታ "'ጎጆ ለማረፊያ እንጂ ለመዋያ አልተገነባም ። ሳድርበት እመጣለሁ ። ወንድ ኦሮው ባደባቢይ ነው'እያልክ ሲነጋ መሹለኩ አንገሽግሾኛል ።" ስትል እንደ ብራቅ ጮኸችበት ።

"አቤት ወንዶች ስትባሉ አንድ ናችሁ ልበል?" ብሳው ከመድረኩ በሚደርሰው የብርሃን ፍንጣቂ የድጋፌን ፊት ለማየት ሞከረች ።

"የ'ግዜር ፈቃዱ ሆኖ አዎን!" ሲል መለሰላት ። ሸዋ'ነሰሽ ከት ብላ ሳቀችበት ።

"ነገሬን ጌሾ አበዛሽበት ። አመረርሽው፤ አሳከርሽው!" ሲል ህሊና ተማረረ ።

"ወጥተህ እስከምትመለስ ምን ያህል እንደምጨነቅ ታውቃለህ?" ስትል ፀሐይምሸት ጠየቀችው ።

"እምን እውቃለሁ ። አሁን እንቅልፍ እየነሳኝ ነው !" ሲል ተሳለቀባት ።

ሳንባዋ በንዴት አየር ተወጥሮ ስትተነፍሰው ውቃቢ እን ደለቀቀው ሰው ያናፋ ነበር ። ከተንጋለለበት ቁልቁል እያየችው አዘነችበት ። በዕውን ዓለም የሚኖር መስሎ አልታይሽ አላት ። ወንዶች ሲባሉ ፍቅራቸውን የት ነው የሚደብቁት ። የጉልበት፣ የሥልጣን፣ የማን አለብኝነትና ከማን አንሼ ለምን ያጠቃቸዋል? በቤታቸው ያለውን ትተው የአደባባዩ የሚበልጥባቸው ለምን ድነው? ስትል አሰበች ። ብዙ ጊዜ እነዚህን ጥያቄዎች አብላልታቻቸዋለች ። አሁንም እንቆቅልሽ እንደሆኑባት አሉ ።

"ድንግልናዬን ያስወሰድኩ ጊዜ እንኳን ተደፈርኩኝ ብዬ አላዘንኩም ። ምክንያቱም እኮራበት የነበረ ወንድ ነበር የወሰደው" ብላው የሚለውን ለመስማት ቆም አለች ።

ክብሯን የወሰደባትም ወንድ እንዲሁ ትምክተኛ ነበርን ። የኃይለ ሥላሴን አመራር በመ ቃወም ግብር አልገብርም በማለት ጥቂት አጋሮቹን ይዞ ከሸፈተ በኋላ የበረሃ ህመም ይዞት ነበር ። ሕይወቱን ለማዳን አጋሮቹ ምጎረት እንጠይቅና እጃችን ን እንስጥ ቢሉት 'ህያው ነኝ ብዬ ትግሌን አልጀመርኩም ። ያገሬ ልጅ ኑሮው ሳይስተካከል እኔ ሞቴ አይበልጥብኝም' ብሎ አሻፈረኝ አለ ። በነጭ ለባሾች ጥቆማ ካለበት ተደርሶበት ከጮሎሚት ማርያም ሸለቆ ውስጥ ውጊያ ሲገጥሙት ጥይት እየጎረሰ ጉሮሮው በሚዘጋ እርጌ ጠመንጃ አዝማቹን መቶ አለቃ ንጥሎ ገድሎ ካመለጠ በኋላ ያገሬ ልጆች የሚላቸው ወዳጅ መስል ጠላቶቹ ሸምቀው ይጠብቁት ስለነበር እነሱን ብሎ ሲቀርባቸው ተኩሰው ገደሉት ። ምጣም ወንድ አጥታ አለቀሰች ። የጀግና ሚስት እየተባለች ከምትኖርበት አገሯ ያበረራት ጀግንነቱን ብቻ ሳይሆን ፍቅሩን የሚተካ ወንድ አግኝታ ለመኖር ባለመቻሏ ነበር ።

"ልቤን ግን አንተ ወስድከው ። ሆኖም አሁን ሌላ ወን ድ እየደፈረው ነው ።" ስትል ብሶቷን አሰማች ።

"ዛሬ ሌሊት ሰፊ ታሪክ አለሽ ።" አላት ለመስማት ያልተዘጋጀ መሆኑን በአካሉ እየገለፀ ።

"የጓደኛህን በደል ከአሁን ወዲያ ልቀበለው አልችልም ።"

ወደ በሩ እየተመለከተ "እይምሮ!" አላት በጥርጣሬ ይሁን በመ ደነቅ መልክ ልዩነቱ ባልታወቀ አባባል ። "ምንድነው በደሉ? ገና መተዋወቅ ከጀመርን ጀምሮ ነው ትጠይው የነበርነ ። አሁን ምን አደረገሽ?" ህሊና በሃሳብ እንደተያዘ ሰው ከበሩ ላይ ዐይኖቹን ሲተክላቸው መብራቱ ቀስ እያለ መጥፋት ጀመረ ።

* * *

አምባር የመ ድረኩን የመሃከል መብራት እንዳጨለመ የሃሳብ ሽግግር ትርዒት ለማሳየት እጆቹ በቅልጥፍና የሚቀጥለውን ብርሃን በተወሰነለት ወቅት ውስጥ ማብራቱን ጀመረ ። ከተቀጠለው መድረክ ላይ በደብዛዛነት የጀመረው መብራት እዕምሮን ከጥላማነት አጥርቶ በማውጣት ጠቅላላ አቋሙን ሲያሳይ በፅላል የሚያየውን በር ሲያንኳኳ ይታያል ። በጥበቃ የተሰላቸው ወረጋ የድምፅ መቆጣጠሪያውን ሲከፍተው ያልጠበቀው ድምፅ ስላሰማው ተደናግጦ በፍጥነት አጠፋው ። የበር መንኳኳቱን ድምፅ በወቅቱ አስመስሎ ለማሰማት ባለመቻሉ እየተበሳጨ የድምፅ ማዳመጫውን ከእናቱ ላይ ሰክቶ የሚቀጥለውን የድምፅ ጥሪ ያስተካክል ገባ ።

ፀሐይምሽት በብርሃኑ በመመራትና የእዕምሮን የበር መምታት የትይይዩ ጥሪ ተከትላ ሄዳ በሩን ትከፍትለታል ።

"እይምሮ! ህሊና አሁን ወጣ አልተያያችሁም?" አለች ፀሐይምሽት እዕምሮን አይታው በመገረምን ይመጣል ብላ አልጠበቀችውም ነበር ።

"ባልሽም ካንቺ ወስዶ ስሜን ያጠፋዋልን" ፀሐይምሽት በመ ደንገጥ አየችው ። ምን ሰምቶ ነው? ስትልም ግራ በተጋባ አስተያየት አየችው ። "እይምሮ ማለት እኮ የማይምር ማለት ነው ። ትክክለኛው ስሜ እዕምሮ ነው ። ሆኖም አመጣጤ አንቺው ጋ ስለሆነ አጣሁት ብዬ አላማርርም ።" ብሎ አስረዳት ።

"የስም አጠራር ስህተቱ ይታረማል ። እኔም አሁን ልወጣ ነበር ።"

"የምትወጂውን ጅን ይዤልሽ ነው የመጣሁት ።"

"ጅኑ ራሱ መጣ አትለኝም !" አለችው የቀልድ አስመስላ ። "እኔ አረቄ ነው የምወደው ።"

ፋታም አልሰጣትም ። ለመመለስ ፊቱን እያዞረ "ሂጄ ልቀይረው እችላለሁ ።" አላት ።

"ግድ የለም አትጨነቅ ።"

"ልቤን እንደዚህ አርጊልኝ እንጂ ። ሳይሽ ልቤ እርግፍ ነው የሚለው ።" ልቡ በደስታ ፈካ ።

"ባትመጣ አታየኝም ነበር ።"

"ባላይሽም አስብሻለሁ ።"

*"አይ ወንድ! ይህን ጊዜ ሚስቱን ከቤቱ አስቀምጦ ይሆናል" አለችና ጥልቅ አለች ሸዋ'ነሰሽ ።*

*"ባይገርምሽ እኮ የጓደኛው ሚስት ነች እኮ !" በማለት ድጋፌ አጋነነላት ።*

"ባለቤትህ የልብ ጓደኛዬ ነች ።" አለችው ረጋ ብላ፤ ከረጅም ጊዜ በፊት የተዘጋጀችበትን ምክንያት በሚያሳምን ሁኔታ ።

"መወደድሽን ለምን ትጠይዋለሽ?" አላት ሃሳቧን የምትቀይር መስሎት እንዳትሸሽበት በመስጋት ።

"ባለቤቴ የልብ ጓደኝህ ነው ። እኔም እንደ ወንድም ነው የምወድህ ።"

"ካንቺ ፍቅር እንዳይዘኝ ባልሽም ሚስቴም እኔም እን ቺም እንችልምን እግዜሩም አይችልም ። በፍቅርሽ ሰምት ዝም ብለሽ አታይኝም ።"

*"ጉድ ነው እኮ! ምን ዓይነቱን እፍ ሰጥቶታል!" አለች ብሽቅ፣ ንድድ፣ ድብን ብላ ሸዋ'ነሰሽ ። ተነስታ ሄዳ ከመድረኩ ላይ አውርዳ ብታደባየው ደስ ባላት ነበር ።*

"እመንዝራነት በመፅሀፍ የተከለከለ ነው ።" ኃጢአት መግባት እንደማትፈቅድና እሱም ቢቀርበት እንደሚሻለው ለመጠቆም ነበር ፀሐይምሽት ይህንን ያለችው ።

"ፍቅር ግን አይከለከልም ።"

*"ነፍስህን አይማረው እቴ! ኃጢአት የምታስገባት!" ሸዋ'ነሰች ነበረች ያርጎመጎመችው ።*

እግዜሩን የማይፈራና ለነፍሱ ደንታ የሌለው ምንም ቢሆን እንደማይለቃት ታውቃለች ። ሆኖም ሳታስቀይመው የሚገጥመውን ችግር እንዲያውቀው ለመግለፅ ግን ፈለገች ። "ባለቤትህ ብትሰማስ፤ ባለቤቴ ቢመጣስ?" ለማስጋትና ለማስፈራራት ነበር ።

"ለፍቅርሽ እሞታለሁ ።" ሲላት እንዳች ነገር ጉሮሮዋን ተናነቃት ።

"ፍቅር አይገድልህም አትስጋ ። ፍቅር ቢገድል እኔ

በባሌ ፍቅር እሞት ነበር።"

"መቃብር ሳይውጠኝ በፊት ለልቤ ደስታ ስምን ትከለክይኛለሽ!"

"ቁጭ በል። ይህንን ችግር ዛሬውኑ መፍታት ይኖርብናል። ከረባትህን ደግሞ አላላው። የምን መወጠር ነው።" በማለት አዝናናችው። እየተንጠራራ ከረባቱን አላልቶ ከሶፋው ላይ ያቀመጣል። ፀሐይምሸት ከጓዳ ገብታ እስከምትወጣ ድረስ *"ልቤ ቢቀርበት ምነው"* የሚለው የጥላሁንን ዘፈን ወረጋ ከፍቶት ስለነበር መስማት ጀምሯልነ ፀሐይምሸት ሁለት እኩል የሆኑ ብርጭቆዎች ይዛ ትመለሳለች።

"እኔና አንተ እዚህ ደረጃ ላይ መድረስ አይኖርብንም ነበር።" አለችው ፀሐይምሸት።

የአባባሏ ትርጉም አልተገለፀለትም። ግን መስመር ለማስያዝ ሲል "ለፍቅር ነው እንጂ ለጠብ አልሞትኩም።" በማለት ፈገግ አለ።

"እግዜሩም ነፍሳችንን አይምረውም።"

ዛሬስ ላገኛት ነው የሚል ውስጣዊ ሽብር ይዞታል። "'ፅድቅና ኩነኔ ቢኖርም ባይኖርም እኔ ላንቺ አልኖርም' ሲባል አልሰማሽም።"

"ለምን ጥቂት ቀናት ወስደህ አታስብበትም።"

"ለቀበሌ ምርጫ እየተዘጋጀሁ ነኝ። ሃሳብ ናላዬን አዙሮታል። ከአንቺ ዘንድ መሆኑ ትንሽ ይቀልልኛል።"

"ትንሽ ብቻ" አለችው በለበጣ።

"ማለቴን ስላንቺ ማሰቡም ያው ችግሬ ነው። እን ዲያው መላ ካላልሺኝ በቀር የሚበጀኝን አላውቅም።"

"የሚጠጣውን አትቀዳልኝም ታዲያ!" ይቀዳላታል። "ሙላው፣ ሙላው የምን ስስት ነው? እስከ አፉ ድረስ ሙላው።" ፉት ብላ ታጣጥመዋለች። "ምን ይመስልሃል?"

የተሞላውን ብርጭቆ ሰጥታው ጠርሙሱን ትቀበለዋለች። ሊጠጣ ሲል ስታስቆመው ብርጭቆውን ከፍ አድርጎ "ይቅርታ ለጤናችን!" ይላታል።

"አንዲት ጠብታ ሳትፈስስ ከዚህ ብርጭቆ ውስጥ ገልብጠው።" ስትል አዘዘችው። መገልበጡን ካየች በኋላ "ምን ልዩነት አየህበት?" አለችው።

"ምንም!"

"ባዶው ብርጭቆ ሙሉ ነበር። የተቀዳውም ለእኔ ነበር አይደለም?"

"አዎን።"

"ባዶ የነበረው ብርጭቆ ደግሞ ሙሉ የነበረውን መጠን ያህል እንዳለው አየን። ስለዚህ በ'ኔና በባለቤትህ መካከል ምንም ልዩነት የለምነ ከ'ኔ የምትጠብቀውን ከባለቤትህ ማግኘት ትችላለህ።"

*ሸዋ'ነሰሽ ቆንጥንጥ አለች። አይ ልብ፣ አይ ችሎታ፣ ወይ ብልሃት ስትል በውስጧ ተደሰተች።*

"አባባልሽ ግሩም ነው። ግን ላንቺ ያለኝን ፍቅር ወዴት ትገለብጭዋለሽ?"

"የማልሰጥህን ፍቅር ነው የምትጠይቀኝ። ፍቅር የለኝም።"

አዕምሮ መጠጡን ከጠረጴዛ ላይ አስቀምጦ ለመውጣት ይቃጣውና ይመለሳል።

"ፍፁም ቅር አትሰኝ። አንተ እንደምታስበው አልጠላህም። እርግጥ እወድሃለሁ። ግን በወንድምነት ነው። የአልጋ ዝምድና ፍላጎት የለኝም።"

ተንደርድሮ ሂዶ ያቅፉትና ለመሳም ይታገላል። ከሶፋው ላይ ትወድቃለች። ከላይዋ ላይ ገና እንዳቅፈባት ህሊና እየዘፈነ ሲመጣ ይሰማል። በድንጋጤ ተውጦ ከሶፋው ላይ ይቀመጣል። እርሷም ከዳር ላይ ትቀመጣለች።

"ይቅርታ አድርጊልኝ።" አላት በር በሩን እየተመለከተ። "ደግሞም እንዳትነግሪው።" በልመና አስተያየት እያስተዋላት ነበር።

"ከማልነግረበት ደረጃ አሳልፈኸኛል።" አለችው ንዴት በተሞላው ሆኖም ራሷን በመቆጣጠር።

"ምን ብለሽ ትነግሪዋለሽ?"

"ያደረግሽኝን ሁሉ።"

"ምን ብለሽ?"

"ልትደፍረኝ መታገልህን፤ ጡቶቼ እስኪፈርጡ መቦጨቅህንና የ'ርሱን ድምፅ ስትሰማ እንደለቀቅኸኝ እነግረዋለሁ።" የህሊናን መምጣት ሁለቱም እየተጠባበቁ ነበር። ህሊና ግን ድምፁ ከመሰማቱ በስተቀር ብቅም አላለም።

"ሁለተኛ አይደግመኝም። የዛሬን ብቻ ማሪኝ!"

"ወንድምነትህን የጣድክ ስለሆንክ ይቅርታ የለኝም።" ስትል ቁርጠኛነቷን አሳወቀችው። ልቧ ግን አንቺ ፊት ሰጥተሽው ነው እንጂ የእኔ ጓደኛ ይህንን አያደርግም እንደሚላት ጠረጠረች።

"እሽሽ... ቀስ ብለሽ ተናገሪ።" ድምጿን ዝቅ እን ድታደርግ ተማጠናት። ለጥቂት ጊዜያትም በመካከላቸው ፀጥታ ሰፈነ። "ያዳምጠን ይሆን?" በስጋት ነበር የጠየቃት።

"ባያዳምጠንስ እኔ መናገሬ ይቀራል።"

"ንገሪው። በማን እንደሚብስ ይታያል። ጠርተሽ እንዳስቸገርሺኝ ብነግረው ካንቺ ይልቅ እኔ ተደማጭነት አለኝ።" የጠረጠረችውን ያሰበ ይመስላል። አዎን ከመጠጥ ቤት ቁጭ ብለው እየጋበዘው ቢወሻከትለት ሊያምነውና ችግሩ በእርሷ ላይ ሊብስ ይችላል። አዕምሮ ተነስቶ ሊወጣ ሲል ህሊና ከበር ላይ ይገናኘውና ጎትቶት ይገባል። ህሊና እየዘፈነ ነው።

'እውነት፣ እውነት ነው የከዳች፣ ሃቅ አልለቅም ብላ
ሃሰትን አታውቅም፣ አታውቅም፣ ምንም ብትጉላላ....'

እውነት! እውነት ብትከዳ ምን ትሆናለች? በሉ እንጂ እንዳችሁ መልሱልኝ። ምን ድንጋይ ይመስል ትዘጋላችሁ። እውነት፤ እውነት እውነትን ስትከዳ ሃሰት ትሆናለች። ግን፣ ግን፣ ግን... ሃሰትን ስለማታምንበት ጊዜዋን ጠብቃ ስታጋልጠው እውነት ትሆናለች። ምን የአደባባይ ፀሀይ ያጠወለገው ሰልፈኛ ይመስል ደንዝዛችሁ ታዩኛላችሁ። አዎን አብድ ነው፣ ቀውስ ነው፣ የዓለም ነገር የማይገባው ነው ትሉኝ ይሆናል። አልቃወማችሁም። ምክንያቱም መብታችሁ ነው። ለመናገር እንደበታችሁ የተያዘ፣ ልሳናችሁ የተዘጋ፣ አዕምሮአችሁ የነገር ድር ያለቀበት፣ ብሎም... ነፃነታችሁ ነው። ስለዚህ እኔ አልወስድባችሁም። እውነትና ሃሰት በሚለው ግን እከርሬ እከራከራችኋለሁ። ምክንያቱም የዲሞክራሲያ ውልድ ነኝ። ትርፉ ጉሮሮ ማድረቅ ነው።" የተቀዳውን ጅን አንስቶ ሊጨልጥ ሲል አዕምሮ እጁን ለቀም ያደርገውና ፈገግ ይላል። የመጠጡን ዓይነት እንዳይቀምስበት ለመደበቅ። የአረቄ ሽታ እንደሆነ ጉንፋን የያዘው አፍንጫም እንኳን ይለየዋል። ተቀብሎት "እሷ የእኔይቱ መጠጥ ነች።" ብሎ በመጨለጥ መቃጠሉ እንዳይታወቅበት ይሞክራል።

*ሸዋ'ነሰሽ ህሊና ሽጉጥ በእጁ ይዞ ሲያሸምነሙን ስታይ የባሏን ክንድ ጠበቅ አድርጋ ያዘች "ወየው እሷንም እንዳይገድላት። ምን ዓይነት ጣሰኛው ነው ያጋጠማት!" አለችው።*

(ወደ ገፅ 41 ይዞራል።)

# የግጥም ጉባኤ

## አዲሳባ ፊሽካ ንፊ!

ከልሳኑ ስምረት (ሲንትሉዊስ ሚዙሪ)

የትዝታ መሪ ልቤ ... የውስጥ ደም ሕዋስ መቅኔ
የኅብለ–ሠረሠር አጥንቴ ... መደገፊያ ሚዛኔ
የዕጢ ፈሳሽ ቅመሜ ... የመለኪያ የምጥኔ
የጥቁር መናገሻ ... አዲሳባ ተገኔ
ወንድ ውለጂ መዲናዬ ... ምጥሽ ይጥና ፍንፍኔ
የሰቀቀን ገበናዬ ... የትብት ዓርማ ከፈኔ።
ዛሬ ደርቀሽ ተኮስምነሽ ... ወዘናሽ ተሚጦብሽ፣
የስንቱ ደም ፈሰሰብሽ ... ሥንቱ ቤትም ተዘጋብሽ።

የምስኪኑ የምሑሩ ... ያቀባባይ የዶፍቶሩ
የቸርቻሪ የጉሊቱ ... የግሪክ ሱቅ የቱጃሩ
የወያኔ የአርመኑ ... የመክሊቱ የዶላሩ
የጠባቡ የተማሪው ... የጥራዝ ነጠቅ የነብሩ
የምንተስኖት የጆቤሳ ... የነኃይሉም የነገብሩ
የሻቢያም የጅቡም ... የድኩላው የነብሩ
የፌንጣው የቁንጫው ... የመስኪዱ የደብሩ።
አዲሳባ ውቀሺያቸው ... የማይሆን ነው በያቸው
ሕዝቦችሽን ርገሚያቸው ... ካልሰሙሽም ገኸቻቸው
አቆላልፈሽ አያይዘሽ ... እናት ሆነሽ ንገሪያቸው።
ፒያሳን ከቀበና ... አገናኝው ከመርካቶ
ሰንዳፋን ከጌጃ–ሠፈር ... ወጣቱን ከሽበቶ፤
እንጦጦን ከወሰርቢ ... ጫንጮን ከአሥመራ መንገድ
አፍንጮ በርን ከኮልፌ ... ጫቱን ከባህር–ዛፍ ግንድ
ሳሪስን ከጃንሜዳ ... መሿለኪያን ካንዋር መስጊድ
ዐቴቴን ከደመላሽ ... አባን ከኡስታዝ ፋዐድ
ሻለቃን ከኮሚሳር ... መነኩሴውን ከበጅሮንድ።
አገናኝው አራት ኪሎን ... ከጌቶ እሪ–በከንቱ
ብሔረ–ፅጌን ከቦሌ ... ጉጃም በረንዳን ከቢሾፍቱ፤
ጉላ ሠፈርን ከሠንጋ ቤት ... ቁጭራን ከቀጨኔ በር
ሞጃ መትን ከለጋሲዮን ... እህል በረንዳን ከለገሀር
ቸርችል ጉዳናን ከራጉዔል ... ኮተቤን ከትግሬ መንደር
ካዛንችስን ከጊዮርጊስ ... ሶማሌ ተራን ከኛ መንደር።

አዲሳባ ምከሪያቸው ... ለኛ አይሆንም በያቸው
የሥምረት ፅጌረዳን ... አንድነትን አውጊላቸው
የክልልን የግንጥል ጌጥ ... አስረግጠሽ ንገሪያቸው፤
እሪ ብለሽ ማቅ ደርበሽ ... እርም አውጥተሽ ቅበሪያቸው
የወላድ መሐን ሆነሽ ... ሙሾ አውርጂላቸው
አልቅሰሽም ይቅር ብለሽ ... ሥጋቸውን ገንዢያቸው።
አመፅ ስበሽ ተነዋውጠሽ ... በታሪክሽ አንጂያቸው፣
እንደሌሎች «መካን» ሆነሽ ... ካልቃሾች ጋር ተሰለፊ
ቃልሽ እንዲያስተጋባ ... ጮክ ብለሽ ለፍፊ
የሰማው እንዲሰማ ... እብድም ሆነሽ ለፍልፊ፤
አሳውጀሽ አዋጅሽን ... የደበሎ ቅዳጅሽን፣
ጠጉር ነጭተሽ ከል አጥልቀሽ ... በወረቀት ላይም ጣፊ
አዲሳባ ሕንፃዬ፣ በሰው ክፋት አትገፊ
ዋይ ዋይ ብለሽ ደረት መተሽ ... ዓይንሽ ፈርሶ ተከፊ።
በአኮርባጅ ተገርፈሽ ... «ለማ ስበቅታኒን» ገጥመሽ፣
አንብተሽው ወጥቶልሽ ... ጡቶችሽን አራግፊ
ጉንጭሽ ለፍቶ ሲልሽ ሟምቶ ...ተሰቃይተሽ ፊሽካ ንፊ!!

## የታሪክ ገለባ (ሠላይ ባፍንጮ በር)

ከሐዲስ ተገኝ ዳላስ/ቴክሳስ

ለማፍረሱማ ምስጥም ... ወጠፍ ኩይሳ ይንዳል
ግን ጠንካራ አለት መሰረትን ... ማናጋት እኮ ይሳነዋል።
ምስጥም እኮ ብልኅ ነው ... እንደሰውም ያስባል
በሳል እንጨቱን አማርጦ ... ረጋ ሰራሹን ይጠጋል።
እንዲያው ለታሪኩማ ... መርጦ መራርጦ ይልሳል
ለደነደነውማ ዋርካ ... በክብደቱ ብቻ ይርዳል
ሕያውነቱን ያውቃል
የተያያዘውን ኪሪስታል ... ገና ሲያየው ይፈራል
በሚተፋው ፈሳሽ መርዝ ... ራሱን መልሶ ይገላል።
ደግሞም እሳት ለኩሶ ... ከድንጋይ ጋር ይጋጫል
እንደጥንቱ ዘመን ጠጣ ... በወላፈኑ ይጋያል
መኖሪያ ጭዱን ለኩሶ ... ባመጣው ነገር ይከስማል።
የገለባ እሳት እየመዘዘ ... ለማቃጠል ለዋለውማ
በጭሱ ግለት ታብቆ ... ትንፋሽ ሳጠረውማ
እሾህ ለሰሪው ሆነና ... የሚሉትን ሳልሰማ
እዚያም ቤት እሳት አለ ... ወደል ምጣድ የሚያሰማ
በኃይሉ ብርቱ የሆነ ... የሚቦረቅስ የሚያደማ።
ሁሉን አቀፍ ቢሆን እንኳ ... ግዴታና መብት ቢኖረው
ሕጉና ደንቡ ሒደቱ ... ስብስቡ የተዋቀረው
ደጀ ሰላሙና መንበሩ ... ታቦቱ የተከበረው
ቤተእግዜርም ያምፃል... በበታኝ ላይና በሥራው፤
በዘረኛ የክርታስ ፍም ... በግለቱ ላላበውማ
የኖረበትን የወንዝ ዛፍ ... «አጓጉል ለናቀውማ»
ገሃድ ይሁን አለሌነቱ ... ስብቀቱ ሁሉ ይሰማ።
ገለባ እየለኮሰ ... «አርሰኒስት» ነኝ ለሚለው
ይህም መልካም ሥራ ሆኖ ... በሰይጣንነቱ ላበጠው፤
የለም እናንተ እርሱማ ... የያዘው እብሊስ ጋኔን ነው
የወያኔ ሰላይ እንዝርት ... አሳዳሪው ሌላ ነው።
ለዚህማ የኛ ነዳጅ ... ከፋይ ፍም የምንለው
ለማፍረስ ለመጣውማ ... እርሱ የባሰ ገዳይ ነው
እንደእሳት ሠርጉ ገብቶ ... የራሱን ቅል የሚያጋየው
አንጉሉን አኮማትሮ ... አክለፍልፎ የሚጠብሰው
አስጭሆ ቀጁል ወቀጁል ... መስተፋቅርት ላይኖረው
የሚመክበት ጉሰኛ ... ሳይደርስበት በፊናው።
ምቀኝነት አብሰልስሎት ... በቅናት ዛር ለሚናጠው
እስከሌሊት አራት ሰዓት ... በስልክ ሽቦ ለሚሰክረው
ምድር ጠቦት ሰማይ ርቆት ... ነፍሱን ሰላም ለሚነሳው፤
ላንዱ ሌላ ለዚህ ሌላ ... ለወያኔም ለርሱ ነገር
ለሻቢያም ገሌ መሌ ... ውሸት በውሸት ሲያሳርር
ላገር ወዳድ ያገር ነገር ... ለዶክተሩ ኪኒን ስፍር
ለቡኩኑ የቃል ተስፋ ... ለአማኙ የመስቀል በር፤
ለዘር ጅማት ካልቾ መርፌ ... ወዲያውኑ የሚያስነዝር
ተቀባዩን የሚያስገምት ... በሐቅ ፊት የሚያስወግር፤
ለጴንጤውም ሰላም ነገር ... የሱስ የሱስ የሚያናግር
ምን ዓይነቱ ኃጢአተኛ ... ፈጣሪን የሚያስመርር
ራሱ እባብ የሚመስል ... እንደኮብራ የሚዘረር።
ለዚህማ የኛ ነዳጅ ... ከፋይ ፍም የምንለው
ለማፍረስ ለመጣውማ ... እርሱ የባሰ ገዳይ ነው፤
እንደ እሳት ሠርጉ ገብቶ ... የራሱን ቅል የሚያጋየው
አንጉሉን አኮማትሮ ... አክለፍልፎ የሚጠብሰው
አስጭሆ ቀጁል ወቀጁል ... መስተፋቅርት ላይኖረው
የሚመካበት ጉሰኛ ... ሳይደርስበት በፊናው።

—— // ——

## ደብዬ በእሥር ቤት

ተራ ጭቆናን የጨቆንክ ... ፍትሕ በጐደለበት ምድር
አንተ የእውነት አባት ... ጠላትህን የምታሳፍር
ቅጥረኞች ቢያዋርዱህ ... ቅስምህ የማይሰበር፤

የለም ስላንተ ያስባሉ ... ሰሞኑን እንቅልፍ አጥተዋል
ግዞት ቤትህ ቢጣበብ ... ተስፋህ ሰንጥቆ ወጥቷል
እግረ ሙቁን ሰባብሮ ... ከዚያች ክፍል አርጓል
መጭውን ድል ተመልክቶ ... ልብህ በሩን ከፍቶታል።

[Miriam Allen De Ford, Debs & The Poets, Upton Sinclair, 1920 Page 24]
(ውርስና ተዛምዶአዊ ትርጉም – ልሳኑ ስምረት፤ ትርጓሜ – ለነፕሮፌሰር አሥራት፣ ዶክተር ታዬ ወልደሰማያት፣ ለነስጦታው፣ በለጠ፣ ፀጋዬና ሌሎችም መታሰቢያ ይሁን)

—— // ——

## ወኔ

(ከዶክተር ፍቅሬ ቶለሳ)

አቅሉን የሳተ አንድ ዕብድ በጦረኞች ታጅቦ
በሥልጣንና በዝና ብዛት ጠግቦ
አንዱን ጉበዝ ሲያዋርደው እየተፋበት ደብድቦ
ጉበዙ ልጆቹን ሊያሳድግ እናቱን ሊጦር አስቦ
ፀጥ ብሎ ቢሰደብ አውቆ ቢረገጥለት
ለድንፋተኛ ዕብዱ
እንዴት ወኔ የለውም ትሉታላችሁ
ለሌሎች ሲል በመዋረዱ?
ቦቅቧቃውስ ጥጋበኛው ዕብድ ነው
አጀብ ባይኖረው ወኔ የሌለው
ላንድ ለራሱ ብቻ ስለሚኖር
ቢገል ቢገደል ደንታ የሌለው
ሥልጣኑን አጀቡን ቢነጠቅ መሬት ዋጭኝ የሚለው።

—— // ——

## ብረሳሽ ይሻላል!!

(መ.ገ.)

እመጣለሁ ብለሽ
ስትቀሪ ቅር ይላል
አልመጣምም ብለሽ
ስትመጪ ይገርማል
ግራ የገባሽ ሆነሽ
ግራ አጋብተሽኛል
እንግዲህ ብተውሽ
ብረሳሽ ይሻላል።

—— // ——

## መሪዬን ያያችሁ!

ከአገኘሁ እንግዳ (አዲስ አበባ)

ብርሃን በሌለበት፣
የአይኔ ማዕረግ ውሉ በጠፋበት።
ድሮ መንገድ የሚመራኝ፣
ዛሬ ሲጠፋ ጥሎኝ።
የእንግልት የመከራ እርምጃዬ፣
በእንቅፋት የታጀበው ጉዞዬ።
በበትር ዳሰሳ ስፈልግ ዓለምን፣
ብሻ የብልጭት ውጋገን።
ፅልመት ሆነ ያለ መሪ፣
ምድረ ገነት ለእኔ አስቸጋሪ።
ብትሆንም ብሌን፤ ወርቅ
በመሪ ... መንገዱ ሁሉ ይደምቅ።
ዘመን ከዘመን አሸጋግሮኝ፣
የዕይታ ዕድሉ ቢያመልጠኝ፣
አልተቀጨሁ አልከፋኝ።
ብቻ አንድ ነገር ልጠይቃችሁ፣
ውሉ ጠፍቶኝ ነው የማስጨንቃችሁ፣
ካለበት ንገሩኝ መሪዬን ካያችሁ።

—— // ——

## ብራ!

ሰማዩም ይጨልም መብረቁም ያጓራ
ዳመናውም ይክበድ ይሸፍን ተራራ
እንኳን ካድሬ ቀርቶ ድንቢጥ ሰውን ትምራ
ጉሰኝነት ነግሶ ሰላዩም ያቅራራ
ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋዩንም ይግራ
ደብተራውን ቀንቶት፣ ከፈለገ ጋኔል ይጥራ፤
የጉሲፕ ቴረሪስት፣ የጠበኞች አውራ
ያልበሰለ አሹቅ የጭቅቅት ሞራ
የሰው በድን የኩይሳ ኖራ
ጂን ተርታሪ የአፍራሾች ናምራ
በተግባሩ አፍሮ እስኪጣራ
የሐቅ እናት የወላፈን ጮራ
የብርኃዊነት ልብ የልምድ ተራ
ቡቃያዋ አድጋ እስክታፈራ
ጭጋግና ካፊያ በነው – እስክትወጣ ብራ።
እርግብ ሆኖ፣ እስከሚለሰልስ ቁራ
የዝንጀሮ መንታ፣ የዝግመተ–ለውጥ ጭራ
የድንቅነሽ አያት፣ የስልጡን ህዝብ ፋራ፤
የእውነት ምስልን እንኳ እስኪፈራ።
ያንድነት ኩል ውኃ እስክትጠራ
በደም በላብ የተጋራ
ግምባር የህዝብ ልፋት –
ማገር መሰረቱ እስኪሰራ እስክትወጣ ብራ!!

—— // ——

# <u>ኢትዮጵያና የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን</u>

– በቀሲስ ኤፍሬም አ. ከበደ
(ካለፈው የቀጠለ)

የኢትዮጵያ አንድነትና ነፃነት፣ እኩልነት እንዲሁም ባህላችንና ቅርሳችን የብሔረሰባችን እኩልነት ይታወቅ ይከበር ካልን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስን ተዋህዶ ቤተክርስቲያንን በቅድሚያ መጠበቅ ሲኖርብን ነው!!

ለምን ቢባል ይህች እናት ቤተክርስቲያን ኢትዮጵያ በእግዚአብሔር ፈቃድ ኢትዮጵያ ተብላ ወይም በዚህ ስም ተሰይማ ከተሰጠችን ጀምሮ ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳንን በመቀበል ለእኛ የሰው ልጅ በአዕምሮው እኩልና ነፃ ሕዝብ፣ በእግዚአብሔርም ዘንድ የተከበረ መሆኑንና በምድር ላይ ያለውን ሁሉ ይገዛና ያዝ ዘንድ ስልጣን ተሰጥቶት (የሚበሉና የማይበሉትን) በኦሪት ዘሌዋውያን ም. 11÷1–ፍፃሜ የተፃፈውን በማስተማር አንዱ አገር የሌላውን አገር መድፈር ክልክል መሆኑን አገርንም ሆነ ሕዝብን (ሰውን) የፈጠረ እግዚአብሔር ስለሆነ እርስ በርሳችሁ ተከባበሩ ተወያዩ፣ እርስ በርሳችሁም ተፈቃቀራችሁ በአንድነት ኑሩ፤ እንዲያውም የምታየውንና(ትን) ወንድምህንና እህትህን ሳትወድ እግዚአብሔርን እወዳለሁ ማለትህ ሐሰተኛ ያደርግሃል። 1ኛ ዮሐንስ 4÷18–ፍፃሜ ይላል።

ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያው ነቢይና ሊቀ ነቢያት የሆነው ሙሴ ኢትዮጵያዊቷን እንዳገባ ታሪክ ይነግረናል። ቤተክርስቲያናችንም ይህን የመሰለ ቁም ነገር እያስተማረች ቆይታለች። ወደፊትም ታስተምረናለች ሂደቱንም እስከዓለም ፍፃሜ ትቀጥላለች። ሕዝቧንም በንቃተ ሕሊና ተቆጣጥራለች። የቤተ ክርስቲያናችን ታሪክና የኢትዮጵያ ክብረ–ነገሥት እንደሚለውና እኛም እንደምናምነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሴሜቲክ (ሴማውያን)ና ካም (ካማውያን) ነው።

እነዚህ ሰዎች አባታቸው ኖህ ይባላል። ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚነግረን በዘፍጥረት 7÷13 ላይ ታላቁ ኖኅ ሦስት ልጆችን ወልዷል። እነርሱም ሴም፣ ካም፣ ያፌት ይባላሉ። እንግዲህ እነዚህ ሁለቱ የእኛ የኢትዮጵያውያን አባቶች ናቸው። አሁንም በዘፍጥረት ም. 9÷8 ቁጥር 6 ላይ «ሰውን በእግዚአብሔር መልክ ፈጥሮታልና እናንተም ብዙ ተባዙ በምድር ላይ ተዋለዱ እርቡባትም» ይላል። በመቀጠል በቁጥር 8 ደግሞ እግዚአብሔር ለኖኅና ለልጆቹ እንዲህ ብሎ ተናገረ «እኔ ም እነሆ ቃል ኪዳኔን ከእናንተና በኋላም ከሚመጣው ዘራችሁ ጋር እቆማለሁ። ከእናንተ ጋር ላሉትም ቃል ኪዳኔንም ለእናንተ አቆማለሁ» ካለ በኋላ «<u>አቀስም ቅስትየ በውስተ ደመና</u>» የቃል ኪዳኔን ምልክት ለእናንተ በደመና መካከል አስቀምጣለሁ አለ። ይህም ምልክት ኖህ ልጆቹንና እሱን የመሰሉትን ሰዎች አራዊትንና እንስሳትን በየወገኑ በመርከብ እንዲያስገባና ከጥፋት ውኃ እንዲድኑ እግዚአብሔር ለኖኅ ተናገረው። ዘመኑ የጥፋት ዘመን፣ ሰው ለእግዚአብሔር አልታዘዝ ያለበት፣ የክፉ ዘመን፣ ክህደት የበዛበት፣ አመፅ የሞላበትና አለመታዘዝ ሰውን መዝለፍ፣ ቀልድና አሉባልታ፣ ዝሙት፣ ውሸት የበዛበት ዘመን ነበር። በዚህ ጊዜ ኖኅንና ቤተሰቡን እግዚአብሔር በማግኘቱ ተደሰተ፣ ኖኅም የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ልዋል፣ ልደር ልሰንብት ሳይል የሰው ልጅ ከጥፋት ውኃ እንዲድን አዋጅ አስነገረ። የሰሙት ወደ መርከቡ ገብተው ሲድኑ ያፌዙበትና አዋጁን ያልተቀበሉት በንፍር፣ በሚነድና በሚያቃጥል ውኃ እንዳለቁ በዘፍጥረት 7÷1–ፍፃሜ ተፅፎ እናገኘዋለን። ታዲያ ከንፍር ውኃ በኋላ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ሰላምን በምድር ያወረደና የሰጠ መሆኑ ቀደም ብለን በገለፅነው ምልክት ቃልኪዳኑን ለእኔና ለእናንተ አቁሟል። ይልቁንም ኢትዮጵያውያን የባንዲራችንን ምልክት ያገኘነው ከዚያ ሲያያዝ በመጣው ነው። በደመናው መካከል የታየወ ቀስት (ምልክት) ከሰባት በላይ የሚበልጡ ኅብረቀለማት ናቸው። በዚያ ታላቅ ምልክት ውስጥ አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ የእኔና የእናንተ ልዩ ምልክታችን ሆኖ ይኖራል። እኛ ብቻ ሳንሆን መላው ጥቁር ሕዝብ የኢትዮጵያ አምላክ ይጠብቀን በማለት ባንዲራችንን ከፍ አድርገው በማውለብለብ ላይ ይገኛሉ። በሌላ በኩል በመጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ (ሁለተኛ) ም. 9÷1–ፍፃሜ ንግሥተ አዜብ (የደቡብ)፣ ንግሥት ማክዳ ወይም ንግሥት ሳባ ኢትዮጵያዊት ንግሥታችን የሰለሞንን ጥበብ ለመማርና ለማወቅ ወደ እስራኤል እንደተጓዘች ይነግረናል። በክብረ ነገስት እንደተፃፈው በዚያም ወቅት እርሷ ቀዳማዊ ምኒሊክን (ፀንሳው) እንደተመለሰች መጽሐፈ ነገሥት ይነግረናል። ንግሥተ ሳባ ከሰሎሞን የወለደችው ልጅ ቀዳማዊ ምኒሊክ ካደገ በኋላ አባቱንና የአባቱን አገር ኢየሩሳሌምን ለመጐብኘት ሄዶ ሲመለስም ለሙሴ በሲና ተራራ ላይ የተሰጠችውን ታቦተ ጽዮንን ከካህናተ ሌዋውያን ጋር ወደ ኢትዮጵያ አምጥቶ በአክሱም አስቀምጦታል። ይህ የቃል ኪዳን ታቦት በሀገራችን በአክሱም በክብር ተቀምጦ በመኖሩ በጣም የታደልን ነን። እግዚአብሔርም ለኛ ያለው ፍቅር እጅግ ብዙ መሆኑን ያሳየናል። ለአሁኑ መስዋዕታችንና አገልግሎታችን በትንቢተ ሶፎንያስ ም. 3÷10 «ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ የሚማልዱኝ የተበተኑት ልጆቼ ቁርባኔን ያመጡልኛል» ይላል። በመዝሙር 67 ቁጥር 31 ላይ ደግሞ «እኔ የምመራቸውና በእኔም ፅኑ እምነት ያላቸው መሆናቸውን ሲገልፁ ኢትዮጵያውያን እጃቸውን ወደኔ ዘርግተው ይፀልያሉ» ይላል። በሌላ በኩል ደግሞ በመዝሙር 71÷8 «እግዚአብሔር ከሰማይ እስከ ምድር ይገዛል። ኢትዮጵያውያን በፊቱ ይሰግዳሉ።» ይላል። እንግዲህ ኢትዮጵያና እግዚአብሔር ስጋ እንደለበሰ ሰው ሲነጋገሩና ሲወያዩ እንደነበር ቅዱስ መጽሐፍ ይግረናል። አዎ ክርስቶስም ሲወለድ «ነገሥተ ተርሴስ ወደሰያት አምኃ ያበውኡ ነገሥተ ሳባ ወአረብ ጋዳ ያመፅኡ ወይሰግዱ ሎቱ ኩሎሙ ነገሥት ምድር» ትርጉሙም፦ የተርሴስና የደሴቶች ነገሥታት ስጦታን ያመጣሉ የአረብና የሳባ ነገሥታትም እጅ መንሻን ያቀርባሉ ሁሉም ነገሥታት ይሰግዳሉ ይላል። እንግዲህ ክርስቶስ ሲወለድ በግርግም ወርቅ፣ እጣንና ከርቤ የገበሩ ሳባውያን ወይም ኢትዮጵያውያን እንደሆኑ አሁንም በመዝሙር 71÷10 ተፅፎ እናገኘዋለን።

እግዚአብሔርም ኢትዮጵያውያን ኃይለኞችና አስፈሪ በመሆናቸው በትንቢተ ኢሳይያስ ም. 18÷1 ላይ ሲቆጣቸው እንመለከታለን። ኢትዮጵያውያን መልካቸው ኅብረ ቀለማት የሆኑና ልባቸውና አስተሳሰባቸው አንድ ሃይማኖታቸው የፀና እግዚአብሔርን የሚያከብሩ የሚፈሩ ትዕግስተኞች፣ ለጓደኞቻቸውና ለሚወዳቸው ሁሉ ህይወታቸውን አሳልፈው የሚሰጡ ናቸው። ለምሳሌ አንድ ሰው መንግሥት ለማሰር ቢፈልገው ተፈላጊው ሰው ቢጠፋና ቢሰወር መንግሥት ቤተሰቡንና ንብረቱን

ለመውሰድ ቢሞክር ጓደኛው ተነስቶ የለም ሚስቱና ንብረቱ ከሚጕሳቆሉ በጓደኛዬ ፋንታ እኔ እታሰራለሁ በማለት እስር ቤት ስለጓደኛው ቤ፡፡ ሲሆን ተሰውሮ የነበረው ሰው አየና ጓደኛዬ ከሚታሰር እኔው ባለዕዳው ልታሰር በማለት እስር ቤት ሲገቡና ቃል ኪዳናቸውን ሲጠብቁ ኖረዋል። የሃይማኖታቸው ጽናት ብቻ ሳይሆን አስፈሪነታቸውና ግርማ ሞገሳቸው ለውጭ ጠላት አልበገር ባይነታቸውን የዓለም ህብረተሰብ ቁልጭ አድርጐ በታሪክ ያውቀናል።

ቀደም ብዬ የገለፅኩት ካም አባታችን ኩሽ የሚባለውን እንደወለደና ይህ ሰው በሞተ በ2 ሺህ 450 ዓመተ ዓለም ከጌታ ልደት በፊት መጻሕፍተ ብሉያትን ከእብራይስጥ ወደ ጽርዕ የመለሱ ሰባው ሊቃውንተ ሙሴ «ኩሽ» እያለ በእብራይስጡ ብሉይ ኪዳን የተፃፈውን ኢትዮጵያ በሚል ቃል ለውጠውታል። ኢትዮጵያዊ ማለት በመልኩ ቀይ፣ የቀይ ዳማ ቀለም ያለው በቁመቱ እንደዛሔል ረጅም ሆኖ ያልተንቀዋለለና እንደ ድንክም አጭር ያልሆነ ሕዝብ ማለት ነው። ስለ ኢትዮጵያ ታላቅነት ታዋቂው ፈላስፋ ሆሜርና ሶቅራጥስ ሌሎቹም የታሪክ ጸሐፊዎች ብዙ ብለዋል። ኢትዮጵያ ለውጪ ወራሪ የማትመች ጋራዋ ሸንተረሩ፣ ገደል አፋፉ፣ ቆላ ደጋ ወይና ደጋ፣ ብርቅየ ልጆች ያሏትና በውስጧ ያሉት እንስሳትና አራዊት ታይተው የማይጠገቡ የአገሪቱ አየር ጠባይ የማይለበልብ የማያቃጥል የማይቆረጥም የማይበርድ የማይሞቅ ልከኛ መጠን ያለው ነው። ኢትዮጵያ በውበቷ ብቻ ሳይሆን በአንጡራ ሀብቷና ከእግዚአብሔር በተሰጣት ፀጋ ከአለም ልዩ ያደርጋታል።

ኢትዮጵያ እምትፈተነው ወይም እየቆሰለች ያለችው በአሁኑ ጊዜ በራሷ ልጆች ይልቁንም በጽዮን ዙሪያ በተወለዱ ልጆች ነው። የኢትዮጵያን ታሪክ መለስ ብለን ለማየት ባለንበት ዘመን ማለትም በኢትዮጵያ አቆጣጠር ከ1966 ዓ.ም. አንስቶ እስካሁን ያለውን የሕዝብ እልቂት ብቻ ሳይሆን በነዮዲት (ጉዲት)ና ግራኝ መሐመድ ያለውን እንመልከት። በ842 ዓ.ም. ገደማ ላይ በአክሱም የድግናሣን ልጅ አንበሣ ውድም የተባለ ሕፃን ንግሥ ሳለ ሕፃኑ ንጉሥ አገሩን ለማስተዳደር አለመቻሉን ሰምታ ዘመዶቿን በክተት አሰልፋ ዮዲት ወደ አክሱም ገሰገሰች። ሕፃኑ ንጉስም ከመኳንንቱ ጋር በመሆን ወደ ሸዋ ሸሸ። ዮዲት አክሱም ከተማ ገብታ ወረራዋን ቀጠለች። ዮዲት አመጣጧ (ዘሮቿ) የመጡት ከእስራኤል ነው። ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ከቀዳማዊ ምኒሊክ ኢየሩሳሌም ደርሶ መምጣት ወዲህ ይህች አገርም ጠላት በተለያዩ ጊዜያት ከደመሰሳት በኋላ ብዙ ይሁዲዎች ወደ ኢትዮጵያ እየፈለሱ መግባታቸው ይታወቃል።

ኢትዮጵያም እንግዳ በመቀበል የታወቀች አገር በመሆኗ እነዚህ ይሁዲዎች በሌላ አነጋገር ፈላሻ (ስደተኞች) በኢትዮጵያ ተራራማ አገር እየኖሩ የኢትዮጵያን ክርስትና አንቀበልም ብለው ኢትዮጵያውያኑም ነፃነታቸውም ሳይነኩ እንዲያውም ጊዶዎን የተባለውን ንጉሠ አንግሰው ይኖሩ ነበር። እንግዲህ ዮዲት ማለት የዚህ ንጉስ ልጅ ናት ተፈጥሮዋም መልከ መልካምና በጣም ኃይለኛ ነበረች የክርስትና እምነትን የማትቀበለውና መጥፋት ያለበት መሆኑን በአዋጅ አስነግራ በክርስቲያኖች ላይ ከአባት የወረደ ጥላቻ ስለነበራት የክርስትናን ቅርስ ሁሉ አቃጠለች። በአብርሃ አጽብሃ ዘመን የተሰራችውን በኢትዮጵያ የመጀመሪያዪቱን የድንግል ማርያምን ቤተክርስቲያን አቃጠለች። ከክርስትና በፊትና በክርስትናም ዘመን የተሰሩ ብዙ ሐውልቶች አፈራረሰች። ብዙ መፃህፍትና ንዋየ ቅድሳት ቅርሶች ታሪኮች ተደመሰሱ። አያሌ ካህናትና ክርስቲያኖች ከድንግል ማርያም ቤተክርስቲያን ጋር አብረው ነደዱ። ከዚያ ስቃይና መከራ የተረፈው ህዝብ ይህችን ሰው በዮዲት ፈንታ «ጉዲት» እያለ ይጠሯት ነበር። ይህ የፍዳና የመከራ ዘመንም ለ40 ዓመት እንደቆየ በታሪካችን ተመዝግቦ ይገኛል። ይህ ብቻ አይደለም ግራኝ መሐመድ ኢትዮጵያ ተወልዶ ክርስትና እምነትን አጥፍቶ ሃገሪቱን በእስልምና እምነት ለማጥለቅለቅ በጊዜው ቱርኮች ከአረብ እስላሞች ጋር ክንዳቸውን አስተባብረው ወረራቸውን በመላው ሰሜን አፍሪቃና አውሮጳ፣ ደቡብ ግሪክ፣ ስፔን፣ አልባኒያ፣ ቡልጋሪያ፣ ሩማንያና፣ ዩጐዝላቪያ እነዚህ ሁሉ የቱርክ ግዛቶች ሆኑ። ግራኝ መሐመድ ኢትዮጵያን ለቱርክ ለማስረከብ ከቱርክ በድብቅ እየተላላከ ያከማቸውን መሣሪያ በመምዘዝ በክርስቲያኑ ላይ አነጣጠረ። በዚህ ጊዜ ቤተ መንግስቱ የጦር መሣሪያ ከካቶሊኮች ቢጠይቅም ጆሮ ዳባ ልበስ ተብሎ ሰሚ አጣ። ምክንያቱም ካቶሊኮች ቀደም ሲል በኢትዮጵያ ምድር ኦርቶዶክስ ተዋህዶን አጥፍተው የራሳቸውን ክልኤ ባህርይ ሃይማኖት ለማስፋፋትና በቅኝ አገዛዝ ውስጥ ለማስገባት ሞክረው ጥረታቸው ሳይሳካላቸው ቀርቷል።

በዚህ ቁጭት ነው የጦር መሣሪያውን ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆኑት በወቅቱ የኢትዮጵያ መንግስት መሣሪያ ባለማግኘቱ መሐመድ በለስ ቀናውና ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ለ15 ዓመት ባለማቋረጥ በኢትዮጵያ ምድር ላይ የቱርክን ጥይት አነደደ። ከዮዲት ወረራ ተርፈው ክርሷም በኋላ የተተከሉት የክርስትና ቅርሶች በግራኝ መሐመድ ወረራ ጨርሰው ወደሙ። በወርቅና በብር በነሐስ የተሰሩ አብያተ ክርስቲያናት በእሳት ተለበለቡ፣ የሃይማኖት መጽሐፍት፣ የታሪክ ሰነዶች የእሳት ራት ሆኑ። ከሞት ያመለጡ ካህናትና ምዕመናን በሰይፍ እየተገደዱ የእስልምና እምነትን እንዲቀበሉ ተገደዱ። በተለይ በወሎ ክፍለሃገር በሸዋ፣ በሐረር፣ በትግራይ፣ በከፊል ጐንደር ወዘተ በአሁኑ ወቅት ብዙ መስቀል፣ ጽዋ ጽና እንዲሁም በድንጋይ ተፈልፍለው የተሰሩ ቤተ መቅደሶች በግራኝ መሐመድ ወረራ ጊዜ የተዳፈኑ ናቸው። በግራኝ ጊዜ ብዙ ችግርና ፈተና የታየበት ከምግብ እንኳ እርጥብ ስጋ መብላት የተጀመረበትና በዱር በገደል እሚታደርበት ጊዜም እንደነበር ታሪክ ይነግረናል።

እንግዲህ መለስ ብለን የሃገራችንን ታሪክ ስንመለከት ኢትዮጵያ የታመመችው፣ የተጠቃችው የተቸገረችው፣ ፈውስ ያጣችው፣ መድኃኒት ያላገኘችው፣ ከአብራኳ በወጡት በራሷ ልጆች ነው። እንግዲህ ዮዲትና ግራኝ መሐመድ ታሪክ ሊሽረው የማይችለውን የታሪክ ጠባሳ ትተው አልፈዋል። እነዚህ ሁለት ሰዎች ኢትዮጵያ ተወልደው በማደጋቸው የኢትዮጵያን ጋራና ሸንተረር ቁልጭ አድርገው በማወቃቸው ኢትዮጵያን ጐድተዋት አለፉ። ይህች አገር የእግዚአብሔር አገር በመሆኗና የእግዚአብሔር ስም ጧትና ማታ የሚጠራባት ሃገር፣ በአንድ ገዳም ወይም ደብር ውስጥ ዘወትር ቅኔ ማኀሌት፣ በጕን ሰዓታት ከዚያ ቅዳሴ፣ ከቀትር በኋላ ምህላ ጸሎት በጠቅላላው ስብሐተ እግዚአብሔር የሚደርስባት አገር

ስለሆነች ይህ ሁሉ ግፍ ሲፈፀምባት ኢትዮጵያና ህዝቧ እንደፀሐይ አበሩ እንጂ አልጠፉም። ኢትዮጵያም ለውጭ ወራሪ የተዳፈነ ረመጥ ናት ታሪኳንም ከሦስት ሺህ በላይ አስቆጥራ ትገኛለች።

በአሁኑ ጊዜም ያለው ችግር ከዚህ በላይ ከጠቀስኩት ጋር የሚመሳሰል እንጂ ያነሰ አይደለም። መልኩን ቀይሮ የኢትዮጵያን ህዝብ በራብ አለንጋ የሚቀጭ፣ የአዕምሮ ቶርች የሚሰጥ፣ ድሮ ገንዘብ የሚቀማበት ቢሆን አሁን ሀሳብ አዕምሮን የሚሰለብበት ጊዜ ደርሰናል። ሕዝባችንም እርስ በእርስ የወንድማማች ፍቅር ይኑር ተብሎ የተሰበከላትን አገር በአሁኑ ጊዜ በቤተሰብ፣ በሃገር፣ በጉጥ፣ በክልል ተከፋፍሏል። አንዳንዶቻችንም ክፍፍሉን ያዳንን እየመሰለን የከፋፋዮች ግልባጭ ስራ እየሰራን ነው። ካህናቱም እንቅልፍ ላይ ከመሆናችን ባሻገር ሕዝቡን አንድ አድርጐ ሰብስቦ ማስተማር አቅቶናል። አንዳንዶቻችን ካህናት አንድ የሆነውን ህዝብ በመዝለፍ፣ በመስደብ፣ መበተኑን ተያይዘነዋል። ይህም በውስጣችን እነማን እየመሩን እንደሆነና ወዴት እየተጓዝን እንደሆነ ማስተዋል አለብን። ጌታ በዮሐንስ ወንጌል ም. 10፥1–22፣ ም.21፥15 ለጴጥሮስ «በጐቹን ጠብቅ፣ ግልገሎቹን አሰማራ፣ ጠቦቶችን ጠብቅ።» በማርቆስ ወንጌል ም.16፥18–20 «በምድር ያሰርከው በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድር የፈታኸው በሰማይ የተፈታ ይሆናል» በማለት የሰማይና የምድር ቁልፍን እንደሰጠው እንመለከታለን።

መልካም እረኛ ስለበጐቹ ራሱን አሳልፎ ይሰጣል። ግድ የሌለውና ምንደኛ እረኛ በጐቹን ለአውሬ አሳልፎ ይሰጣል። ይህ ምሳሌ በግ የተባሉ የሰው ልጅ ሲሆን እረኛ የተባለው ደግሞ ካህናት ናቸው። እንግዲህ ካህናት መሪና ጠባቂ ከሆኑ ከተመሪነት ወጥተው መሪ መሆን አለባቸው። ሕዝቡንም አንድ ማድረግ አለብን፣ ግፍና በደል እንዳይፈፀምበት ነቅተውና ተግተው ማስተማር አለባቸው። ካህናት ወገን የላቸውም፤ ወገናቸውም በክርስቶስ ኢየሱስ ክርስቲያን የሆነው ሕዝባቸው ነው። አገራቸውም የተማሩበት ት/ቤት፣ መነኩሴ ከሆንም የመነኰሰበት ገዳም ነው። አባታቸውም ለክህነት ያበቋቸው ያስተማሯቸው መምህሮቻቸውና እግዚአብሔር ነው። እናታቸውም ቤተክርስቲያን ናት። ተከታዩን በሚቀጥለው እናቀርባለን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር አሜን!!

# ፀሐይምሸት

(ከገፅ 37 የዞረ)

ሽጉጡን ሳያሳያት ከጀርባዋ ያቅፋታል። ሽጉጡንም አውጥቶ ሊያስጨብጣት ሲል ፊቱን በጀርባዋ ለማየት ትዞራለች። በፍርሃት ተውጣለች። ከግጥሙ ጋር ስልቱ የተያያዘ እን ቅስቃሴ እያደረገ፤ አከላቷን እየደባበሰና እያሽሞነሞነ። በአዕምሮ ተመልካችነት ጥበባዊ ፍቅርን መግለፅ የጀመረው ህሊና አንዳንድ ጊዜ ሽጉጡ በሚስቱና በጓደኛው ላይ ያነጣጥር ነበር።

ፀጥታ በሁሉም ዘንድ ሰፈነ። በጡቶቿ መካከል በደረቷ ላይ ያንሸራተተው አፈሙዝ ከአገጯ ሥር ይደግን ባታል። "በርሽን ደፍሮ ገብቶ ሊደፍርሽ የመጣውን እንደ ቄጤማ እንድታረግፊበት ነው ይህንን የገዛሁልሽ። ልትሞክሪው ትፈልጊያለሽ?"

"ህሊና ትንሽ አስጨነቅሃት።" አለ አዕምሮ በራሱ እንደሚመጣበት ቢያውቅም ይበልጥ ስለእርሷ በመስጋት።

ህሊና ፀሐይምሽትን ገፍትሯት ያነጣጥርባታል። "ለቀቅ ላድርጋታ!" በቁጣ ነበር።

"እንደርሱ ማለቴ አይደለም!!"

"ተደረብና ፎቶግራፍ ላንሳችሁ።" በግራ እጁ ይዞት የነበረውን ቀኝ እጅዋን በመጎተት አዕምሮ ከተቀመጠበት ሶፋ ላይ ይወረውራታል።

"አሁንስ ህሊናህን ሳትስት አልቀረህም። ወዲያ በለው መሣሪያውን።" የፍርሃቱን ተናግሮ ወጣለት።

"*'ህሊና ህሊናውን ሳተ!' 'እውነት እውነትን ከዳች'* *'ህሊና ህሊናውን ሳተ!'*

"ፖለቲካ ባንድ ሰው ቡጢ የሚዘረር አይደለም። ባድማ ካልወቁት ፍሬውን ማግኘት አይቻልም። ራስህን ጎድተህ እሷንም አትጉዳት! እኔንም ቢሆን ትጎዳኛለህ! ላጣህ አልፈልግም። ከብዕር ሌላ መሣሪያ የለኝም የምትለው ሰውዬ ሽጉጥ ምን አስመኝቶህ ነው የገዛኸው?"

"በሚስትና በአገር ቀልድ የለም። እኔ ባልኖርም እንደ ወንድም ጋሻ ሁነህ እንደማታስደፍራት አምናለሁ። ግን በየቀበሌው የማንም ኩታራ ሥልጣን ጨበጥኩ ብሎ እኛን ልጆቻችንን የፈጠሩና የሚፈጥሩትን አማልክት ነው እኮ የሚዳፈረው። ምነው የሠራችሁት ወንጀል እንዳለ ነገር ተደናገጣችሁ?! ለባለቤትህም አንድ የዚሁ ዓይነት ገዝቼ ስጥቻታለሁ። እዚህ በር ከደረስኩ በኋላ ተመልሼ ሂጄ እንዴት እንደምትጠቀምበት አሳይቼአት ነው የመጣሁት።"

"ማድረግ አልነበርብህም።" አለው ያላወቀና ያልጠረጠረ መስሎ ስለታየው።

"ለማጥቂያ ሳይሆን ለመከላከያ ነው። ጊዜው የከፋ ነው።"

"እኔን ማማከር ነበረብህ።"

"ጥቃት ሲደርስባት መድረስ ባልችል ይሄ ትልቅ ዕርዳታዬ ይሆናል። ይልቁን ቡና አፍልታ እየጠበቀችህ ነው።"

"እናንተም መምጣት ትችላላችሁ።" አለ አዕምሮ ከዚያ ለመውጣት እየተጣደፈ።

"እኔ አልመጣም። ራስ ምታት ይዞኛል። መተኛቱን እመርጣለሁ።" ስትል ፀሐይምሽት ተቃወመች። ፊቱን ዳግመኛ ለማየት አልወደደችም። ለጉደኛዋም እንዴት ብላ እንደምትነግራት መንገድ አላገኘችለትም።

"መንገዱ እንዳይከዳው ሸኝቼው እመጣለሁ።" ይልና ከአዕምሮ ጋር ተያይዞ ይወጣል።

---

*(በሚቀጥለው እትም ይቀጥላል።)*

# ዜና ቤተክርስቲያን

## በሴንት ሉዊስ የቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ተመሰረተ

የኢትዮጵያ ሕዝብ እምነቱንና ባህሉን አክባሪ ህዝብ ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ኃይማኖት ለዘመናት የማንነታችን መግለጫ በመሆን ከሌላው ህዝባችን ኃይማኖት ማለትም ከእስልምና ጋር ተቻችሎና ተከባብሮ በመኖር ይህ ነው የማይባል ታሪካዊ አስተዋፅኦ አድርጓል። በውጭ ሀገርም በስደት የተበተነው ሕዝባችን የማንነቱ አሻራ ተውጦ እንዳይቀር፣ እዚህ የተወለዱትም ሕፃናት በአልባሌ መጥፎ ባህል ውስጥ እንዳይገቡና አስተዳደጋቸውም በፈሪሃ እግዚአብሔር ግብረገብነት እንዲታነፅ በየቦታው ቤተክርስያናትን መስርቷል። በአትላንታ፣ በዳላስ፣ በኦሀዮ፣ በካሊፎርኒያ፣ በዋሽንግተን–ዲሲ፣ በኒውዮርክ፣ በሂውስተን፣ በካናዳና በአውሮጳ ...ወዘተ ከሀገር ፍቅር፣ ከባህል፣ ከፍትህና ከአምላክ ፀጋ ጋር ምኞቱንና ሐሳቡን በግብር በመተርጐም በከባድ መስዋዕትነት በምዕራቡ ዓለም መንበረ–ጵጵስና ስር አያሌ አብያተክርስቲያናትን መስርቷል።

በሴንትሉዊስም የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ይህንን አርአያ በመከተል በኦክቶበር 26 ቀን ብፁዕ አባታችን አቡነ መልከፀዴቅ ወርቅነህ በተገኙበት በደመቀ ሁኔታ ተመርቋል። በበዓሉ ላይ የልዩ ልዩ ኃይማኖት ተከታይ ምዕመናንና ማለትም የእስልምና እምነት ተከታዮች፣ የሴንትሉዊስ የካቶሊክ ጳጳስ ተወካይ፣ የሰብዓዊ ድርጅቶች ወኪሎች፣ በአካባቢው የሚገኙ የኮሌጅና ዩኒቨርስቲ ምሁራንና እንደዚሁም ከሌሎች የሚዞሪ ስቴት ካውንቲዎች የመጡ ኢትዮጵያውያን ነበሩ። የሴንትሉዊስ ከንቲባ የዕለቱን ክቡርነት በማወደስ ኦክቶበር 26ን የኢትዮጵያውያን የፍልሰ–ስደተኛ ቀን (Ethiopian Immigrants Day) የሚል አዋጃዊ መግለጫ (PROCLAMATION) ከጽህፈት ቤታቸው ልከዋል። የሚዙሪም ሀገረ ገዢ የተከበሩ ሜል ካርንሀን የበዓሉን ዐቢይነት የሚገልፅ ተመሳሳይ የምስክርነት ወረቀት ልከዋል፤ በዚህ አጋጣሚ ከሌሎች ስቴቶች በገንዘብና በሞራል ድጋፍ ላበረታቱን ኢትዮጵያውያን ማለትም የኦሮቶዶክስ ምዕመናን፣ የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮችና ሀገር ወዳዶች ምስጋናችን ከፍተኛ ነው። በሴንትሉዊስ የቅዱስ ገብርኤል ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን መስራችና አተባባሪ ኮሚቴ ተገቢውን የመንግስት ሰነድ በማሟላት የባንክ ሂሳብ የከፈተ ሲሆን፤ የሚቀጥለው ፕሮግራሙ ከኪራይ ባሻገር ለቤተክርስቲያን መስሪያ የሚሆን መሬትና ቤት ለመግዛት በጥናት ላይ ነው። ለዕርዳታና ለመሳሰሉት የሀሳብ ግኑኝነቶች በሚከተለው አድራሻ ይፃፉልን።

ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች!!

የሴንትሉዊስ ቅዱስ ገብርኤል ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን መስራችና አስተባባሪ ኮሚቴና ምዕመናን

St. Gebriel Ethiopian
Orthodox Tewahido Church
2149 South Grand Blvd.
St. Louis, MO 63104
(Phone) (314) 367 - 4014


# ኢትዮወርድ EthioWord

## ግዕዝና የዓለም ፊደላት በኢንተርኔት

በተሟሉና ባልተቀጠሉ እንዲሁም በተቀጠሉና በጎደሎ ፊደላት ማንኛውም ፎንት የሚቀበል የዊንደውስ ፕሮግራም ውስጥ በማንም ፎንት ለመጻፍ ግዕዝኤዲት GeezEdit $99.00 ፡፡ ኢትዮወርድ/ግዕዝኤዲት EthioWord/GeezEdit $199.00 - for use in any Windows 3.1 and Windows 95 program which allow font substitution. ግዕዝን ከዓለም ፊደላት ጋር ኢንተርኔት ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ለማተምና ለመፈለጊያ ኢትዮሳይበር EthioCyber $495.00 ፡፡ (Multi-lingual hyper linked documents)

ምሳሌ:- ዐረብኛ/Arabic ([illegible]) ግሪክ/Greek (Σ'Ωϱ,ῦώεῦ) ሕብራይስጥ/Hebrew ([illegible]) ጃፓን/Japanese (ムラ三トメヤメト二) etc. Type, publish and search Ethiopic documents on the Internet and enjoy it on Windows, Macintosh an UNIX platforms. Check out the Ethiopic pioneers at *http://www.ethiopic.com* and get FREE software.

### የኢትዮጵያ ኮምፒዩተሮችና ሶፍትዌር

### Ethiopian Computers and Software

9781 W. Fremont Pl., Littleton, Colorado 80123, USA

Fettan Graphics 1209 U St. NW, Washington, DC 20009

Tel: 303/972-2186, 202/785-1618 and 301/270-3865

Fax: 303/973-4342 or 202/785-1626

E-mail: Ethiopian@aol.com – ይቢር አበራ ሞላ ኢ-ሜል በግዕዝ (Ethiopic E-Mail)

# ከአበው

## ታሪክና ምሳሌ

### ዕጓለ አንበሳ መሆኑ አይረሳ

በጥንት ግሪክ በተረብ (ቀልድ) አነጋገር የታወቀ ዝነኛ ኤዞፕ የሚባል ሰው ነበር። ይህም ተረበኛ ሰው እንስሳትን፣ አዕዋፍን፣ የባህር ዓሳዎችንና ሌላውንም ተንቀሳቃሽ ፍጥረት ሁሉ እንደገናም ነባቢና ኢነባቢ የሆነውን ግዑዝ ፍጥረት ሁሉ ማለትም ዕፅዋትን፣ አዝርዕትና አትክልትን፤ በአጠቃላይ ሣርና ቅጠሉን ሁሉ በሰዎች እየመሰለ በሚናገረው ተረብ ሁሉ የሰዎችን መጥፎ ጠባይና የአመራር መዛባትን፣ የአስተዳደግን በደል፣ እከብር ባይ ጎሊናን፣ የራስ በራስ መለያየት የሚያመጣውን ጉዳት፣ አሉባልተኛነትን፣ ዘረኛነትን በአጠቃላይ የክፋትን ዘር ሁሉ (social evils) የሚኰንን ብርቱ አቃቂረኛ ነበር።

ስለዚህም ኤዞፕ ከተናገራቸው አስደናቂ ተረቦች አንዳንዱን መጥቀስ ብንፈልግ የአንዲት እንስት አንበሳ ታሪክ ተቀዳሚነትን ይይዛል።

«ይኸውም» ይላል ኤዞፕ «ይኸውም አንዲት ወላድ ቀበሮ ብዙ በመውለድዋ ትምክህትና ትዕቢት አድሮባት በአንዲት እንስት አንበሳ ላይ መዘባበትና መዳደድ ፈልጋ በማፌዝ መልክ ስትናገር «አንቺ እኮ ግርማ ያለሽ የእንስሳት ንግሥት እየተባልሽ የምትጠሪው በከንቱ ነው። መመስገን የሚገባንስ መንታ መንታውን የምንወልድ እኛ ቀበሮዎች ነበርን። አንቺ ግን ከአንድ በላይ መውለድ አትችዪም» አለቻት። እንስት አንበሳይቱም በሰከነ መንፈስ ረጋ ብላ ስትመልስላት «ቁም ነገሩ እኮ ሰባት መንታ የቀበሮ ልጅ ያው ቀበሮ ነው። ከእኔ የተወለደው አንድ ለእናቱ ግን የአንበሳ ደቦል (ዕጓለ አንበሳ) መሆኑ አይረሳ» አለቻት ይባላል።

ይህንን አባባል አሁን ላለንበት ዘመነ ልደት እንደምሳሌያዊ ማስረጃ አድርገን ብንጠቀምበት እንስት አንበሳ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ መሆን ትችላለች። ይኸውም ምሳሌ ዘየሐፅፅ(ተመጣጣኝ ያልሆነ) ተቀራራቢ ማስረጃ እንጂ መቶ በመቶ እርስዋን የሚተካ ማለታችን አይደለም። መመልከት ያለብን አንድ ለእናቱ የተባለ መሲህ (ክርስቶስ) ቀደም ሲል በአንበሳ ተመስሎ ትንቢት የተነገረለትና ትንቢቱን፥ ምሳሌውን ለመፈጸም በራሱ ቅዱስ ፈቃድ ወደ ዓለማችን መምጣቱን ነው። ክርስቶስ በአንበሳ ተመስሎ የተነገረውን ትንቢት በዘፍጥረት 49፥9–10፣ በመጽሐፈ ራእይ ም.5፣5 ማየት ይቻላል። ይህም ዕጓለ አንበሳ (ክርስቶስ) ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት የተወለደ፣ ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው አንድ ለአባቱ ሲሆን፣ በማዕከለ ዘመን ደግሞ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ያለምድራዊ አባት በግብረ መንፈስ ቅዱስ ተፀንሶ የተወለደ አንድ ለእናቱ ነው።

የዚህም ሁሉ ተቀዳሚ ትንቢት «እነሆ ድንግል በድንግልና ፀንሳ ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች፥ አማኑኤል ማለትም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ሆነ በሥጋ ተዛመደን ማለት ነው» (ኢሳ. 7፡14) ተብሎ ተጽፎአል።

ነቢዩ ሕዝቅኤልም ቅድስት ድንግል ማርያም ጌታን ከመውለዱዋም በፊት ሆነ ከጌታ መወለድ በኋላም በንጽህና በቅድስና በድንግልና መኖርዋን በምዕ. 44፥1–3 የእስራኤል አምላክ የሆነ ጌታ እግዚአብሔር የገባበት ምሥራቃዊት የቤተ መቅደስ በር ለዘለዓለም ተዘግታ እንደምትኖር የጌታችን እናት ቅድስት ድንግል ማርያምም በድንግልና ጸንታ የመኖር ዕድል ሀብተ ድንግልና የተሰጣት መሆኑን በመግለጥ ጽፎልናል።

አንዳንድ ስሑታን እንደሚሉት ሌሎች ልጆች ኖረዋት ቢሆንማ ጌታ በመስቀል ላይ እያለ እንኳ ያልረሳት ቅድስት ድንግል እናቱ በእግረ መስቀል ስር ወድቃ ስታለቅስ አይቶ በመራራት የሚወደውን ደቀመዝሙሩን ዮሐንስን ጠርቶ «እነሆ ልጅሽ፥ ለአንተም እነሆ እናትህ» ብሎ ማረካከብ ባላስፈለገውም ነበር።

ለሞግዚትነት ለአደራ ጥበቃ የተመረጠው አረጋዊ ዮሴፍ በእጮኛነት ስም የተጠራበት ምክንያት በጥንት ስርዓተ አይሁድ ማንኛዋም እስራኤላዊት ድንግል ከአስራ አምስት ዓመት በኋላ ያለ ባል መኖር ስለማትችል ባል አልባ ከመባል ሊጠብቃት፣ ክርስት እንዳትነቀል ጠበቃ ሆኖ እንዲቆምላት ታቅዶ የተፈጸመ ሃይማኖታዊ ሥርዓተ አበው ነው። አረጋዊ ዮሴፍን በወጣትና በጎልማሳ መልክ እየሳሉ የልደት ካርድ በማሳተም ባል ለማስመሰል የሚደረገው ሁሉ ልንቀበለው የማይገባ የባዕዳን ህዝብ አጉል ባህል ነው። አረጋዊ ዮሴፍ ለእመቤታችን አደራ ጥበቃ፣ ለሞግዚትነት ከመመረጡ በፊት ከሌላ ሚስት የወለዳቸውን ልጆች ሁሉ ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደ አስመስሎ ማቅረብ ትልቅ ስህተት ነው። ጸሀፍትና ፈሪሳውያን በጠላትነት የጌታ ወንድሞች ብለው የጠሩዋቸው ልጆች ሁሉ (ማቴ. 13፥54–57) እንደ ሰውኛው አባባል ከሆነ ለእመቤታችን እንደ እንጀራ ልጆች መቆጠር የሚገባቸው ናቸው። እርስዋ ግን እንደ እንጀራ ልጆች ሳታይ እንደ ፀጋ ልጆችዋ ትንከባከባቸው ነበር። ለምሳሌ፣ የሁሉም ታናሽ የሆነውን ያዕቆብን ከጌታ ሳትለይ ሐሊበ ድንግልና እያጠባች ስላሳደገችው ብቻ የጌታ ወንድም ተብሎ ተጠርቷል። ይህ አስገራሚ አይሆንም። ምክንያቱም እንኳንስ አብረውት ያደጉትን የቤተሰብ አባላት ይቅርና ጌታ ከተወለደ ሰላሳ ዓመት በኋላ ለሐዋርያነትና ለአርድእትነት የመረጣቸውን ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት፣ ቅዱስ ፈቃዱን ለመፈጸም የተዘጋጁ አማኞችን ሁሉ ወንድሞቼ፥ እህቶቼም ብሎ ሲጠራቸው እናያለን (ማቴ 12፥50)፣ ወዳጆቼም ይላቸዋል (ዮሐ. 15፡14)

ስለዚህ በእንደዚህ ያለው ጉዳይ ክርክር የሚያነሱ ሰዎች ሁሉ ጊዜ ለማጥፋት ካልሆነ በቀር ለክርስቲያናዊ ሕይወት መታነፅ አስበው የሚያደርጉት አይደለም። ይህ ጉዳይ ገና ከአራተኛው ምዕተ ዓመት መደምደሚያ በፊት የነበሩ ሊቃውንት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ተከራክረው እንስጥሮስንና ተከታዮቻቸውን አውግዘው በመለየት ፍትሐ ነገሥትና ቀኖና ቤተክርስቲያን ጽፈው ፈርመውበት የተዘጋውን ፋይል ከ1600 ዓመት በኋላ ለመክፈት መሞከር ገደብ የለሽ ውጣ ውረድ የመፍጠርን ዝንባሌ ያሳያል። ስለሆነም በነጋ በጠባ ቁጥር ከነርሱ ጋር መነታረኩ ለነገረኛ ሰው መመለስ ለቱኋን ልጓም ማጉረስ እንደተባለው ማጎለቅት የሌለው ያማ ከናፍር ነው።

መልካም ዘመነ ልደት ይሁንላችሁ እያልኩ በሌላ ዝግጅት እስክንገናኝ ጤና ይስጥልኝ።

መጋቢ አእላፍ መከብብ አጥናው

# ኑሮ በአሜሪካ

በአሜሪካ ኑሮአችሁ ምን ገጠማችሁ? ኑሮን ለማመቻቸት በሚደረጉ ጥረቶች ላይ ባሉ የማህበራዊ ኑሮ ችግሮች ላይ ለመወያየት ይህ አምድ አስተዋጽኦ ያደርጋል የሚል እምነት አለን። በውይይት የጋራ መፍትሄ ለማግኘት ይቻላል። በተጨማሪም በዚህ አገር ኑሮአችን ተሰባስበን በጋራ የምናከናውናቸውን ተግባራት ለማስተዋወቅም ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል እንላለን። በአምዱ ላይ በተለይ ካልተጠቀሰ በስተቀር የሚቀርቡት አስተያየቶችም ሆኑ የገጠመኝ ታሪኮች አንባብያን የሚልኩልን መሆኑ ይታወቅልን።

## <u>እልፍ ሲሉ እልፍ ሊገኝ!!</u>

### ከአትናትዮስ

### ክፍል 12

### (የመጨረሻው ክፍል)

«ሶስት ቀን ቆይተህ ለመሄድ አልነበረም እንዴ የመጣኸው? አለችኝ ትዝታ ደግማ።

«አሁን እሱን ማንሳት ምን ይጠቅማል? እንደሚመስለኝ በዚሁ ማብቃቱ ጥሩ ነው።» አልኳት ለዘብ ብዬ። በየሰከንዱ ለሚለዋወጠው (Unstable) ያልተረጋጋ ባህርይዋ እኔ ሰለባ የምሆንበት ሁኔታ አልታይህ ብሎኝ።

«ታዲያ ቁርስ ላቅርብና ትንሽ ነገር አፍህ አድርግ።» አለችኝ።

ትላንት ማታ አውሬ የነበረችው ትዝታ ሳትሆን ሌላ ሰው መስላ ታየችኝ። ይህም አስፈራኝ።

«ግዴለም፣ እዚያው አይሮፕላን ማረፊያ እበላለሁ» አልኳት ወደመጣሁበት አገር ተመልሼ ለመሄድ በውል መቁረጤን እንድትረዳ ብዬ።

«እንዴ ዛሬውኑ ልትሄድ? አገሩን እንኳ ሳትጐበኝ?» አለችና ፈገግ ብላ ወደ ወጥ ቤት ገባች።

ነገረ ሁኔታዋ እየገረመኝ ቁጭ አልኩ። ታክሲ ካልጠራችልኝ ወይ እሷ ካላደረሰችኝ ምንም መሄጃ አልነበረኝምና የነበረኝ አማራጭ መቀመጥ ብቻ ነበር።

«እንዲያው ቶሎ ቅይም ትላለህ አንተ ደግሞ» አለች በስኒ ይዛልኝ የመጣችውን ቡና በእጄ እየሰጠችኝ።

«እንግዲህ ጠባዬ ስለሆነ ምን ላድርግ ብለሽ ነው» አልኳት የሰጠችኝን ቡና ምስጋና አቅርቤ እየተቀበልኩ።

እሷም ሲኒ ቡናዋን ይዛ ፊት ለፊቴ ወንበር ስባ ቁጭ አለች።

«ምንድነው አንተ እንዲህ የሚያደርግህ? ነገሩ ሁሉ ትንሽ ስለተምታታብኝና ግር ስላለኝ ምናልባት የሚያስቀይም ነገር ብዬህም ከሆነ ትንሽ ትዕግስት ማድረግ አይኖርብህም እንዴ?» አለች በሚያሳዝንና አንጀት በሚበላ የአነጋገር ለዛ።

«ቱሪስት ብዬ» አልኩ በሆዴ። ለሌላ ዙር የራስ ምታት እያዘጋጀችኝ መሆኑ መሰለኝ።

«ምንድነው የተምታታብሽ ነገር?» አልኳት ፍርጥም ብዬ።

«አስበው እስቲ፤ ገና መተያየታችን ነው። ከዚህ በፊት በስልክ እንጂ ብዙ ንግግር የለን። ገና በመጀመሪያው ቀን የተደረገውን ሁሉ መፈፀም የነበረብን ስላልመሰለኝ ነው። ተምታታብኝ ያልኩህ» አለችና አንገቷን ደፍታ ዝም አለች።

እኔ ፈልጌ ሳይሆን አንቺው ባመጣሽው ግፊት ነው ብላት እንደገና ሌላ ጦርነት ሊከፈት ሆነ። ዝም ብል ደግሞ በእኔ ግፊት የተደረገ ነው ብዬ ማመኔ ሆነ። ቢሆንም ከእሷ ጋር ከእንግዲህ ወዲያ ምንም ዓይነት ግኑኝነት እንደማይኖረኝ የቆረጥኩበት ጉዳይ ስለሆነ የፈለግሁትን ብናገር የምችል መሆኔ ተሰማኝ።

«የመፈቃቀድና የመፈላለግ የስሜት ግፊት ጉዳይ ሆኖ የተፈፀመ ነገር በመሆኑ ያ ለምን ሆነ ብለሽ በዚያ ሳቢያ ሌላ ችግር መፍጠር አግባብ አልመሰለኝም» አልኳት።

«የስሜት ግፊት ጉዳይ ላልከው ከእኔ የመነጨ ነው ብዬ ለማመን አልችልም፤» አለች።

«እሱ እንዳልሽው ይሁን። ለማንኛውም ያ ያለፈና የሆነ ጉዳይ ስለሆነ እንዳልሆነ ልናደርገው ስለማንችል እንተወው። ለወደፊቱ ግን አንቺን በወንድምነት የምመክርሽ ነገር ቢኖር አንድን ነገር አስብሽውም አላስብሽውም ከፈፀምሽው በኋላ ልትመልሺው የምትችይው ጉዳይ ስላልሆነ በመፈፀሙ ስትበሳጪ መዋልና ማደር አይኖርብሽም። የፈፀምሺው ነገር ከሆነ በኋላ ስህተት ማድረግሽ ከተሰማሽ ለወደፊቱ ያ እንዳይሆን በትምህርትነቱ ማስታወስ እንጂ አሁንም አሁንም እሱኑ እያነሱ ራስን ብቻ ሳይሆን በአካባቢው ቅርበት ያለውን ሰው ሁሉ ማወክ ተገቢ አይመስለኝም።» አልኳት ፍርጥ አድርጌ ብታብድም ትበድ ብዬ።

«ሆደ ባሻ ነህ? ቶሎ ይከፋሃል» አለችና

ካለችበት ተነስታ እኔ ወዳለሁበት ቦታ ተቀመጠች። ትናደዳለች ብዬ አስቤው የነበረው ሌላ ሆነ። ቁራሽኑ እኔን ማባበል ያዘች።

«እና አየህ ለኑሮ ጥሩ አይደለም። ቶሎ ብስጭት ማለት፣ አይመስልህም?» አለች።

ሴቶች መሳሳታቸውን ላለመቀበል የሚጠቀሙበት ዓይነት ዘዴ በመሆኑ ተነስታ እኔ ጋ ቀረብ ማለቷና በአጠቃላይ የሁኔታዋ መለዋወጥ ብዙም አዲስ አልሆነብኝም። የጀመርኩትን ምክር የመስጠት ጉዳይ እንዳልቀጥል የመፈለግ አዝማሚያዋ መሰለኝ። እኔ ግን ተርጫለሁና ቀጠልኩኝ።

«ስሚ የእኔ እህት፤ ስለእኔ ቶሎ መከፋት አለመከፋት ብዙም አያሳስብሽ። ይልቅስ አንቺ ያለሽበትን ሁኔታ በደምብ መርምረሽ የሚበጀውን ለማድረግ እንድትችዪ ምክሬን ተቀበይ። ቅድም ያልኩሽን እንደገና ልድገምልሽ። የሆነ ነገር እንዳልሆነ ሊሆን አይችልምና ቀደም ብለሽ ባደረግሽው ነገር እየተፀፀትሽ ጊዜሽን ማባከን አይኖርብሽም። ይህ ትልቁና ዋናው የምሰጥሽ ምክር ሲሆን ሌላው ደግሞ ሃሳብን ረጋ አድርጎ ውሳኔ ላይ የመድረስ ችሎታሽን ማዳበር እንዳለብሽ ነው የምመክርሽ።" አልኳት ኮስተር ብዬ።

"ውሳኔ ላይ የመድረስ ችሎታ ስትል አልገባኝም፤" አለችና ጠየቀችኝ።

"ልጠይቅሽ እስቲ፤ በውነቱ ባል ለማግባት ተዘጋጅተሻል ወይ? ይህን ስል በዕድሜሽ ማለቴ አይደለም፤" ብዬ ጥያቄዋን በጥያቄ መለስኩት።

"በዕድሜሽ አይደለም ስትል ምን ለማለት ፈልገህ ነው?" ዓይኗ ፈጠጥ አለ፤ እንደመቆጣት ሊዳዳት እንዳለ ያስታውቅባታል። የዕድሜ ቆጠራው ጉዳይ ቀርቶ ቃሉ እንኳ ሲጠራ ሴቶች ለምን ትዕግሥት እንደሚያሳጣቸው ዘላለም ይገርመኛል።

ያኔ ግን ብትናደድም የራሷ ጉዳይ በሚል፤ "ዕድሜሽ ለጋብቻ ከመድረስም ሌላ አልፈሻል ለማለት ነው።" አልኳት።

ከት ብላ ሳቀችና "ቆመሽ ቀርተሻል ማለትህ ነው! ገባኝ! እሺ ሌላ የምትለው ስድብ አለህ?" አለች የሚያናድድ ዓይነት ሳቅ እየሳቀች።

"እውነቱን መናገር እንደስድብ ሊያስቆጥር አይገባም። ለማንኛውም ለጋብቻ ዝግጁ ነሽ ወይ? ብዬ የጠየቅሁሽ ምን ለማለት ፈልጌ እንደሆነ ላስረዳሽ፤ እንደምታውቂው ጋብቻ ወይም ትዳር መስዋዕትነትን የሚጠይቅ ትልቅ ተግባር ነው። ለራስ ብቻ ማሰብ ቀርቶ ለትዳር ጓደኛ፣ ቀጥሎም ለሚወለዱ ልጆች የማሰብ ተግባር ያለበት ትልቅ ኃላፊነትን የመቀበል ዝግጁነትን ይጠይቃል። ጋብቻ ሰዎች ስላደረጉት ብቻ በፉክክር ከመሬት ተነስቶ የሚፈፀም አይደለም። እና አንቺ ለዚህ መስዋዕትነት ልብሽ ወይም ራስሽ የተዘጋጀሽ ነሽ ወይ?" አልኳት።

"አንተስ ምን ይመስልሃል? አዋቂ አይደለህ?" አለች። ጥያቄዬን በጥያቄ መልሳ። መናደዷን እንዳላውቅባት በጣም እየጣረች እንዳለች ገባኝ። ንዴቷን ፈልጌ የተናገርኩ ስለመሰላትና እኔን ላለማስደሰት ስትል መናደዷን ውጣ የያዘችው እንደሆነ ያስታውቅባታል።

ተራዬን ፈገግ አልኩ፤ "አንቺው ተጠያቂዋ ብትመልሽው አይሻልም፤ የኔን ግምት ከመውሰድ?" አልኳት ዘና ብዬ።

"የኔን ተወውና እስቲ ራስህን ልጠይቅህ፤ አንተ ለዚህ መስዋዕትነት ዝግጁ ነህ ወይ?" አለችኝ።

"ዝግጁማ ሆኜ ነው ላይሆንልኝ እዚህ ድረስ የለፋሁት፤" አልኳት ፍርጥ አድርጌ።

"አልሆነም ብለህ ውሳኔ ላይ ደረስክ እንዴ?" አለችና እንደገና ፈገግ አለች በማግባባት መልክ።

ንዴቴ ሲመጣ ተሰማኝ። አነጋገሯ፣ አባባሏና በአጠቃላይ በየሰኮንዱ የሚለዋወጠው ፀባይዋና ሁኔታዋ እያስጠላኝ መምጣቱ የበለጠ ታወቀኝ። ለቆረጥኩበት ነገር መቆየትና ወሬ ማብዛት ትርፉ ራሴን ማሳመም መሆኑን ተረዳሁና ከመቀመጫዬ ብድግ ብዬ ሻንጣዬን አነሳሁ። ብታደርሰኝ ባታደርሰኝ ጉዳዬ አልነበረም። ከዚያ ቤት መውጣቱን ብቻ ነበር የፈለግሁት። ትዕግሥትም እኮ ወሰን አለው።

"በይ ቻው!" አልኩና የውጪ መውጫውን በር ከፍቼ ከቤቷ ወጣሁ። ትንሽ ሄድ ብዬ ታክሲ ማግኘት እችላለሁ ብዬ በመወሰኔ መለስ ብዬ ለማየት እንኳ ቤቱን ተጠየፍኩት። እሷ ትከተለኝ አትከተለኝ ያየሁትና የማስታውሰው ነገር የለም። የምን መሚዘዝ ነው "እልፍ ሲሉ እልፍ ሊገኝ!" ካለችበት ግቢ ከአንድ ነገር እንደሚሸሽ ሰው እየተንደረደርኩ ስወጣ ታክሲ አገኘሁ። አበሻ ነበር ታክሲ ነጂው።

"ታዲያስ!" አለኝ።

"አለና!" አልኩት።

"ወዴት ነው?"

"ኤርፖርት" አልኩት።

በቃ! ቃል ሳልተነፍስ ኤርፖርት ደረስኩ። ታክሲ ነጂው ገርሞት አስሬ በመስታወቱ ሲመለከተኝ አይቼዋለሁ። ሁሉም ነገር አስጠላኝ በተለይ እዛ ከተማ ያለ ነገር ሁሉ፤ እሷ ያለችበትን ከተማ እየረገምኩ ሁለተኛ ላለመመለስ ወደ መጣሁበት ተመለስኩ።

* * *

ተ ፈ ፀ መ

# « ቅ ም ሻ »

(ከጥምቀተ አርዲዮን)

ባለፈው ስለቆምጫምባው እንደገና እንደምመለስ ቃል ገብቻለሁና ዛሬ አንዱን ላውጋችሁ!

ጓድ ቆምጭአምባው የጉጂም ክፍለሃገር አስተዳዳሪ ጋ ለስራ ጉዳይ ተጠርቶ ይሄድና አንዳንድ ጥያቄዎች ቀርበውለት ሲመልስ ይቆይና በቅርቡ በአቸፈር ወረዳ ስላቋቋመውና እሱ ስለሚመራው ማህበር ወቅታዊ ሁኔታ ተጠየቀ። ማህበሩ እንዴት ነው አዝማሚያው ሲባል «ቀና ነው» አለ። ተጠናክሮላችኋል ወይ ሲሉት «ግጥም አድርጉ» አለ። ምን ያህል ናችሁ ሲባል «የት የለሌ» ነው አለና ለመሆኑ ማህበራችሁ ሴቶችን ያቅፋል ወይ ሲባል «ኋላ ማታ ማታ ሴቱን እማያቅፍ ማን አለ?» አለ ይባላል።

* * *

ሁለት ጓደኛሞች አንድ ቦታ ቁጭ ብለው ቡና እየጠጡ ስለኑሮዋቸው ሲጨዋወቱ ይቆዩና በጨዋታቸው መሃል ስለ አንዳንድ ሱሶች ማለትም ስለሲጋራ ሱስ ይነሳና አንደኛው ጓደኛ አጫሽ ጓደኛውን እንደው ወንድሜ እንደምንም ብለህ ይህን ሲጋራ ለማቆም ብትተወው ጥሩ ነበር። ሰሞኑን ባነበብኩት አንድ ጋዜጣ ላይ በየቀኑ በሲጋራ ማጨስ ምክንያት ብቻ ... ሰዎች ይሞታሉ፣ ... ሰዎች በሳምባ ካንሰር በሽታ ይለከፋሉ፣ ... ሰዎች ደግሞ በ.. ብሎ ሳይጨርስ፤ አጫሽ ጓደኛው ከመቀመጫው ይነሳና እኔ ያነበብኩትን ልንገርህ በሶስተኛው ዓለም ከሚሞተው የህዝብ ብዛት ትልቁን ቁጥር የያዘው ሰዎች በማያገባቸው ነገር እየገቡ በሚያወሩት ወሬ ነው ብሎት እርፍ።

* * *

መቸም የጓድ ሊቀመንበር መንግስቱን ሚስት ውብአንቺን ቢሻውን የማያውቅ የለም (የአሁኑን ፕሬዚዳንታችን ሚስት ግን አውቃለሁ የሚል ባይኖርም)። እና ወይዘሮ ውብአንቺ ጓድ ሊቀመንበር አንዳንዴ ጊዜ አግኝተው ቤት በዋሉ ቀን ቡና የሚያፈሉላቸው ራሳቸው ባለቤታቸው ውባንቺ ናቸው ይባላል። እና እንደተለመደው አንድ ቀን ቡናው ተፈልቶ ለጓድ ሊቀመንበር በአሳላፊው ሲሰጣቸው፤ ጓድ ሊቀመንበር ፊታቸውን ጭፍግግ አድርገው ወ/ሮ ውቤ ለምንድነው ሁልጊዜ እንደበረዶ የቀዘቀዘ ቡና የምትሰጡኝ ብለው የሙያ ጥያቄ አቀረቡ። ወ/ሮ ውባንቺም ኧረ ጓድ ሊቀመንበር እኔስ ትኩሱን ነው የምሰጠው። ነገር ግን አሳላፊው ላንተ ሊሰጥህ ሲል «ጓድ መንግስቱ ኃይለማርያም የኢትዮጵያ ወታደራዊ መንግስት አስተዳደር ሊቀመንበር፣ የመከላከያ ሚኒስትርና የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም፣ የኢሠፓአኮ አንደኛ ፀሐፊ፣ የወቅቱ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ፀሐፊ፣ የ... » በማለት ይህንን ሁሉ እስኪጠራ ድረስ ነው ቡናው የሚቀዘቅዘው ብለው አስረዷቸው ይባላል።

* * *

የመጠጥ ሱስ ያለባቸውን ሰካራሞችን ከስካር ባህርያቸው ለማላቀቅ ትምህርትና ምክር የሚሰጥበት ማዕከል ውስጥ የሆነ ነው።

ሱሰኞቹ ቁጭ ብለው በጽሞና ከፊት ለፊታቸው ካለው አስተማሪ የሚሰጠውን ትምህርት ይከታተላሉ። አስተማሪው ትምህርቱን በምሳሌ ለማስረዳት ሁለት ጠርሙሶችን ከፊት ለፊት ያደርግና በአንደኛው ጠርሙስ አልኮል መጠጥ በሌላኛው ጠርሙስ ደግሞ ውኃ ይቀዳል። ከዚያም በመጀመሪያ ውኃ በቀዳበት ጠርሙስ ውስጥ ትሎች ይጨምራል። ትሎቹ ውኃ ውስጥ እንደገቡ ከላይ እታች እያሉ ሲንቀሳቀሱ ይታያሉ። እንደገና አልኮል ባለበት ሁለተኛው ጠርሙስ ተመሳሳይ ትሎች ውስጥ ሲጨምር ትሎቹ መንቀሳቀስ ቀርቶ ወዲያው እንደገቡ ድርቅ ብለው ይቀራሉ፤ ይሞታሉ።

ከዛ አስተማሪው ወደ ተማሪዎቹ ይዞርና «በሉ እንግዲህ ካያችሁት ነገር ምን ትምህርት አገኛችሁ?» ብሎ ይጠይቃቸዋል።

አንደኛው የመጠጥ ሱሰኛ ብድግ ይልና «ቀላል ነው» አለ። «አልኮል ባለበት ሆድ ውስጥ ትሎች ሊኖሩ አለመቻላቸውን ነው የተማርነው» አለ ይባላል።

* * *

# ሰንጠረዥ ፮

በሰይፉ ኣዳነች ብሻው

(መ) መብቱ የተጠበቀ ፲፱፻፺፱ ዓመት

SAEFU © Copyright 1997

ይህን የሰንጠረዥ ጨዋታ ምንባቡ ውስጥ ያሉትን ቃላት ከግራ ወደ ቀኝ፣ ከቀኝ ወደ ግራ፣ ከላይ ወደ ታች፣ ከታች ወደ ላይና በሰያፍ ፈልጋችሁ በመክበብ የቀሩት ሆሄያት የሚያነቡትን በመፈለግ በጊዜዎት ይዝናኑ።

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| እ | ን | ጀ | ራ | እ | ና | ት | ባ | አ | ራ | ጀ | ን | እ | የ |
| ኧ | ብ | ሰ | ተ | ረ | ብ | ኀ | ዕ | እ | ቁ | ብ | ኀ | ዛ | አ |
| ቅ | ረ | ት | ና | እ | አ | ድ | ድ | ቅ | ብ | ረ | ሬ | ን | ዲ |
| መ | ጎ | ባ | ታ | ህ | ገ | ር | ር | ሐ | ር | ዪ | ድ | ት | ሰ |
| አ | ች | አ | ቃ | ት | ረ | ኽ | ዘ | ደ | ቱ | ነ | ብ | ነ | ዘ |
| ያ | ያ | ክ | ለ | ረ | ሀ | መ | አ | ኢ | ት | ት | ራ | ም | መ |
| ት | ድ | ስ | አ | ጥ | ን | ቶ | ት | መ | እ | ሠ | ላ | ም | ን |
| ያ | ል | ት | ይ | መ | ጥ | ዮ | ሥ | ም | ት | ራ | ት | ስ | መ |
| አ | ው | ን | ለ | ወ | ጵ | ራ | ር | ራ | ማ | ተ | ረ | ፀ | ጠ |
| መ | ት | ወ | በ | ያ | ት | ይ | ደ | ት | አ | ኛ | ብ | ሐ | ያ |
| ድ | ጫ | ነ | የ | በ | ታ | ች | አ | ለ | ቃ | ስ | ኀ | ፊ | የ |
| ቅ | ጠ | ን | ፃ | ር | ር | ቀ | ቶ | ር | ሁ | ም | ኪ | ል | ቅ |
| ጦ | ር | ነ | ት | ነ | ብ | አ | ር | ቀ | ፋ | መ | ግ | ያ | ክ |
| ር | ግ | ማ | ና | ር | ድ | መ | ሠ | ለ | ፍ | ት | ሪ | መ | ጅ |

ሐቅ
መምራት
መሪ
መሠለፍ
መሥራት
መጠያየቅ
መፋቀር
መኸር
ምሁር
ምራት

ሠላም
ሠርቶ አደር
ሠራተኛ
ሥራ አስኪያጅ
ስምምነት
ብርታት
ቀብር
ቅመ አያት
ቅድመ አያት
ትርታ
ትውልድ
ትግል

ኅብረተሰብ
ኅብረት
ነፃነት
አማት
አብነት
አባት
አንድነት
አክስት
አያት
አገርህን
አጎት
አዲስ ዘመን
እህት

እቁብ
እትብት
እንጀራ እናት
እናት
ኧረ
ዕድር
ዕድገት
ወጥቶ አደር
ዘመን መለወጫ
የበላይ አለቃ
የበታች አለቃ
የእንጀራ አባት

የዛሬዪቱ ኢትዮጵያ
ድርና ማግ
ጥረት
ጦርነት
ፀሐፊ


ያለፈው የሰንጠረዥ ፭ መልስ "ፍትኅና ሰብዕና የሕዝብ የተፈጥሮ መብቶች ናቸው" ነበር።

* የዚህን ሰንጠረዥ መልስ ያገኘች ቤዛ ታደሰ ከለንደን ብቻ ነች።


## <u>ያለፈውን ሰንጠረዥ የመለሱ</u>

1. አስናቀ አሰፋ—ከሂውስተን ለ5ኛ ጊዜ
2. ተስፋሁን ልጅ ዓለም – ከኦሃዮ ለ4ኛ ጊዜ
3. ትዕግስት ጥላሁን –ከሴንት ሉዊስ ለ3ኛ ጊዜ
4. አሸብር አበበ – ከሎስአንጀለስ ለ2ኛ ጊዜ
5. ሳራ አምሳሉ – ከፊላዴልፊያ

(ሳያቋርጡ 5 ሰንጠረዥ በትክክል ሞልተው በወቅቱ በአድራሻችን ለሚልኩ ሶስት እትም በነፃ እንሸልማለን)



# በቃላት ሰንጠረዥ



## <u>ወደ ጐን</u>

1. ፎርመኛ
4. የአማርኛ መጽሔት
7. የሚያብለጨልጭ ድንጋይ
9. ድሮ
11. ማዋረድ
12. አትጩህባት
13. ያረጀች ሴት
15. አልጠበቀም
17. ብስለት
19. የሚያስመልስ
22. ተወስዶባታል
24. ቲያትር
25. አንኳሰሰ
26. 1/4ኛ
27. ከፍተኛ ዋጋ ያለው
28. የቴዎድሮስ መድፍ
30. ለማሽሟጠጥ
33. ከውካዋ ናት

## <u>ወደ ታች</u>

1. የሚገለደም
2. የሚቀባ
3. ጠብ
4. የበግ ጭራ
5. ነካ አደረጋት
6. ጽሑፉን ትመልከት
8. እሪታ
10. የተቀቀለ እህል
11. ደረሰባት
12. አትኮራረፉ
13. አሳባፊ
14. ተናዳፊ
16. ችግር
18. በእሳት ትቃጠል
20. ግጥሚያ
21. ታንድድ
23. ትችት
27. እውነት ያልሆነ
29. _____ ብሎ አያት
31. ባዶ
32. ሴራ

# የላንዳፍታ መጽሔት ማዘዣ ቅጽ

የላንዳፍታ መጽሔት እንደታተመች ወዲያውኑ ካሉበት ቦታ
እንዲደርሶት ይህንን ቅጽ በመሙላት ከነክፍያው ይላኩልን።

| | 12 ISSUES | | 6 ISSUES | |
|---|---|---|---|---|
| U.S | $30.00 | ☐ | $16.00 | ☐ |
| Canada | $40.00 | ☐ | $22.00 | ☐ |
| Europe | $56.00 | ☐ | $30.00 | ☐ |
| Asia | $70.00 | ☐ | $38.00 | ☐ |
| Institutions | $80.00 | ☐ | $40.00 | ☐ |

*(please, mark your choice above and send your payment in U.S. Dollars)*

*Subscriber's Name:* ______________________

*Address:* ______________________

*City:* ______________________

*St.* __________ *Zip* __________ *Phone: (     )* __________

==========================================================

*I would like to order for my friend as well. I have included both payments.*
*My friend's name and address are as follows.*

*Subscriber's Name:* ______________________

*Address:* ______________________

*City:* ______________________

*St.* __________ *Zip* __________ *Phone: (     )* __________

==========================================================

*TOTAL PAYMENT ENCLOSED: $* ☐

*LANDAFTA, P.O.BOX 49301, Atlanta, GA 30359*

# L & M GLOBAL SERVICES, INC.

450 N. Indian Creek Dr., Clarkston, GA 30021
Phone: 404-296-3088 - Fax: 404-296-7413

## ታክስ በማዘጋጀት ልምድ ባላቸው፤

- ✈ የግልና የንግድ
- ✈ ፈጣን የታክስ አገልግሎት
- ✈ ፌዴራልና ስቴት
- ✈ አሜንድድ ሪተርን

ጥያቄ ካልዎት ለአከን ያነጋግሩ።

ለአከ ማለደ — LEAKE MALEDE

AUTHORIZED IRS e-file PROVIDER

**BE THE FIRST**
***IN YOUR NEIGHBORHOOD***
**TO GET A**
***TAX REFUND!!***

## RTS ACCOUNTING & INCOME TAX SERVICE

Professional Tax Preparation

- ➢ Indiviadual & Business
- ➢ Electronic Tax Filing
- ➢ Federal & State Return
- ➢ Amended Return

### Other Services:

- ⇒ **Prepare monthly Sales Tax Report**
- ⇒ **Prepare Business Loan Package**
- ⇒ **Book Keeping Service**

Choose how fast you want your Refund:

- ♦ Electronic Refund
- ♦ Direct deposit
- ♦ I.R.S. Check

**REFER A FRIEND AND GET A FREE $5.00 PHONE CARD!!**

## GRAND OPENING!!

# ONE-STOP FOOD MART

450 N. Indian Creek Dr., Clarkston, GA 30021
Phone: 404-296-3088 - Fax: 404-296-7413

- COLD BEVERAGE
- GROCERY
- MONEYGRAM
- SOFT DRINK
- FRESH COFFEE/GOURMET
- LOTTERY

BEST PRICE IN TOWN!
COMPARE & SAVE

Drive through window service available

We are located at Campus Plaza Mall across from Dekalb Book Store


# አትላንታ በኢትዮጵያውያን የሚሰጡ አገልግሎቶች
# ETHIOPIANS SERVING ETHIOPIANS IN ATLANTA

ኢንሹራንስ

**Allstate®**
You are in good
4122 East Ponce DeLeon Ave. Suite 4
Clarkston, GA 30021
Phone: (404)508-8978 - Fax: (404)299-6266

- AUTO
- HOME OWNER'S
- RENTERS
- LIFE
- BUSINESS
- COMMERCIAL AUTO

**CALL US FOR NEW & USED CARS LOAN**



Theodros Hailegiorgis
*Exclusive Agent*

Allstate Life Insurance Company, Northbrook, IL
Allstate Indeminity Company, Northbrook, IL
Allstate Commercial Companies
(subject to limitations and availability)

**You're in good hands.**

---

ቤትና ንግድ መግዛት

**RE/MAX®** today's inc.
an independent member broker

Remax Today's Inc
1597 Phoenix Blvd Suite 5
College Park, GA 30349

የንግድ ሥራ መግዛት ለምትፈልጉ
Business Broker - Convinient Store
Liquor Store - Dry Cleaning & so on
FINANCING AVAILABLE

- √ Residential
- √ Commercial
- √ Business
- √ Relaocation
- √ Forclosures
- √ HUD

ቤት መግዛት ለምትፈልጉ መሬትም ገዝታችሁ መሥራትም ሆነ Subdivision ውስጥ ለማሠራት የምትፈልጉ ሁሉ ደውሉልኝና እረዳችኋለሁ። የክሬዲት ችግር ቢኖርብትም ደውሉልኝ! ሁልጊዜ ኮሚሽን የምከፈለው በሻጭ ነው



ሰላማዊት ታደሰ
Selamawit "Sammy" Tadess
Realtor
Tel. (770)907-0525
(770) 907-0183
Voice Mail: (770)798-7496
Fax: (770)907-0524

---

የጉዞ ወኪል

MRA'G TRAVEL, Inc.
ሚራዥ የጉዞ ወኪል
*International - Business - Leisure - Cruise*
92 Piedmont Ave. NE - Atlanta, GA 30303

ለአለም አቀፍና
ለአገር ውስጥ ጉዞዎ አለንልዎ!

EXCELLENT SERVICE - SPECIAL FARE - GROUP FARE

Please, call (404)577-4404
(404)577-4682
(404)577-4889
Fax: (404)222-9305

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ልዩ ወኪል
CONSOLIDATOR FOR
*ETHIOPIAN AIRLINES*



ገነት ፈቀደ – ፕሬዚዳንት
GENET FEKEDE
PRESIDENT